የባልንጀርነትን ገመድ
የበጠሰ ወንጀል
ገጽ 10

ወጣቱ የተስከፈበት አዲስ ሱስ!
ገጽ 11

የጥቁር ድንጋይ ቴክኖሎጂ-
ለኮንስትራክሽን ግብዓት
ገጽ 14

ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
83ኛ ዓመት ቁጥር 082 ኅዳር 22 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






## «አረንጓዴ ዐሻራ ኢትዮጵያ ለብልጽግና ለምታደርገው ትግል ወሳኝ ድርሻ አለው»

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ:- የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብር ኢትዮጵያ ልማትና ብልጽግናን ለማሳካት በምታደርገው ትግል ወሳኝ ድርሻ አለው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በ28ኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ (ኮፕ28) ላይ ንግግር አድርገዋል።

በንግግራቸው የኢትዮጵያ የአረንጓዴ ዐሻራ ሥራ ከኢትዮጵያ አልፎ ለዓለም ሀገራት የአየር ንብረት ለውጥ መከላከል ወሳኝ ድርሻ እንዳለው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ገልጸዋል።

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቁ የደን ልማት ፕሮጀክት ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ መርሐ-ግብሩ የአካባቢ ጥበቃና ልማትን ከማሳደግ ባለፈ ለበርካቶች

«አረንጓዴ ዐሻራ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## ኢትዮጵያ በአራት ወራት ከወጪ ንግድ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ አገኘች

አማን ረሺድ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ባለፉት አራት ወራት ከወጪ ንግድ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ማግኘቷን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር

ኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ኃይሉ አዱኛ

## መንግሥት ለሰላማዊ ውይይት ሁልጊዜም በሩ ክፍት ነው

- በሸኔ ላይ የተጠናከረ ርምጃ እየተወሰደ ነው

ገጽ 4

## ኤች አይ ቪን የመከላከል ሥራ ቀዳሚ አጀንዳ ሊሆን ይገባል

- በዓመት ከ11 ሺህ በላይ ዜጎች በኤች አይ ቪ ቫይረስ ሕይወታቸውን ያጣሉ

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- በሀገሪቱ የኤች አይ ቪ (ኤድስ) ቫይረስን የመከላከል ሥራ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ቀዳሚ አጀንዳ ሊሆን እንደሚገባ ጤና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ በዓመት 11 ሺህ 322 ዜጎች በቫይረሱ ሕይወታቸውን እንደሚያጡ ተጠቁሟል፡፡

የዓለም ኤድስ ቀን «የማኅበረሰብ መሪነት ለላቀ ኤች አይ ቪ መከላከል» በሚል መሪ ሃሳብ ለ35ኛ ጊዜ ትናንት ተከብሯል፡፡ በወቅቱ የጤና ሚኒስትር ሊያ ታደሰ (ዶ/ር) ባደረጉት ንግግር ፤ የቫይረሱን ስርጭት ለመቀነስ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የመከላከል ሥራውን ከፍተኛ አጀንዳ ሊያደርጉት ይገባል፡፡

በሀገሪቱ የቫይረሱን የስርጭት መጠን በቫይረሱ ተጋላጭ በሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ ሊጨምር እንደሚችል ጠቁመው፤ በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም፣ የሲቪክ ማኅበራትንና የሌሎች ባለድርሻ አካላትን አቅም በመጠቀም ኤች አይ ቪን የመከላከል ሥራው ላይ በትኩረት ሊሠራ ይገባል ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ ከ610 ሺህ 350 በላይ ዜጎች ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ እንደሚገኝ የገለጹት ዶክተር ሊያ፤ በቂ የመድኃኒት አቅርቦትና ሕክምና ባለማግኘት በዓመት 11 ሺህ 322 ዜጎች በቫይረሱ ሕይወታቸውን እንደሚያጡ አስታውቀዋል፡፡

ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው ዜጎች በቂ ሕክምና እንዲያገኙና እራሳቸውን የማያውቁ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ምርመራ በማድረግ ጤንነታቸውን እንዲጠብቁ የማድረጉ ሥራ ተጠናክሮ መቀጠሉን አመልክተዋል።

ኤች አይ ቪ በደማቸው የሚገኝባቸው ዜጎች ሕክምና እንዲያገኙ እንዲሁም ሕክምና ከጀመሩት መካከል ደግሞ የቫይረሱ መጠን ዝቅ እንዲል የማድረግ ሥራ እንደሚከናወንም ገልጸዋል።

በየደረጃው በሚገኙ አስተዳደሮች ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከል የሚችል የሥራ አመራር ቦርድ በሚፈለገው ደረጃ አለመቋቋምና ሥራ ላይ አለመሆን፣ የኤችአይቪ ስርጭት ባለባቸው አካባቢዎች የሚሰጠው ምላሽ በቂ አለመሆን እንዲሁም ቫይረሱ በደማቸው ካለ እናቶች ለሚወለዱ ሕፃናት የሚደረገው ክትትል አናሳ መሆን፣ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚፈጠሩ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮች የቫይረሱን ስርጭት ለመከላከል ተግዳሮት መሆናቸውን አንስተዋል፡፡

በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ኤርቪን ጄ ማሲንጋ በበኩላቸው፤ የአሜሪካ ሕዝብና መንግሥት ኤች አይ ቪ/ ኤድስን ለመከላከል በኢትዮጵያ በተለያዩ ዓመታት ከሦስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ድጋፍ መደረጉን አውስተው፤ በቀጣይም አሜሪካ የምታደርገው ድጋፍ

ኤች አይ ቪን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡- ገበዘ ገብሬ

ሊያ ታደሰ (ዶ/ር)








ሰናይት መብሬ

# ማዕከላቱ

## ግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለሚያደርገው ሽግግር አበርክቷቸው ትልቅ ነው

**መስከረም ሰይፉ**

መቂ፡- የገጠር የሽግግር ማዕከላት ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለሚያደርገው ሽግግር አበርክቷቸው ትልቅ መሆኑን የኦሮሚያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ገለጸ፡፡

የኦሮሚያ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ሥራ አስፈጻሚ ሰናይት መብሬ እንደገለጹት፤ እንደሀገር ትልቅ የግብርና አቅም ያለ ቢሆንም ገበሬዎችን፣ ዩኒየኖችን፣ ላኪዎችንና ምርት አቀነባባሪዎችን አቀናጅቶና አስተሳስሮ የመሥራት ችግር አለ። የገጠር የሽግግር ማዕከላት እነዚህን ችግሮች በመፍታት ውጤት የሚያስገኙ ናቸው፡፡

የገጠር የሽግግር ማዕከላትም የቅንጅት ችግሮችን በመፍታት የግብርና ምርቶች ላይ እሴት ለመጨመር፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶች በሀገር ውስጥ በመተካት እንዲሁ ወደ ውጭ ለመላክ የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶችን ያማከሉና የግብርናውን ዘርፍ የሚያዘምኑ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የቡልቡላ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ በስሩ ስድስት የገጠር የሽግግር ማዕከላት ያሉት ሲሆን አንዱ የመቂ የሽግግር ማዕከል ነው ያሉት ሥራ አስፈጻሚዋ፤ ይህ የሽግግር ማዕከል ምርቶችን የማጠብ፣ የመለየት፣ ደረጃ የማውጣት ሥራ ሠርቶ ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኩ በመላክ በርካታ ሥራዎችን ያቀላል ብለዋል፡፡

ማዕከሉም ግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለሚያደርገው ሽግግር አበርክቶው ትልቅ መሆኑ አመልክተው፤ በማዕከሉ የተገነቡ ሼዶች ለቡናና ቅመማ ቅመሞች፣ ለሰብሎች፣ ለማርና ዋክስ፣ እንዲሁም ስጋና ጥራጥሬዎችን ማቆየት የሚችሉ ሲሆን ሙሉ መሠረተ ልማታቸው ተጠናቆ ለባለሀብቶች ክፍት መደረጉንም አብራርተዋል፡፡

ሥራ አስፈጻሚዋ የመቂ የገጠር የሽግግር ማዕከል ግብርናውን በማዘመንና ምርቶች ደረጃቸውን ጠብቀው ወደ ገበያ ለማድረስ ትልቅ ሚና እንደሚኖረው ገልጸው፤ ከዚህ በተጨማሪም በግብርና ዘርፍ ላይ የሚሳተፉ አካላት እኩል ተጠቃሚ የሚያደርግ ሥርዓት እንደሚገነባም ተናግረዋል፡፡

የመቂ የገጠር የሽግግር ማዕከል ሥራ አስኪያጅ መንግስቱ ታደሰ በበኩላቸው ማዕከሉ በአካባቢው ያሉ የግብርና ምርቶችን በመሰብሰብ ጥራታቸውን እንደጠበቁ እንዲቆዩ በማስቻል ለቡልቡላ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሚያቀርብ መሆኑ ገልጸዋል፡፡

ማዕከሉ 10ሺ ሄክታር ላይ ያረፈ ሲሆን በአካባቢው የሚገኙ አርሶ አደሮችን ምርት ተረክቦ መሥራት የሚያስችል አቅም ያለው ነው ብለዋል፡፡

የሽግግር ማዕከሉ መቂ ላይ እንዲቋቋም የተደረገው አካባቢው በግብርና ምርቶች ላይ ያሉትን ጸጋ በማየት ነው ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ አቅርቦትን በተመለከተ ስጋት እንደማይኖር አብራርተዋል፡፡

# 52 ሚሊዮን ኮንዶም ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶ በጥራት ፍተሻ ሂደት ላይ ነው

**አዲሱ ገረመው**



አዲስ አበባ፡- ለኤች. አይቪ. ኤድስ ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች በነፃ የሚሠራጭ 52 ሚሊዮን ኮንዶም ተገዝቶ የጥራት ፍተሻ ሂደት ላይ መሆኑን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በሚኒስቴሩ የኤች. አይቪ. ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር መሪ ሥራ አስፈጻሚ የዘርፈ ብዙ የኤች. አይ.ቪ ምላሽ ማስተባበር ዴስክ ኃላፊ አቶ ሀብታሙ ካሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ «ሶሻል ማርኬቱ» ላይ በተፈጠረ ጫና የኮንዶም እጥረት ተስተውሎ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት 52 ሚሊዮን ኮንዶም ሀገር ውስጥ ገብቶ የጥራት ፍተሻ ሂደት ላይ ነው፡፡ የጥራት ሙከራው እንደተጠናቀቀ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ወደ ሥርጭት ይገባል፡፡ ይህ ሲሆን ሶሻል ማርኬት ላይ አጋጥሞ የነበረው ጫና ይቀንሳል፡፡

ኃላፊው እንዳሉት፤ እንደ ሀገር ካለው የኮንዶም ስትራቴጂ ሦስት ዓይነት የኮንዶም ገበያዎች አሉ፡፡ አንደኛው ሶሻል ማርኬት የሚባለው ሲሆን፤ መንግሥት በተወሰነ መልኩ የሚደጎምና በሀገሪቱ ከፍተኛውን የገበያ ድርሻ የሚይዝ ነው፡፡ ይህንን ዲኬቲ በሽያጭ ያሰራጨዋል፡፡ ሁለተኛው በነፃ የሚታደል ሲሆን፤ በጤና ሚኒስቴር በኩል የሚገዛና ለቤተሰብ ምጣኔና ለኤች አይቪ መከላከያ የሚውል ነው፡፡

ይህም ለኤች አይቪ ኤድስ ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ ለሴተኛ አዳሪዎች፣ ለረጅም ርቀት አሽከርካሪዎች፣ የተለያየ የምርመራ ውጤት ላላቸው፤ ለአፍላ ወጣቶችና ሌሎች ትኩረት ለሚሹ የማኅበረሰብ ክፍሎች የሚታደል መሆኑን ጠቅሰው፤ ሦስተኛው አዲስ ፕሮግራም ሲሆን፤ ማንኛውም ነጋዴ ከውጭ አስመጥቶ እንደ ማንኛውም ዕቃ ያዋጣኛል ባለው መልክ ለገበያ የሚያቀርበው መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ማንኛውም የሕክምና መገልገያ መድኃኒት ሀገር ውስጥ ሳይገባና ከገባ በኋላ ብዙ የጥራት ማረጋገጫዎችን አልፎ ለተጠቃሚ እንደሚሰራጭ ኃላፊው ገልጸው፤ «እኛ ገዝተን የነበረው ኮንዶም ብዙ ሂደቶችን አልፎ ሀገር ውስጥ ሲገባ ጥራትን የሚቆጣጠረው ተቋም ጥራት ያረጋግጣል፡፡ ጥራቱን የማያሟላ ከሆነ ተመላሽ ይሆናል፡፡ ይህ ተፈጥሯዊ ሂደቱ ነው፡፡» ብለዋል፡፡

ከዚህ አኳያ አምና አንድ ዙር ተገዝቶ የመጣው ኮንዶም ጥራት ሳያሟላ መቅረቱን ገልጸው፤ በዚህ መሀል በነፃ በሚሰራጨው ኮንዶም ላይ ትልቅ ክፍተት ተፈጥሮ መቆየቱን ተናግረዋል፡፡

በነፃ የሚታደለው ኮንዶም እጥረት ባጋጠመን ወቅት ጫናው ሶሻል ማርኬቱ ላይ መሆኑን አውስተው፤ ሁሉም ቦታ እየተዳረሰ ያለው የሶሻል ማርኬቱ ኮንዶም በመሆኑ ፋርማሲ ላይ የዋጋ መጨመር እንደሚያስከትል ገልጸዋል፡፡ ሆኖም የዋጋ ጭማሪው በዚህ ችግር ብቻ የሚመጣ ሳይሆን ዓለም አቀፍ የዋጋ ጭማሪንም መሠረት እንደሚያደርግ ተናግረዋል፡፡

ችግሩን ለመፍታት ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑና ትኩረት ለሚሹ የማኅበረሰብ ክፍሎች በያሉበት በነፃ የሚታደለው 52 ሚሊዮን ኮንዶም የጥራት ፍተሻውን ሲጨርስ በቅርብ ጊዜ ውስጥ እንደሚሰራጭ ኃላፊው አስታውቀዋል፡፡



# የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች ማኅበር መመስረት ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ያስችላል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተለያየ ጊዜ ሀገራቸውን በልዩ ልዩ ኃላፊነቶች ሲያገለግሉ የነበሩ የቀድሞ አምባሳደሮች፣ ዲፕሎማቶችንና እያገለገሉ ያሉ የመሥሪያ ቤቱ ባለሙያዎችን ያካተተ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች ማኅበር ተመሰርቷል።

በማኅበሩ ምስረታ ወቅት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ የሀገራቸውን ብሔራዊ ጥቅምና ክብር እንዲጠበቅ ያደረጉ አንጋፋ ዲፕሎማቶችንና የአሁኑን ትውልድ ባለሙያዎች የሚያሰባስበው ማኅበር መመስረቱ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ገልጸዋል።

ማኅበሩ በውጭ ግንኙነት ሥራ ውስጥ በጥናት እና ምርምር፣ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በማሳየት እንዲሁም ወጣቶችን በማሰልጠን የእውቀት ሽግግር በማድረግ አስተዋጽኦ ያደርጋል ብለዋል።

በማኅበሩ ምስረታ የተገኙ አንጋፋ ዲፕሎማቶች እንዲህ ዓይነት የሙያ ማኅበር መመስረቱ የዲፕሎማሲ ሙያና ጥበብ እንዲጎለብት እና በባለሙያዎች መካከል ማኅበራዊ ትስስር እንዲጠናከር እንደሚያስችል ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች ማኅበር መመስረቱ በተደራጀ መልኩ ሙያዊ አስተዋጽኦ ለማድረግና የሀገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ እንደሚያስችልም ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ ማኅበሩን የሚመሩ አመራሮችን በመምረጥ ተጠናቋል።

ዜና



ወይዘሮ ዘቢደር ቦጋለ

## የፆታ ጥቃት በሴቶች ነፃነትና መብት ላይ ገደብ ይጥላል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት መሠረታዊ ነፃነቶችና መብቶች ላይ አግባብ ያልሆኑ ገደቦችን የሚጥል ድርጊት መሆኑን የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በዓለም ለ32ኛ እንዲሁም በኢትዮጵያ ለ18ኛ ጊዜ «መቼም፣ የትም በምንም ሁኔታ ፆታዊ ጥቃትን ዝም አንበል!!» በሚል መሪ ቃል ለሚከበረው የፀረ- ፆታዊ ጥቃት ቀን የተዘጋጀ ንቅናቄ ማስጀመሪያ ፕሮግራም ሰሞኑን ተከናውኗል፡፡

በመድረኩ መልዕክት ያስተላለፉት በሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሴቶችና ሕፃናት ዘርፍ የሚኒስትር ዴኤታ አማካሪ ወይዘሮ ዘቢደር ቦጋለ እንዳሉት፤ ፆታን መሠረት ያደረገ ጥቃት መሠረታዊ ነፃነቶችና መብቶች ላይ አግባብ ያልሆነ ገደቦችን የሚጥል ድርጊት ነው፡፡

እንደ ወይዘሮ ዘቢደር ገለጻ፤ የሴቶች ጥቃት በሰላምም ሆነ በጦርነት ወቅት በግልም ሆነ በማኅበራዊ ሕይወት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያሳድር ነው፡፡ በኢትዮጵያ ሕጎች የተረጋገጡ ነፃነቶችና መብቶች ላይ አግባብ ያልሆኑ ገደቦችን የሚጥል ጭምር ድርጊት ነው።

በሴቶችና በሕፃናት ላይ የሚፈጸም ማንኛውም ዓይነት አካላዊ፣ ወሲባዊም ሆነ ሥነልቦናዊ ጥቃት ኢኮኖሚያዊ ችግር የሚያስከትል የሰብአዊ መብት ጥሰት ስለመሆኑም ወይዘሮ ዘቢደር ጠቁመው፤ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚደርስ ጥቃት አካላዊ፣ አእምሯዊ ጤንነት እና ደህንነት በሁሉም የሕይወታቸው ደረጃ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል ብለዋል፡፡

የ16ቱ የፀረ-ፆታዊ ጥቃት ቀናት በዓለም አቀፍ ደረጃ ፆታን መሠረት ያደረገን ጥቃት ለማስቀረት የሚደረግ ዓለምአቀፍ ትግል አካል በመሆኑ ቀናቶቹ በዓለም አቀፍ ፀረ-ፆታዊ ጥቃት ቀን ተብለው እንዲታሰቡ ስለመደረጉም ወይዘሮ ዘቢደር ጠቅሰዋል፡፡

ይህም የተደረገው በሴቶች ላይ በኃይል የሚፈፀመውን ጥቃትና ሰብአዊ መብት ያላቸውን ቁርኝት ለማገናዘብ እና ጥቃቱ የሰብአዊ መብት ጥያቄ መሆኑን ለማሳየት ነው ብለዋል፡፡

በዚህም ወንዶች ነጭ ሪቫን በማድረግ ከኅዳር 16 ጀምሮ ለአስራ ስድስት ቀናት በሴቶች ላይ ማንኛውም ዓይነት ጥቃት ላለመፈፀም ቃል የሚገቡበት ሂደት ስለመኖሩም ተጠቅሷል፡፡

ዘኢኮኖሚስት ኢንተለጀንስ ዩኒት በሚባለው ተቋም የተደረገ ዓለምአቀፍ ጥናት እንዳመለከተው 38 በመቶ የሚሆኑ ሴቶች በቀጥታ ጥቃት ሲደርስባቸው 85 በመቶ ደግሞ በዲጂታል ቴክኖሎጂ አማካኝነት ጥቃት / online Violence/ እንደሚደርስባቸው ተመልክቷል።

በቴክኖሎጂው ዘርፍ በሚሠሩ ሴቶች ላይ የተደረገ ዓለም አቀፍ ጥናት እንዳመለከተው 44 በመቶ የሚሆኑ የሴቶች ማኅበራት መሥራቾች በ2020 በሥራ ቦታ ላይ ጥቃት አጋጥሟቸዋል፤ ከነዚህም 41 በመቶዎቹ ሴቶች ወሲባዊ ትንኮሳ ደርሶባቸዋል ይላል።

## «የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ወንድማማችነትን በማጠናከር ሀገራዊ አንድነትን የሚያጎለብት ነው»

- አቶ ኃይሉ አዱኛ
የኦሮሚያ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ

**ማርቆስ በላይ**



አዲስ አበባ፡- የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓል መከበሩ እንደሀገር በሕዝቦች መካከል ወንድማማችነትን በማጠናከር ሀገራዊ አንድነትን የሚያጎለብት ነው ሲሉ የኦሮሚያ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ኃይሉ አዱኛ ገለጹ፡፡

18ኛውን የብሔር ብሔረሰቦችን ቀን በዓልን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀው 35ኛው ጉሚ በለል የውይይት መድረክ «ብዝሃነትና እኩልነት ለሀገራዊ አንድነት» በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት ተካሂዷል።

በመድረኩ የተገኙት አቶ ኃይሉ አዱኛ እንደተናገሩት፤ የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓል በሕዝቦች መካከል ወንድማማችነትን በማጠናከር ሀገራዊ አንድነትን የሚያጎለብት በመሆኑ ያጋጠሙ የተለያዩ ችግሮችን በጋራ ለመቅረፍ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

የፌዴራሊዝም ሥርዓት በኢትዮጵያ ለሚገኙ ሕዝቦች ባህል፣ ቋንቋና እምነት ዕውቅና ሰጥቷል ያሉት አቶ ኃይሉ፤ በተለይም ራስን በራስ ለማስተዳደርና በጋራ ሀገርን ለመምራት ያስቻለ ሥርዓት መሆኑን ጠቁመዋል።

ሕገ-መንግሥቱ የጸደቀበት ኅዳር 29 ቀን የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በመሆን የሚከበር በመሆኑ በሕዝቦች መካከል ለመቀራረብና ለመተዋወቅ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ብለዋል፡፡

የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ባህል፣ ቋንቋና እምነት ማሳደግ እንዲችሉ ማድረጉን ጠቅሰው፤ ሕገ-መንግሥቱ ዜጎች ልዩነታቸውን አክብረው በጋራ እንዲኖሩ የሚያስችል ሰነድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

እንደሀገር በሕዝቦች መካከል የመረዳዳትና የመቀራረብ ባህልን ማሳደግ እንደሚገባ ጠቁመው፤ ልዩነትን በማጥበብ በሀገራዊ ግንባታ ጉዳዮች ላይ በጋራ መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የሕዝቦችን የጋራ አቅም፣ ሀብትና ዕውቀት በመጠቀም አቃፊ ትርክትና አሳታፊ የሀገር ግንባታ ማከናወን እንደሚያስፈልግ ተናግረው፤ በአብሮነት ልማቱን ለማፋጠን የምሁራን ድርሻ ማጉላት ይገባል ሲሉ አመልክተዋል፡፡

የበዓሉ መከበር የሕዝቦችን ባህል ቋንቋና ማንነትን ለመጠበቅ እንደሚያስችል የገለጹት አቶ ኃይሉ፤ በሀገሪቱ ያጋጠሙ ችግሮችን በጋራ በመቅረፍ የትውልዱን መጻኢ ጊዜ ብሩህ ለማድረግ መሥራት ይገባል ብለዋል።

የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓል መከበር ወንድማማችነትን እንዲጠናከር በማድረግ ሀገራዊ አንድነት እንዲጎለብት ያስችላል ያሉት ኃላፊው፤ በዓሉ ወንድማማችነትንና ሀገራዊ አንድነት ለማጠናከር የሚያስችል መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በውይይት መድረኩ የኦሮሚያ ክልል ምክትል አፈ ጉባኤ ኤሊያስ ኡመታን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና የፌዴራሊዝም ምሁራን እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

## የጥርስ ምርመራ ማድረግ ባህል ሊሆን ይገባል

**ሄለን ወንድምነው**



ስመኝ አሰፋ (ዶ/ር)

አዲስ አበባ፡- ዜጎች ከመታመማቸው አስቀድሞ የጥርስ ምርመራ ማድረግን ባህል ሊያደርጉ ይገባል ሲሉ በአለርት ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የጥርስ ሕክምና ማዕከል አስተባባሪ ስመኝ አሰፋ (ዶ/ር) ገለጹ። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከአለርት ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የጥርስ ሕክምና ማዕከል ጋር በመተባበር ለድርጅቱ ሠራተኞች ነፃ የጥርስና የአፍ ምርመራ አገልግሎት እንዲያገኙ አድርጓል።

በሆስፒታሉ የጥርስ ሕክምና ማዕከል አስተባባሪ ስመኝ አሰፋ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደተናገሩት፤ የጥርስን ጤንነት ለመጠበቅ በትንሹ በዓመት ሁለት ጊዜ ሐኪም ጋር መታየት ይገባል፡፡

በርካታ ሰዎች ጥርሳቸው የመጨረሻው የጉዳት ደረጃ ላይ ሲደርስ ወደ ሕክምና ተቋም ይመጣሉ ያሉት ዶክተር ስመኝ፤ ይህም ከጥርስ ጉዳት አልፎ ለተጓዳኝ የጤና ችግሮች፣ ለአፍ ጠረን ችግርና ለሥነ-ልቦና ጉዳት እንደሚያጋልጣቸው አስረድተዋል።

በአፍ ውስጥ የምግብ ትርፍራፊ ከዋለና ከአደረ ለጥርስ ህመም እንደሚያጋለጥ ገልጸው፤ በዓመት ሁለት ጊዜ ሐኪም ጋር በመታየት፣ ጠዋትና ማታ ጥርስን በማጽዳትና ቫይታሚን ሲ ያላቸውን ምግቦች በመመገብ የጥርስን ጤንነት መጠበቅ እንደሚቻል አመልክተዋል።

ዜጎች ከመታመማቸው በፊት የጤና ክትትል ማድረግን ባህል ማድረግ እንዳለባቸው አንስተው፤ ለኢፕድ ሠራተኞች ነፃ ቅድመ ምርመራ አገልግሎት የተሰጠው ሌሎች ዜጎች ከመታመማቸው በፊት ምርመራ ማድረግን ባህል እንዲያደርጉ ለማስገንዘብ ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የደንበኞች አገልግሎት ባለሙያ ትንሳኤ ደገፉ በበኩሉ፤ በተደረገው ነፃ የጥርስ ምርመራና የግንዛቤ ማስጨበጫ አገልግሎት ከመታመማችን በፊት ወደጤና ተቋም ሂደን ክትትል ማድረግ ያለውን ጠቀሜታ ተረድተናል ብሏል።

በቀጣይም ሳልታመም ወደጤና ተቋም እየሄድኩ ክትትል ከማደረግ ባለፈ በአካባቢዬ የሚገኙ ሰዎች ከመታመማቸው በፊት የጤና ክትትል እንዲያደርጉ ግንዛቤ እፈጥራለሁ ሲል ተናግሯል።

በኢፕድ የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ክፍል ኃላፊ ወይዘሮ ብርሃኔ ደመቀ በበኩላቸው፤ የተቋሙ ሠራተኞች የጥርሳቸውን ጤና ለመጠበቅ ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት ከአለርት ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የጥርስ ሕክምና ማዕከል ጋር በመተባበር ነፃ የጥርስና የአፍ ምርመራና ሕክምና አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

የአለርት ሆስፒታል ላደረገው ትብብር አመስግነው፤ በቀጣይም ለተቋሙ ሠራተኞች በተለያዩ የሕክምና ዘርፎች የሚሰጠው ግንዛቤ ማስጨበጫና የቅድመ ምርመራና ሕክምና አገልግሎት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አመላክተዋል፡፡

ዜና

# መንግሥት ለሰላማዊ ውይይት ሁልጊዜም በሩ ክፍት ነው

## - በሸኔ ላይ የተጠናከረ ርምጃ እየተወሰደ ነው

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሸኔ ከሚፈጽመው የሽብር ተግባር ተቆጥቦ ወደ ሰላማዊ መንገድ የሚመጣ ከሆነ መንግሥት ሁልጊዜም ለሰላም በሩ ክፍት መሆኑን የኦሮሚያ ክልል ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ፡፡ ቡድኑ የቀረበለትን የሰላም አማራጭ ወደ ጎን ብሎ በሽብር ተግባሩ በመቀጠሉ መንግሥት የሕግ የበላይነትን የማስከበር ኃላፊት ስላለበት በቡድኑ ላይ ርምጃ እየወሰደ መሆኑንም ገለጸ፡፡

የቢሮ ኃላፊው አቶ ኃይሉ አዱኛ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኦሮሚያ ክልል የሚንቀሳቀሰው ሸኔ ሽብር ቡድን በተከፈተው የፖለቲካ ምህዳር ባለመጠቀም ኃይልን መሠረት ያደረገ የትጥቅ ትግል አንስቶ ባለፉት ዓመታት በሰው ሕይወትና በብረት ላይ የተለያዩ ጉዳቶችን አድርሷል፡፡ መንግሥትም ቡድኑ ወደ ሰላማዊ እንቅስቃሴ እንዲመጣ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡

ሆኖም ቡድኑ የሰላም አማራጮችን ወደ ጎን ትቶ በሽብር ተግባሩ በመቀጠሉ ጠንካራ ርምጃ እየተወሰደበት ይገኛል ብለዋል፡፡

ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት ብዙ ጥረቶች መደረጋቸውን ያስታወሱት አቶ ኃይሉ፤ በፖለቲካ ምህዳሩ ብልሽት ምክንያት ከሀገር ተሰደው የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ሀገር እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡

ሸኔም የተከፈተውን ሰላማዊ የትግል ሜዳ ከመጠቀም ዓላማዬን በትጥቅ ትግል አሳካለሁ በማለት በሰላማዊ ዜጎች ላይ የተለያዩ ጉዳቶችን ሲያደርስ መቆየቱን አንስተው፤ መንግሥት በኦሮሞ ባህል መሠረት ችግሮች እንዲፈቱ በሀገር ሽማግሌዎች፣ በአባ ገዳዎችና በሀደ ስንቄዎች አማካኝነት እርቅ ለመፍጠር ጥረት አድርጓል። ሆኖም ቡድኑ በአባገዳዎች የቀረበለትን ሰላም ጥሪ ወደ ጎን ትቶ ሦስተኛ ወገን በተገኘበት ካልሆነ አልደራደርም በማለቱ መንግሥት ለሰላም ቅድሚያ በመስጠት በሁለት ዙር ንግግር ተደርጓል፡፡

ሽብር ቡድኑ አሁንም ወደ ሰላማዊ መንገድ መመለስ ፍላጎት ስለሌለው ንግግሩ ፍሬ እንዳያፈራ አድርጓል፤ በሽብር ተግባሩም ቀጥሏል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

መንግሥት የሕግ የበላይነትን ማስፈን የዜጎችን ደህንነት ማረጋገጥ ኃላፊነት ስላለበት የክልሉና የፌዴራል ፀጥታ ተቋማት በቡድኑ ላይ ርምጃ እየወሰዱ መሆኑን ገልጸው፤ በዚህም ቡድኑ ተቆጣጥሯቸው የነበሩ ቦታዎችን የማስለቀቅ ሥራ እየተሠራ ነው፡፡

በመሬት ላይ እየወሰደ ባለው ርምጃ የተደናገጠው ሽብር ቡድኑ በሰላማዊ ዜጎች ላይ አሰቃቂ ርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል ያሉት ኃላፊው፤ በዚህም በአርሲ ዞን ሼካ ወረዳ በወሰደው ጭካኔ የተሞላበት ርምጃ ብዙ ዜጎች ገድሏል፡፡ ቤት ንብረታቸውንም አቃጥሏል፡፡

እንደ ቢሮ ኃላፊው ገለጻ፤ ቡድኑ አሸባሪ ካስባሉት ጉዳዮች አንዱ የራሱን የመደራደር አቅም ከፍ ለማድረግ ሰላማዊ ዜጎቸ ላይ ያነጣጠረ ርምጃ መውሰዱ ነው፡፡

በተጨማሪም ዜጎች ሠርተውና አምርተው ኑሯቸውን በአግባቡ እንዳይመሩ የእርሻ ግብዓቶችን እንዳያገኙ፣ እንዳይጠቀሙና የእርሻ ሥራቸውን በወቅቱ እንዳያከናውኑ እንቅፋት እንደሚፈጥር ጠቁመው፤ የተመረተው ምርት በአግባቡ እንዳይሰበሰብ ለማድረግም ጥረት እያደረገ ነው ብለዋል፡፡

በመሆኑም መንግሥት የዜጎችን ደህንነትና ሰላማዊ እንቅስቃሴ የማረጋገጥ ኃላፊነት ስላለበት በቡድኑ ላይ ርምጃ እየወሰደ ይገኛል ነው ያሉት፡፡

በተሠራው ሥራም ባለፈው ሳምንት ከምሥራቅና ምዕራብ ወለጋ ቡኖ በደሌን ለማጥቃትና ለማውደም የተንቀሳቀሰውን የሽብር ቡድን በተወሰደበት ርምጃ ሙትና ቁስለኛ ሆኗል ያሉት አቶ ኃይሉ፤ ሕዝቡም መረጃ በመስጠትና በተለያዩ መንገዶች ከመንግሥት ጎን መሆኑን አረጋግጧል፡፡

ሕዝቡ ቡድኑ ወደ ሰላማዊ መንገድ ይመጣል በሚል ተስፋ አድርጎ ነበር ያሉት ቢሮ ኃፊው፤ መንግሥት ለሰላም ካለው ቁርጠኝነት ወደ ስምምነት ለመምጣት ብዙ ርቀት ሄዶ ጥረት አድርጓል፡፡ ሽብር ቡድኑ ለድርድር ይዞ የቀረበው የጋላቢዎቹን አጀንዳ ነው፡፡ ይህ የሀገርን ሉዓላዊነት አደጋ ላይ የሚጥል ስለሆነ ተቀባይነት የለውም ብለዋል፡፡

በዚህም ድርድሩ የሚፈለገውን ውጤት ስላላስገኘ የዜጎችን ደህንነት ለማስጠበቅና የሕግ የበላይትን ለማረጋገጥ አስፈላጊው ሁሉ ዋጋ እንደሚከፍል ጠቅሰው፤ ቡድኑ ተገዶ ወደ ሰላም እንዲመጣ የሚያደርግ ጠንካራ ሥራ ይሠራል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በተሳሳተ መረጃ ሽብር ቡድኑን የተቀላቀሉ ወጣቶች ወደ ሰላማዊ ሁኔታ እየተመለሱ መሆኑን አመልክተው፤ በቀጣይነትም ሕዝቡን በማስተባበር ቡድኑ የዜጎች ስጋት ከማይሆንበት ደረጃ ለማድረስ የሚያስችል ርምጃ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡

መንግሥት ለሰላም የዘረጋው እጁ ዛሬም አልታጠፈም ያሉት አቶ ኃይሉ፤ የሽብር ቡድኑ ከሽብር ተግባሩ ተቆጥቦ ወደ ሰላማዊ ውይይትና ንግግር ከተመለሰ መንግሥት ለሰላም ሁልጊዜም በሩ ክፍት ነው ብለዋል፡፡

# ኢትዮጵያ በአራት ወራት...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በሚኒስቴሩ የኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ በላይነሽ ረጋሳ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016 በጀት ዓመት አራት ወራት አጠቃላይ ለውጭ ገበያ ከቀረቡ ምርቶች ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል፡፡

ሚኒስቴሩ ወደ ውጭ ገበያ ከላካቸው የጥራጥሬ፣ የቅባት እህሎች፣ የብርዕና አገዳ ሰብሎች፣ የጫት ምርት፤ የቁም እንስሳት፣ ደንና የደን ውጤቶች ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱን ተናግረዋል፡፡

የጥራጥሬና የቅባት እህሎች ለአፈጻጸሙ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው የገለጹት የኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚዋ፤ የተገኘውን ውጤት በሌሎች ዘርፎች ላይ ለማሳካት እየተሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

በጫት ምርት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመቅረፍ አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ለማድረግ አዳዲስ አሠራሮች ተግባራዊ እየተደረጉ መሆናቸውን ጠቁመው፤ በተለይም ጫት ላኪዎች በሕጋዊ መንገድ ወደ ውጭ እንዲልኩ በማድረግ እንደ ሀገር የሚታጣውን ገቢ ማዳን መቻሉን አስረድተዋል፡፡

በግብይት ሥርዓቱ የኦንላይን አገልግሎት ተግባራዊ በመደረግ ላይ መሆኑን ገልጸው፤ በዚህም የውጪ ኮንትራት ምዝገባ አፈጻጸምና የኤክስፖርት መላኪያ ፍቃድ አሠጣጥን ጊዜ ቆጣቢና ቀላል ማድረግ መቻሉን ተናግረዋል።

ምርት ላኪ ድርጅቶች በወቅቱ ኮንትራት ገብተው ለዓለም አቀፍ ገበያ ማቅረብ እንዲችሉ ክትትልና ድጋፍ በመደረግ ላይ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ ሕገ-ወጥ እንቅስቃሴና የኮንትሮባንድ ንግድ ላይ የተጠናከረ ክትትል መከናወኑን አመልክተዋል።



በዘርፉ የኮንትሮባንድ ንግድ መስፋፋት፣ የቅባት እህሎች የወጪ ምርት አቅርቦት እጥረት መኖራቸውን ጠቅሰው፤ በኤክስፖርት ምርቶች ላይ አላስፈላጊ ታክስ መኖርና የክፍያ ኬላዎች መበራከት የወጪ ንግድ ገበያው እንዳያድግ ምክንያት መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

በዘርፉ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታትና ገቢን ለማሳደግ በምርቶች ላይ የክትትልና ድጋፍ ሥራዎች መሠራታቸውን የገለጹት በላይነሽ፤ አገልግሎት አሠጣጡን ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ ለማድረግ የሪፎርም ሥራዎች መሠራታቸውን አስረድተዋል።

በቀጣይ የኮንትሮባንድ ንግድ ቁጥጥርን ማጠናከር፣ የድንበር ላይ ንግድን ወደ ሕጋዊ መንገድ የማስተሳሰር ሥራዎች እንደሚሠሩ በመግለጽ፤ የገበያ መዳረሻዎችን ማስፋትና ነባር የገበያ መዳረሻን ማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም የበይነ መረብ የወጪ ንግድ ግብይትን ማዘመን፣ የወጪ ንግድ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓትን ማሻሻል እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ በተለይም ዓለም አቀፍ፣ ቀጣናዊና የሁለትዮሽ የንግድ ትስስር ተግባራትን ማጠናከር ትኩረት እንደሚሰጣቸው አመልክተዋል፡፡

# «አረንጓዴ ዐሻራ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

የሥራ ዕድል የፈጠረ መሆኑን አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብርን በማጠናከር ለጎረቤት ሀገራት ጭምር የተለያዩ ችግኞችን በማከፋፈል መሥራቷን ጠቁመው፤ መርሐ-ግብሩ በአፍሪካ ለሚገኙ ሌሎች የልማት የትብብር ሥራዎችም መጠናከር ግብዓት እንደሚሆን አመላክተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከኮፕ28 ጉባኤ ጎን ለጎን ከተለያዩ ሀገራት መሪዎች ጋር በሁለትዮሽ ትብብር ጉዳዮች ላይ ገንቢ ውይይት አድርገዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከቤልጂየም ጠቅላይ ሚኒስትር አሌክሳንደር ዴ ክሮ ጋር በሀገራቱ ሁለትዮሽ ትብብር ጉዳዮች ዙሪያ ላይ ተወያይተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከኮፕ28 ጉባኤ አስቀድሞ ከቤልጂየም ጠቅላይ ሚኒስትር አሌክሳንደር ዴ ክሮ ጋር በኢትዮጵያ አረንጓዴ ዐሻራ መካነ ርዕይ (ፓቪሊዮን) ተገናኝተዋል፡፡

ሁለቱ መሪዎች በወቅታዊ የሀገር ውስጥ እና ሁለትዮሽ ትብብር ጉዳዮች ላይ ውይይት ማድረጋቸውን ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

በተያያዘ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከሕንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ ጋር ተወያይተዋል፡፡

መሪዎቹ ከኮፕ28 ጉባዔ ጎን ለጎን ባደረጉት ውይይት በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን ታሪካዊ ወዳጅነት ይበልጥ ለማጠናከር ቁርጠኛ መሆናቸውን አረጋግጠዋል።

በተመሳሳይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በኮፕ28 ጉባኤ ጎን የኩባውን ፕሬዚዳንት ሚግዌል ዲያዝ-ካናልን በኢትዮጵያ አረንጓዴ ዐሻራ መካነ ርዕይ (ፓቪሊዮን) ተቀብለው አነጋግረዋል፡፡

ሁለቱ መሪዎች የዓለም የአየር ጠባይ ለውጥ ኃላፊነትን፣ የሁለትዮሽ ትብብርን እና የብሔራዊ ልማት ጉዳዮችን የተመለከተ ውይይት አድርገዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከእንግሊዝ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ቶኒ ብሌር ጋር ተወያይተዋል።

በ28ኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ላይ በመሳተፍ ላይ የሚገኙ የዓለም ሀገራት አዲስ የአየር ንብረት አደጋ ፈንድ ስምምነት አጽድቀዋል፡፡

# ኢትዮጵያና ቻይና በግብርናው ዘርፍ በትብብር ለመሥራት ተስማሙ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡-ኢትዮጵያና ቻይና የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ በትብብር እንደሚሠሩ የሁለቱ ሀገራት ከፍተኛ አመራሮች ገለጹ፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ ወይዘሮ ሎሚ በዶ ከቻይና ብሔራዊ ኮንግረስ አባልና ልዑክ ቡድናቸው ጋር የሁለትዮሽ ውይይት በትናንትናው ዕለት አካሂደዋል፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባዔ ወይዘሮ ሎሚ በዶ የቻይናን ልዑክ በምክር ቤቱ ተቀብለው ባወያዩበት ወቅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ የምትሠራቸው ሁለተናዊ ሥራዎች ተጨባጭ ውጤት እያስገኙ ናቸው፡፡ ዘርፉን ይበልጥ ለማዘመን፣ እንዲሁም የግብርና ውጤቶችን የበለጠ በብዛትና በጥራት ለማምረት የቻይና ድጋፍ አስፈላጊ ነው፡፡

ኢትዮጵያ እና ቻይና የቆየ ታሪካዊ ግንኙነት እንዳላቸው የገለጹት ምክትል አፈ- ጉባዔዋ፤ ቻይና ግብርናውን በማዘመን የተሻለ ደረጃ ላይ እንደምትገኝ ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵያ ግብርና ላይ እየሠራች ያለችውን ሥራ ለማሳደግም ቻይና አሁን የደረሰችበትን የግብርና እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግር ልምዷን ለኢትዮጵያ እንድታካፍል ጠይቀዋል፡፡

ኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ የምታመርታቸውን ምርቶች በብዛትና በጥራት ወደ ውጭ ገበያ ማቅረብ እንደምትፈልግም ተናግረዋል፡፡

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ሰለሞን ላሌ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ በግብርናው ዘርፍ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳድር በአፈርና ውሃ ጥበቃ ትልቅ ሥራ እንዳከናወነች ገልጸዋል፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት በተደረገው የአረንጓዴ ልማት ዘመቻ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ችግኞች ተተክለው አመርቂ ውጤት እየታየ ነው ያሉት አቶ ሰለሞን፤ በዚህም የተነሳ የሀገሪቱ የሥነ-ምህዳር ሁኔታ የተሻለና ለውጥ እያሳየ ነው ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ስንዴን በመስኖ በማልማት ከባለፉት ሦስት ዓመታት ጀምሮ የተሻለ ምርት በማምረት ከውጭ የሚገባውን ስንዴ በሀገር ውስጥ የመተካት ታሪካዊ ሥራ ያከናወነች መሆኑን አቶ ሰለሞን ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ የግብርናውን ዘርፍ ለማዘመን በምታደርገው ጥረት እና ከለውጡ ወዲህ ማስመዝገብ የጀመረችውን የምርታማነት ስኬት የበለጠ አጠናክራ እንድትቀጥል የቻይናን ድጋፍ የምትሻ መሆኑን አቶ ሰለሞን ላሌ አሳስበዋል፡፡

የቻይናው ብሔራዊ ኮንግረስ አባል እና የግብርና እና ገጠር ጉዳዮች ኮሚቴ ሊቀመንበር ሚስተር ዱ ጂአሃኦ በበኩላቸው፤ ቻይና ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ግብርናውን በማዘመን እና የገጠር ግብርና ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመሥራት ተጨባጭ ውጤት እያስመዘገበች መሆኑን አንስተዋል፡፡

ኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ ተጨባጭ ውጤት እያስመዘገበች መሆኑን እንረዳለን ያሉት ሊቀመንበሩ፤ ግብርናውን ለማዘመን እና ምርታማነትን ለመጨመር ቻይና የበኩሏን ድጋፍ የምታደርግ መሆኑን አስታውቀዋል።

የቻይና ፓርላማ የግብርና ገጠር ጉዳዮች ምክትል ሰብሳቢ ዴንግ ኤክሱሲን በበኩላቸው፤ ቻይና በግብርና የካበተ ልምድ ያላት መሆኑን አንስተዋል፡፡

የግብርናው ዘርፍ ሀገሪቷ የተሻለ የኢኮኖሚ ጥቅም የምታገኝበት አንዱ ዘርፍ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ የጀመረችውን ስኬት አጠናክራ መቀጠል እንድትችል ቻይና በዘርፉ ያላትን ልምድ ለማካፈል እና ለመደገፍ ሙሉ ፈቃደኛ እንደሆነችም ምክትል ሰብሳቢው ዴንግ ተናግረዋል፡፡

# ኤች አይ ቪን...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

እንደሚጠናከርና ኅብረተሰቡ የሚያደርገው የመከላከል ሥራ ሊቀጥል እንደሚገባ ተናግረዋል።

በመድረኩ በጤና ዘርፉ የሚሠሩ የዓለም አቀፍ ተቋማት ተወካዮች፣ አምባሳደሮች፣ የተለያዩ የክልልና የከተማ አስተዳደር ቢሮ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሔት

የውስጥ ገጾች




ገጽ 16

‹‹እንደ ሀገር አብረን ለመዝለቅ ሀገራዊ ምክክሩ ከፍተኛ ፋይዳ አለው››

- ወይዘሮ አዜብ አልፍሬድ ሻፊ

ገጽ 6





በማዕድን ልማት እየተጋ ያለው ዋዳፍ ኢትዮጵያ

ገጽ 13

ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ
አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

## ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

አዲስ አበባ
The Vibrant Hub of Africa

አፍሪቃዊቷ መልጎቅ

# የአስተሳሰብ ለውጥን የሚሻው፤የሥራ ባህላችን

ዳንኤል ዘነበ

የሰው ልጆች የአኗኗር ዘዬ በየጊዜው እየተቀየረ ነው። በሁሉም ዘርፍ ዕድገት ለማስመዝገብ ከተፈለገ ብዙ መድከምና መሥራት የግድ እየሆነ ነው፡፡ ለመኖር መልፋት፣ በተለይ በአገልግሎትና ንግድ ዘርፍ ያለው ውድድር ሀገራዊ ብቻ አይደለም፡፡ ውድድሩ ዓለም አቀፋዊ ሆኗል፡፡ ተወዳድሮ ለማሸነፍ ደግሞ ብዙ ሊለወጡ የሚገቡ የአሠራር ዘዬዎች አሉ፡፡ ከብዙዎቹ አንዱ የሥራ ባህል ነው፡፡ ዕድገት ከታሰበ የሥራ ባህል መቀየር ይኖርበታል፡፡ በመልካም የሥራ ባህልና እሴቶች የታነፀ ማኅበረሰብ የአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እድገት ለማምጣት ወሳኝ ነው። ያደጉት ሀገሮች ልምድም ይህንን ይነግረናል፡ ፡ በዚህ ረገድ የሀገራችንን የሥራ ባህል በጥልቀት እንቃኝ ካልን፤ ጠንካራ የሥራ ባህል ሲታሰብ በብዙዎች አዕምሮ ቀድሞ የሚከሰት አንድ ማኅበረሰብ አለ፤ የአውራአምባ ማኅበረሰብ። ማኅበረሰቡ የተመሠረተው በ1964 ዓ.ም. በዙምራ ኑሩ (ክቡር ዶክተር) ነው። አውራአምባዎች ከሌላው የኢትዮጵያም ሆነ የክልሉ ነዋሪዎች በተለየው የአኗኗር ዘይቤአቸው ይታወቃሉ።

ማኅበረሰቡ ለየት ባለ መልኩ የፆታ እኩልነትን በተግባር ያሳየ፣ ሥራን «የማኅበረሰቡ እምነት» ያደረገም ነው። ማኅበረሰቡ ልማዳዊና ባህላዊ ክንዋኔዎችን ለሀገር በሚጠቅም አግባብ በማሻሻልና አዳዲስ እሴቶችን በማስተዋወቅ ልምድ የሚቀመርበት ተቋም ሆኖ እያገለገለ ይገኛል። በተለይ የሥራ ፍቅሩ፣ታታሪነቱ፣ የጊዜ አጠቃቀም፣ በወንዶችና በሴቶች መካከል ድንበር የሌለው የሥራ መስተጋብር የአውራአምባ ማኅበረሰብ እንቁ እሴቶቹ ናቸው። በሥራ ባህሉ ባሳየው ተምሳሌታዊነት የበርካታ ግለሰቦችን፣ ቡድኖችን፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ቀልብ በመሳብ የቱሪዝም መስህብ ሆኖ እየተጎበኘ ይገኛል። ጠንካራ የሥራ ባህልና ከአድሎ የፀዳ አሠራርን በመተግበር የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት



«የሥራ ባህልና የግል ኃላፊነት» በሚል ርዕስ 12ኛው ዙር የሃሳብ መዋጮ ኅዳር 11 ቀን 2016 ዓ.ም በስካይ ላይት ሆቴል ተካሂዷል

ለቻለው የአውራአምባ ማኅበረሰብ ውጤታማነት ትልቁ ሀብት የአስተሳሰብ ሀብት ነው። በመሆኑም ጠንካራ የሥራ ባህል እንዲፈጠር እንደ ሀገር የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል። በተለይ በአመለካከት ላይ ከተሠራ የሥራ ባህሉ የዳበረና አምራች ዜጋን መፍጠር እንደሚቻል የአውራአምባ ማኅበረሰብ ማሳያ ይሆናል። በመላ ሀገሪቱ ሊለመድ የሚገባው ይህ የሥራ ማክበር ባህል በሁሉም ዘንድ እንዲሰርጽ በማድረግ ረገድ የመንግሥት ተቋማት ኃላፊነት አለባቸው።

በዚህም የአዲስ አበባ ባህል ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የባህል ዘርፍ ማኅበራዊ ዕድገትን ወደ ኋላ የሚያስቀሩ አመለካከቶች፣ እምነቶች፣ ልማዳዊ ድርጊትና አሠራሮችን በጠቃሚ የባህል እሴቶች አሠራር ለመለወጥ የሚያስችሉ የስርፀት ሥራዎችን ያከናውናል። የማኅበረሰቡን የግንዛቤ አድማስ ለማሳደግ በተለያዩ መንገዶች የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በየጊዜው የሚያዘጋጀው ቢሮው፤ በዚሁ መሠረት«የሥራ ባህልና የግል ኃላፊነት» በሚል ርዕስ 12ኛው ዙር የሃሳብ መዋጮ ኅዳር 11 ቀን 2016 ዓ.ም በስካይ ላይት ሆቴል አካሂዷል። ርዕሰ ጉዳዩን መነሻ በማድረግ ከባህል እይታ አንፃር፣ ከአስተዳደር እይታ አንፃር፣ ከፍልስፍና አንፃር እና ከማኅበረሰብ ጥናትና ከማኅበረሰብ ሥራ እይታ አንፃር እንዴት ይታያል በሚል አንኳር ነጥቦች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነድ በምሁራን ቀርቧል።

በመድረኩ የሥራ ባህላችን ከባህል አንፃር መነሻ ጽሑፋቸውን ያቀረቡት ዶክተር ፍሬሕይወት ባዩ እንደተናገሩት፣ የሰው ልጅ ከሚገለጽባቸው ነገሮች አንዱ ሥራ ነው። በመሆኑም ለሥራ የሚገባውን ክብርና ፍቅር ልንሰጥ ይገባል። ሥራ ለስኬት የማይበቃው ትልቅ ዋጋ አለመስጠት መሆኑን ገልጸው፤ ለሥራ ተገቢውን ዋጋና መስዋዕትነት በመስጠትና የጊዜ አጠቃቀማችንን በማኅልበት የሥራ ባህላችንን ማዳበር ይገባልም ብለዋል።

ዶክተር ፍሬሕይወት፤ የሥራ ባህል የሚነሳው ከቤተሰብ ወደ አካባቢው ፤ ብሎም ሀገሩን የሚጠቅም ዜጋ ይኖራል። አንድ ሰው ራሱን፣ ቤተሰቡን፣ አካባቢውን ብሎም ሀገሩን ለመጠበቅና ለማስተዳደር የግድ ሥራ መሥራት እንዳለበት አብራርተዋል። በማኅበረሰባችን የማይሠራ ሰው የሚነቀፈውን ያህል ሲሠራ ደግሞ የማበረታታት፣ የመሸለም ብሎም ሥራውን ከመቃብር በላይ እንዲውል የማድረግ ባህልም አለው ሲሉም አስረድተዋል።

በመድረኩ የሥራ ባህልና የግል ኃላፊነት ከአስተዳደር አንፃር በሚል መነሻ ሃሳባቸውን ያካፈሉት ረዳት ፕሮፌሰር ጌትነት ተሾመ እንደገለጹት፤ የሥራ ባህላችን እየተበላሸ የመጣው በአቋራጭ የሚከብሩትንና ሥራ የማይሠራን አካል አልፎ አልፎ የማበረታታት ሁኔታ ይስተዋላል። አለፍ ሲልም የአገልጋይነት መንፈስ እየጠፋ መጥቷል። ይህን ጎጂ ባህል ለማጥፋት ደግሞ ባለድርሻ አካላት፣ የሃይማኖት ተቋማትና ማኅበረሰቡ በመረባረብ ችግሩን መቅረፍ እንደሚገባ አሳስበዋል ።

የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ኂሩት ካሳው ባስተላለፉት መልዕክት ፤ ለሥራ ባህል መነሻ ትልቁ ቦታ ቤተሰብ ነው፡፡ ከቤተሰብ ወጥቶ ነው ለማኅበረሰብና ለሀገር የሚተርፍ ሥራ የሚሠራው፤ የሥራ ባህል ከሌለን አሉ ብለን የምንኮራባቸው ነገሮች ከመኖር ወደ አለመኖር ሊቀየሩ የሚችልበት እድል ሰፊ ነው ብለዋል። የሃይማኖት ተቋማት ከሕፃናት ጀምሮ አስተሳሰብን መቅረፅ ላይ ያላሰለሰ ጥረት ሊያደርጉና ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ የቢሮ ኃላፊዋ አሳስበዋል።

የሀገራችንን የሥራ ባህል በጥልቀት እንቃኝ ካልን ኋላቀር ከመሆኑ ባሻገር ጠንካራ የሥራ ባህል የሌለን ስለመሆኑ በድፍረት መናገር ይቻላል፡፡ ስለዚህ እንደ ሀገር ጠንካራ የሥራ ባህል እንዲፈጠር እንደ ሀገር የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል። በተለይ አመለካከት ላይ ከተሠራ የሥራ ባህሉ የዳበረና አምራች ዜጋን መፍጠር እንደሚቻል የአውራአምባ ማኅበረሰብ ማሳያ ይሆናል።

በዚህም በሀገራችን ከሥራ ባህል ጋር ተያይዞ የሚታዩ የአመለካከት ችግሮችን ቀስ በቀስ እንዲቀየር በማድረጉ ረገድ በተለይ ከመንግሥት አካል ብዙ ይጠበቃል። በተጨማሪም ከሚመለከታቸው አካላት በሙሉ ማለትም፤ የእምነት ተቋማት፤ ጋዜጠኞችና ተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች፤ የከፍተኛ ትምህርት ምሁራን እና ፖለቲከኞች እንዲሁም በሥራ ፈጠራ የተሳካላቸውና ታዋቂ ግለሰቦች የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይገባል።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹እንደ ሀገር አብረን ለመዝለቅ ሀገራዊ ምክክሩ ከፍተኛ ፋይዳ አለው››

- ወይዘሮ አዜብ አልፍሬድ ሻፊ

ምሕረት ሞገስ

እዚሁ አዲስ አበባ ተወልደው ያደጉት የዛሬዋ የዘመን እንግዳችን ወይዘሮ አዜብ አልፍሬድ ሻፊ ይባላሉ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በሊሴ ገብረማርያም የተማሩ ሲሆን፤ በመቀጠል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እስከ 10ኛ ክፍል ድረስ ናዝሬት የልጃገረዶች ትምህርት ቤት ተከታትለዋል። የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በምድረ አሜሪካ ውድሮ ዊልሰን ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተምረዋል።

በአሜሪካ ምርጥ የተሰኘ ሰውን እነኩዋሜ ኑኩሩማ የተማሩበትን የጥቁሮች መማሪያ ሃዋርድ ዩኒቨርሲቲን መርጠው፤ በፖለቲካል ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ተምረዋል። ቀጥለው ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በቴክኖሎጂ ማኔጅመንት በዛው በአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ሜሪላንድ ተከታትለው አጠናቀዋል። ለ38 ዓመታት በአሜሪካን የኖሩ ሲሆን፤ አሜሪካን እንደገቡ በልጅነት ዕድሜያቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ለውጥ ማምጣት አለበት የሚል ድርጅት ተቀብሏቸው እርሳቸውም ከዕድሜ እኩዮቻቸው ጋር ሲታገሉ ቆይተዋል።

የፖለቲካው ፍላጎት ስለነበራቸው ቀዳማይ ኃይለ ስላሴ ይውረዱ ብለው ባንዲራ ይዘው ከፊት ተሰልፈው ተቃዋሚ ሆነው በወቅቱ መንግሥት እንዲቀየር ጠይቀዋል። በአጠቃላይ ከኢትዮጵያ ወጥተው ለ38 አመታት ቢኖሩም ኢትዮጵያን ከልባቸው ማውጣት አልቻሉም። ስለዚህም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወነውን እያንዳንዱን ነገር በአንክሮ ይከታተላሉ፤የተቻላቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ይጥራሉ። በአሁኑ ወቀትም በኢትዮጵያ ውስጥ ሀገራዊ ምክክር መጀመሩ አስደስቷቸውም የበኩላቸውን ጥረት ለማድረግ ተነስተዋል። በተለይም በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሀገራዊ ምክክሩ በንቃት እንዲሳተፉ በኩላቸውን ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

እኒህ እንግዳችንም ወይዘሮ አዜብ አልፍሬድ ሻፊ ጋር የሚባሉ ሲሆን በሀገራዊ ምክክሩ እና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አዘጋጅተንላችኋል መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን፡- ወደ አሜሪካን እንዴት ሔዱ ከሚለው እና በአሜሪካ ስለነበረው ሕይወትዎ ከማውራት እንጀምር?**

**ወ/ሮ አዜብ፡-** ኢትዮጵያ እያለሁ ወደ 11ኛ ክፍል ትምህርቴን ከመቀጠሌ በፊት ታናሽ ወንድሜ ሳምሶን አልፍሬድ በመኪና አደጋ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። በዛው በቤታችን አቅራቢያ ሃያ ሁለት አካባቢ የወንድሜ ሕይወት ማለፉ እና በሁለታችን መካከል የነበረው ግንኙነት፣ ልጅነቴ ሁሉም ነገር ተደራርቦ ሃዘኔን አከበደው። መሞቱን መቋቋም አቅቶኝ ነበር።

ቤተሰቦቼ የመንፈስ ጤንነቴ ጉዳይ አሳሰባቸው። ከሀገር ወጥቼ ሃዘኑ እንዲቀልኝ በማሰብ ወደ አሜሪካን ላኩኝ። በዛ አጋጣሚ ኢትዮጵያን ለቅቄ አሜሪካን ስገባ ፓን አፍሪካኒዝም የጀመረበት ጊዜ ነበር። እኔም የፖለቲካ ተሳትፎ ውስጥ ገባሁ። ነገር ግን ትምህርቴን አላቋረጥኩም ነበር። የመጀመሪያ ዲግሪዬን እንደያዝኩ ከዛ በላይ ትምህርቴን ለመቀጠል ብፈልግም መሥራት እና ከትምህርት ማረፍ አለብኝ ብዬ ወሰንኩ። ሥራ ስይዝ ትዳር መስርቼ ልጅ ወለድኩ። ስራዬን እየሠራሁ ልጄን አሳድጌ ዩኒቨርሲቲ ለማስገባት ደረስኩኝ።

ልጄ ስታድግ በአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ሜሪላንድ ሥራ ጀመርኩኝ። እዛ ዩኒቨርሲቲ የገባሁበት ምክንያት ለልጄ እና ለራሴ ነፃ የትምህርት ዕድል ለማግኘት ነበር። ያኔ እርሷን ሳስተምር እኔም በቴክኖሎጂ ማኔጅመንት ሁለተኛ ዲግሪዬን አገኘሁ። ልክ የሁለተኛ ዴግሪዬን ስይዝ ዕቅዴ ከአምስት ዓመት በኋላ ወደ ሀገሬ እገባለሁ የሚል ነበር። አምስት ዓመት ያልኩበት ምክንያት አሜሪካን ሀገር ሁሉ ነገር የሚገኘው በብድር ነው። መኪና በብድር ነው። ቤት በብድር ነው። በዛች አምስት ዓመት ሁሉንም ዕዳ ጨርሼ ሀገሬ ለመግባት አሰብኩ።

ጓደኞቼ ውሸት መስሏቸው ነበር። እኔ ግን ሀገሬ ስለመግባት የወሰንኩት ተንበርክኬ እየፀለይኩ ነበር። ለፈጣሪዬ ‹‹ ሀገሬ ብትወስደኝ ውሃ ተቋርጧል፤ መብራት የለም፤ የቆሻሻ ሽታ አለ›› ብዬ አላማርርም እል ነበር። ፈጣሪ ፈቅዶልኝ በዕቅዴ መሠረት ልጄን ዩኒቨርሲቲ ካስገባሁ በኋላ አክሰስ ካፒታል ተቋቁሞ ስለነበር እዛ ተቀጥሬ ኢትዮጵያ ገባሁ። ለ38 ዓመት አሜሪካን ኖሬ ወደ ኢትዮጵያ ተመለስኩ። አሁን አስራ አምስት ዓመት ሆነኝ።

**አዲስ ዘመን፡- በቀድሚያ ፖለቲካል ሳይንስ ከተማሩ በኋላ ደግሞ ለምን ቴክኖሎጂ ማኔጅመንትን መረጡ?**

**ወ/ሮ አዜብ፡-** የትምህርት ዘርፌን የቀየርኩበት ምክንያት አንደኛ ፖለቲካን በጣም ጠልቻለሁ። ሌላው ማኔጅመንት ቴክኖሎጂ ጥሩ ፊልድ ነው። ምክንያቱም ዘመኑ የቴክኖሎጂ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሜሪካን ሀገር በነበሩበት ጊዜ ኢትዮጵያን በተመለከተ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳትፎዎ ምን ያህል ነበር? በተጨማሪ**

**ወ/ሮ አዜብ፡-** ከኢትዮጵያ ከመውጣቴ በፊት የናዝሬት የልጃገረዶች ትምህርት ቤት እና የሴንጆሴፍ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለዕረፍት ትምህርት ሲዘጋ ገጠሩን ለማየት በሐራምቤ ኢትዮጵያ ፕሮግራም አማካኝነት ከከተማ ወጣን። ወሎ፣ ትግራይ፣ አስመራ ፣ ጎንደር እና ጎጃምን አየን። ለመጀመሪያ ጊዜ ሌላውን ኢትዮጵያን የገጠሩን ሕዝብ አኗኗር አወቅን። ያ በእኔ ላይ ትልቅ ተፅዕኖ ፈጥሮብኛል። በሰዓቱ የነበረው ነገር አልገባኝም። ረሃቡ እየጀመረ ነበር።

በተለይ ደሴ የነበረው ጭንቅላቴን ጎድቶት ነበር። ልክ አሜሪካ ስደርስ የተማሪ ንቅናቄ ማህበርተኞች ተቀበሉኝ። ለእንደዛ ዓይነት ነገር ዝግጁ ነበርኩኝ። ማህበሩ ኢዙና (ኢትዮጵያን ዩኒየን ኢን ኖርዝ አሜሪካ) ይባላል። እዛ ውስጥ ገባሁ። በዛ ጊዜ ‹‹ሀገር መለወጥ አለባት፤ መንግሥት መለወጥ አለበት›› አልኩ። ቀዳማይ ኃይለስላሴ ከስልጣን ይውረዱ እያልኩ ባንዲራ ይዤ ሰልፍ ወጣሁ።

በጊዜው የኮሚኒስት መጽሐፍን እያነበብን ውይይት እናደርግ ነበር። በስሜት የተነዳን ወጣቶች ነበርን። ስሜታዊነታችን ሀገር ከመውደድ የመነጨ ነበር። የሔድነው ከደህና ቤተሰብ ወጥተን ነው። ነገር ግን የሌላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይወት ያሳስበን ነበር። ያ የሐራምቤ ኢትዮጵያ ጉብኝት በጣም ልቤን የነካው ስለነበር የፖለቲካ ፍላጎቴ ከፍተኛ ሆነ።

ነገር ግን ብዙ ጓደኞቼ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ምክንያት ሕይወታቸውን አጥተዋል። መጀመሪያ ንቅናቄ ውስጥ ስንሳተፍ ትምህርት አቁመን ወደ ኢትዮጵያ ሔደን ለመታገል መዘጋጀት አለብን የሚል ሃሳብ መስተጋባት ጀመረ። እኔ ብልጥ ሆኜ ‹‹እኔ አባቴ ከምንም በላይ ትምህርትሽን አስቀድሚ ብሎኛል። ›› አልኩና ትምህርቴን ቀጠልኩኝ። ጓደኞቼ ትምህርታቸውን አቋርጠው ወደ ኢትዮጵያ መጡ።

ጓደኞቼ ኢትዮጵያ ሲመጡ መንግሥት ተለውጧል። ቀዳማይ ኃይለስላሴ ወርደው ደርግ ሀገሪቷን ተቆጣጥሮ ነበር። በእኔ እድሜ የነበሩ ምርጥ ሀገር የሚለውጥ ጭንቅላት ያላቸው ብዙ መሥራት የሚችሉ ወጣቶች በሙሉ አለቁ። የመጣው ለውጥም ከቀዳማይ ኃይለስላሴ የተለየ አልነበረም። የጓደኞቼ መሞት፤ ለውጡ እንደታሰበው አለመሆኑ፤ በፖለቲካ ውስጥ መሳተፍ አልነበረብኝም ብዬ እጅግ እንድቆጭ አደረገኝ። ሙሉ ለሙሉ ፖለቲካውን ጠላሁት። ነገር ግን ያም ቢሆን ማንበቤን እና መጠየቄን አላቆምኩም።


ፎቶ ፡- ገባቦ ገብሬ

ለወጣቶች እኛ የሠራነውን ስህተት አትድገሙት የሚል መልዕክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ። በጦርነት ከእልቂት ውጪ የሚመጣ ለውጥ የለም። ይህንን የምለው የጓደኞቼን መጨረሻ ስላየሁ ነው። ጓደኞቼ በሕይወት ቢኖሩ ኖሮ ምን ዓይነት ሕዝብ የሚያገለግሉ የሕክምና ባለሙያዎች እና ኢንጂነሮች መሆን ይችሉ ነበር? እያልኩ ራሴን እጠይቃለሁ። በጣም ሀገር ወዳዶች ስለነበሩ ሀገራቸውን ምን ያህል ይጠቅሟት እንደነበር ለመገመት ይከብዳል። ተምረው ሲጨርሱ ሀገራቸው እንደሚመጡ እርግጠኛ ነኝ። ፈረንጅ ሀገር ቁጭ ብለው ዘላለማቸውን ፖለቲካ እያወሩ አይኖሩም ነበር።

በዛ ጊዜ ዘመኑ የሶሻሊዝም ጊዜ ነበር። ሃዋርድ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የነበሩት መምህሮቼ በጣም ባለምጡቅ አዕምሮ ነበሩ። በተለይ ፖለቲካል ሳይንስ ያስተምሩ የነበሩ፤ ከሶስተኛው ዓለም እና ከሌሎችም ጥቁሮች በብዛት ካሉበት ትንንሽ ደሴቶች የመጡ ነበሩ። የፖለቲካል ሳይንስ መምህራኖቼ በወቅቱ ሶሻሊዝምን የሚደግፉ ዓይነት ነበሩ። በፖለቲካው ላይ መሳተፌ ትምህርቴ ላይም ረድቶኛል። የጥናት ወረቀት ለመስራት በፖለቲካ ውስጥ የነበረኝ ተሳትፎ በእጅጉ አግዞኝ ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- በእርግጥ መጀመሪያ ወደ ፖለቲካው የሳብዎ የሐራምቤ ኢትዮጵያ ጉብኝት ብቻ ነው? ወይስ አባት እና እናትዎ በፖለቲካ ውስጥ ተሳትፎ ነበራቸው?**

**ወ/ሮ አዜብ፡-** አባቴ ተራማጅ አስተሳሰብ ያለው ሰው ነበር። በቀዳማይ ኃይለስላሴ ጊዜ የፀጥታ ዳይሬክተር ነበር። ድሬዳዋ ሀገረ ገዢም ነበር። በጣም ጥሩ ሥራዎችን ሠርቷል። የሀገር ፍቅር ስሜት ነበረው። ለእኛም የሚያስተላልፈው ያንኑ የሀገር ፍቅር ስሜቱን ነበር። ደጋግሞ የሚናገረው ‹‹ከእኔ ዕርስት እና ሀብት አትጠብቁ፤ ለውጥ ይመጣል፤ ያለን መሬት ይወረሳል፤ ስለዚህ በማይወረሰው ጭንቅላታችሁ ላይ ሥሩ። ›› ይለን ነበር።

እናቴም ሀገር ወዳድ ናት። ቀዳማይ ኃይለ ስላሴን በጣም ትወድ ነበር። እርሳቸውን የሚቃወም ሰው እኔ እረግመዋለሁ ትል ነበር። አሜሪካን መጥታ ልጄን ስታሳድግልኝ እኔም ተቀየርኩኝ። አባት እና እናቴ ይመክሩኝ ነበር። ሀገር እንድወድ ሀገርን እንድጠቅም ሀገርን እንዳገለግል ይመክሩኝ ነበር።

አዲስ ዘመን፡- እርሶ እንደአንድ የፖለቲካ ተሳትፎ እንደነበረው እና የፖለቲካ ባለሙያ እንደሆነ ሰው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ዋነኛው ችግር ምንድን ነው?

ወ/ሮ አዜብ፡- ይህንን ለመመለስ ይከብደኛል። ነገር ግን አንድ ኢትዮጵያዊ ከአስተዳደጉ አንፃር ምኞቱ የተለያየ ነው። እኔ ወጣት በነበርኩበት ጊዜ አብዮታዊ ለውጥ ተመኝቻለሁ። አሁን ግን የምፈልገው ሰላማዊ ለውጥ ነው። ምክያቱም የኃይል አማራጩን አየነው፤ ወደታች ወረድን እንጂ ወደ ላይ አልወጣንም።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹እንደ ሀገር አብረን ለመዝለቅ...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

ስለዚህ ከአሁን በኋላ ሀገርን የሚጎዳ ነገር ሳይሆን ሀገርን የሚጠቅም ነገር ላይ መሥራት አለብኝ ብዬ ተነስቻለሁ። በእርግጥ በፊትም ሁኔታውን ስላልተረዳሁ ጃንሆይ ይውረዱ ብዬ ተሳትፎ ሳደርግ ነበር።

አሁን ላይ የእናት እና የአባቴ መሬት ላይ የሕፃናት ማቆያ ገንብቼ ሕፃናቶች ላይ እየሠራሁ ነው። ከአንድ ዓመት ጀምሮ እስከ አራት ዓመት ዕድሜያቸው እኔ ጋር ሲቆዩ፤ ብሔራዊ መዝሙር ይዘምራሉ፤ ባንዲራ ይሰቅላሉ። ያቺ ትንሿ ጥረቴ ታድጋለች ብዬ አስባለሁ። እኔ በልጅነቴ የተሠራብኝ የሀገር ፍቅር አድኅብኛል። ስለዚህ መፍትሔው የሀገር ፍቅር ላይ መሥራት ነው ብዬ አምናለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ አሁን ላስችበት ደረጃ የደረሰችው በትውልዱ የልጅነት ሕይወት ላይ በተገቢው መልኩ ባለመሠራቱ ነው ማለት ይቻላል?**

**ወ/ሮ አዜብ፡-** አዎ! የሕፃናት ትምህርት ቤት ላይ ትኩረት ያደረግኩት ለዚህ ነው። ልጆች ስለሀገራቸው በጥሩ መንገድ ቢማሩ ጥሩ ነው ብዬ አስባለሁ። ትልቅ ሰው ላይ ተፅዕኖ መፍጠር ጥሩ አይመስለኝም። ራሱ ሲያድግ በልጅነቱ የተሠራበት ነገር ተመልሶ ይመጣል። ለምሳሌ እኔ ስለሀገር ፍቅር የተማርኩት አሜሪካን ውስጥ ገብቼ አይደለም። በልጅነቴ እናት እና አባቴ ስለ ሀገር ፍቅር ያስተማሩኝ በመሆኑ ነው።

ያ በልጅነቴ የተሠራብኝ ከውስጤ ሊወጣ አልቻለም። ነገር ግን የመጣው በተለያየ ሁኔታ ነው። ድሮ ወጣት ሳለሁ በአብዮታዊነት ስሜት መጥቷል። አሁን ደግሞ ብዙ ጓደኞቼን አጥቼ ስበስል ለውጥ የሚመጣው በሰላማዊ መንገድ ነው ብያለሁ። ምክንያቱም የጦርነት ለውጥ ለማንም አልበጀም። በቀዳማይ ኃይለስላሴ ጊዜም የተገደሉት ሚኒስትሮች እና በደርግ ጊዜም ያጣናቸው ብዙ ወጣቶች ሀገር መጥቀም የሚችሉ ነበሩ። ነገር ግን በጦርነት ሰው በመግደል ለውጥ እናመጣለን ብለን አጣናቸው።

ብዙ የተማሩ ሰዎች፤ በጊዜው ሀገር ጠል አድርገን ያሰብናቸው እነአክሊሉ ሀብተወልድ አሁን ስናውቃቸው፤ ለሀገራቸው የከፈሉትን ዋጋ ስንረዳ ባለፈው ድርጊታችን እንቆጫለን። ስለዚህ አሁንም ከመቸኮል ይልቅ ረጋ ብለን መንቀሳቀስ አለብን። በእርግጥ አውቄያለሁ ብሎ መምከር ይከብዳል። ነገር ግን አንድ በችግር ያደገ ሰውን ለምን እንደዚህ አላደረግክም ወይም ለምን እንደዚህ አታደርግም ማለት ይቸግራል። እኔ ኢትዮጵያ ውስጥ ሳልቸገር ኖሬያለሁ። ለሀገሬ የሆነ ነገር መስራት አለብኝ። ብዬ በምችለው አቅም እየሠራሁ ነው።

ነገር ግን ሰው ጦርነት ውስጥ እንዲገባ አልፈልግም። በእርግጥ አሁን እኔ አርጅቻለሁ፤ ጦር ይገፍ ጫካ መግባት አልችልም። ስለዚህም ሕፃናት ሲያድጉ ስለጦርነት እንዳያስቡ የማያልቅ የሀገር ፍቅር እንዲኖራቸው የአቅሜን አደርጋለሁ። አሁንም እናት እና አባቴ እኔ ላይ የሠሩትን እየሠራሁ ነው። በኋላ እየኮተኮትኳቸው ያሉ ልጆች እያደጉ ሲመጡ ሁሉንም ማመዛዘን ሲጀምሩ ስለሀገራቸው በጥልቀት ያስባሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ልጆች የሀገር ፍቅር እንዲኖራቸው ወላጆች በምን መልኩ መሥራት አለባቸው?**

**ወ/ሮ አዜብ፡-** እኔ ስለአባቴ ብናገር አባቴ ለሁለት ዓመት የድሬዳዋ ገዢ ነበር። የድሬ ሰዎች በስሙ ድልድይ ሰይመውለታል። አልፍሬድ ሻፊ የተሰኘ ድልድይ በድሬዳዋ አለ። አባቴ ድሬዳዋ ሔዶ ሀገር ያቀናው ሀገሩን ስለሚወድ ነው። ቤተሰቦቼ በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም የሀገር ፍቅር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ሲያሳዩን ነበር። እናቴም ሀገሯን የምትወደው ከልቧ ነበር። ምንም እንኳ ውጣ ውረዶች ቢኖሩም ያ የተገነባው ፍቅር መልሶ መምጣቱ አይቀርም።

አባቴ ድሬዳዋ የሔደው የደቡብ ተወላጅ ጉራጌ ሆኖ ነው። ድሬዳዋ በነበረበት ጊዜ ለድሬዳዋ ሕዝብ ሙሉ ፍቅር ሰጥቷል። እኔም ከእዛ ብዙ ተምሬያለሁ። የሀገር ፍቅር ግን አንዳንዴ የሚወረስ ይመስለኛል። አሜሪካን ሀገር ሰባት እህት እና ወንድሞች አሉኝ። ሁኔታዎች ከኢትዮጵያ በእጅጉ የተለዩ ናቸው። እዛ ኑሪ ብባል አይመቸኝም። ምክንያቱም የሀገር ፍቅር ጉዳይ ከልጅነቴ ሰርፆብኛል።



የተማሪ ንቅናቄ ውስጥ መግባቴም ደግሞ ሀገሬን የበለጠ እንዳውቃት አድርጎኛል። ከዛ በኋላ ሁልጊዜ ሀገሬ የመግባት ፍላጎት ነበረኝ። ኢትዮጵያ ከገባሁ አሁን አሥራ አምስት ዓመት ሆነኝ። ኢትዮጵያ ይመቻል ማለት አይደለም። በተለይ አሜሪካ ሀገር ለኖረ ሰው ኢትዮጵያ ላትመቸው ትችላለች። እኔ ግን የትም ሀገር ብኖር እንደዚህ ሀገር አያስደስተኝም።

አዲስ ዘመን፡- በውጪ ያሉ ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸው ምን ማድረግ አለባቸው ይላሉ?

ወ/ሮ አዜብ፡- እንዲህ ያድርጉ ለማለት ይከብዳል። ነገር ግን ሁሉም ራሱን ይፈትሽ። ሀገር መውደድ እና ሀገርን ማገዝ ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ ብቻ አይደለም። የትም ሆኖ ኢትዮጵያን አለመርሳት ይቻላል። ለምሳሌ እህት እና ወንድሞቼ እነርሱም ባሉበት እንዳልረሷት እርግጠኛ ነኝ። አሁን ልጆች ላይ እየሠራሁ ያለሁት እናት እና አባቴ ባቆዩልኝ ቤት ውስጥ ነው። ቤቱን እና ቦታውን ሀገሬን ለማገልገል እንድጠቀምበት ወንድም እና እህቶቼ መፍቀዳቸው በራሱ ትልቅ ነገር ነው። እህት እና ወንድሞች ሀገር ወዳድ ስለሆኑ ይህንን ፈቅደውልኛል።

አሜሪካን ሀገር ብዙ ቤተሰብ አለኝ። ሁሉም ኢትዮጵያ ገብተው መኖር እና ለኢትዮጵያ መሥራት ይፈልጋሉ። ነገር ግን የተሻለች ኢትዮጵያን እየጠበቁ ነው። እኔ ግን ኢትዮጵያን የተሻለች የምናደርጋት ራሳችን ነን ብዬ ሀገሬ ገብቼ እየሠራሁ ነው። አሁን በእኔ ይቀናሉ። በእርግጥ መብራት ይጠፋል፤ ውሃ ይቋረጣል፤ ሌባ ቤት ቢሰብር ፖሊስ የሚደርሰው ቆይቶ ነው። ነገር ግን ያም ቢሆን ሀገር ሀገር ናት።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሕፃናት ማቆያው የተወሰነ ነገር ይበሉን?**

**ወ/ሮ አዜብ፡-** የሕፃናት ማቆያ ነው። አሁን 53 ልጆች አሉ። ሲጀመር በስምንት ልጆች ነበር። ከተቋቋመ 10 ዓመቱ ነው። በየዓመቱ እየተመረቁ ወደ ትምህርት ቤት ይገባሉ። እዚህ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ። እየሰራሁ ያለሁት ትርፍ ገንዘብ ለማግኘት አይደለም። የምሰራው ለሀገሬ ሥጦታ ለማበርከት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ውስጥ ስለተጀመረው ሀገራዊ ምክክር ምን ይላሉ?**

**ወ/ሮ አዜብ፡-** ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወደ ሌላ አማራጭ ከመግባት ይልቅ ምክክሩን መሞከር አለበት። ብዙ ሌሎች ነገሮችን ሞክረናል፤ ነገር ግን አልተሳካልንም። ኢትዮጵያ ከዚህ በላይ መድረስ ያለባት ደረጃ ላይ መድረስ ነበረባት። እዛ ላይ መድረስ ያልቻለችው እኛ የሞከርናቸው መንገዶች ትክክለኛ ባለመሆናቸው ነው።

ዋነኛው ጉዳይ ኢትዮጵያ እንዳታድግ የሚፈልጉ የራሳቸው ዓላማ ያላቸው እንዳሉ እርግጠኛ ነኝ። አሜሪካም ቢሆን ኢትዮጵያን የምትፈልገው ከራሷ ጥቅም አንፃር ብቻ ነው። የምትፈልጋት ለእርሷ ጠቃሚ እስከሆነች ብቻ ነው። አሁን አለም ላይ ከባድ ችግር አለ። ምክክሩ ምናልባት ሀገራችን ላይ ብቻ ሳይሆን ዓለም ላይ ያለውንም ችግር እንድናውቀው ያስችለናል። ኢትዮጵያ እንዳታድግ ፣ እንድትከፋፈል የሚሠሩ ኃይሎችን ለይተን እንድናውቀው ያስችለናል።

አንዳንዴ የገዛ የሀገራችን ሰዎች በገንዘብ ተገዝተው መከፋፈል ላይ እንደሚሠሩ ማወቅ አለብን። ይህንን ስንል ኢትዮጵያን የመከፋፈል አጀንዳን ይዘው የሚንቀሳቀሱ ኢትዮጵያውያንም ሆኑ የሌሎች ሀገር ዜጎች መነሻቸው ኢትዮጵያውያንን ጠልተው ሳይሆን፤ የእነርሱ ሀብት በእኛ መውደቅ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ነው። እኔ መጠቀም አለብኝ በሚል ነው።

እኛም እርስ በእርስ መጣላታችንን እስካላቆምን ድረስ፣ እርስ በእርስ እስካልተረዳዳን እስካልተደማመጥን ድረስ በሀገራችን ያለው ችግር መፍትሔ ያገኛል ብዬ አላምንም። እስከ አሁንም ያለነው በፈጣሪ እርዳታ ነው። ሃይማኖተኛ አይደለሁም። ነገር ግን እንደጠላቶቻችን ብዛት፣ እንደተሠራብን ሥራ እንፈርስ ነበር። በፈጣሪ እርዳታ እስከ አሁን ቆይተናል። ከዚህ በኋላ አብረን እንደ ሀገር አብረን ለመዝለቅ ሀገራዊ ምክክሩ ከፍተኛ ፋይዳ አለው ።

**አዲስ ዘመን፡- አንዳንድ ሀገራት ኢትዮጵያን ለምን በጠላትነት ማየት አስፈለጋቸው ?**

**ወ/ሮ አዜብ፡-** ኢትዮጵያ በብዙ መልኩ ታሰጋቸዋለች። ኢትዮጵያ ለአፍሪካውያን ጥሩ ምሳሌ በመሆኗ ቅኝ ገዢዎች በጠላትነት ያዩዋታል። ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ምሳሌ የምትሆንበት ሁኔታ በመኖሩ፤ ጥሩ ምሳሌ እንዳትሆን መፍረስ ይኖርባታል የሚል ፍላጎት አላቸው። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ካደገች ልክ ቅኝ ገዢነታቸው እንደተመናመነው ሁሉ፤ አፍሪካን እንደፈለጉ የሚዘርፉበት ዕድልም ይመናመናል። ሀገሪቱ ማደግ ያልቻለችው በዚህ ምክንያት ነው። ምንም እንኳ በየዘመኑ መንግሥታትን ብንቃወምም፤ መንግሥታቱም የሚችሉትን ሲሞክሩ ነበር።

የኢትዮጵያ ማደግ ሌሎችንም ስለሚያነቃ እና እንዲያድጉ ስለሚያደርግ እንድታድግ አልተፈለገም። ያንን የውጪ ጠላቶችን ሴራ እስከምንረዳ እና እርስ በእርስ መጣላታችንን እስካላቆምን ድረስ ሀገራችን ማደግ አትችልም። ኢትዮጵያ እንዳታድግ ይልቁኑም እንድትፈርስ በውጪ ጠላቶች ስትራቴጂ ተነድፎ በየጊዜው ይሠራባታል። ይህንን ማወቅ አለብን። ትልቁ የውድቀታችን መንስኤ የውጪ ጠላት የሚሠረው ሥራ ነው። ይህንን በቅጡ እስካልተረዳን ድረስ ሀገራችንን አንድ አድርጎ ማስቀጠል እና ማሳደግ አንችልም።

ልብ ብለን ከተመለከትን ኢትዮጵያን የሚል ኃይል በውጪ ጠላት ሴራ እንዲከፋፈል ይደረጋል። እኔ የተማሪ ንቅናቄ ውስጥ ሆኜ ሲጀመር ንቅናቄው አንድ ቢሆንም፤ በኋላ ግን ለሁለት ተከፍሏል። በየቦታው ኢትዮጵያውያንን እየከፋፈሉ አንድ እንዳንሆን የሚሠሩበት ሁኔታ አለ። ይህንን ካልተረዳን የውጪ ጠላት እየተጫወተብን ይኖራል። ለምሳሌ በትግራይ ጦርነት የነበረ ጊዜ የጠላቶቻችን መገናኛ ብዙኃኖች በምን መልኩ እንደሚዘግቡ ስንታዘብ ነበር። ቢቢሲ፣ ሲ ኤን ኤን እና አልጀዚራ እንዴት ሲዘግቡ እንደነበር አይተናል። ኢትዮጵያ እንድትበተን እንዳትጠነክር ፍላጎት ስለነበራቸው የሚዘግቡት በዛው መልኩ ነበር። አሁንም ቢሆን ውስጥ ውስጡን እየቦረቦሩን መሆኑን ማወቅ አለብን። ነገር ግን ተስፋ እንደማደርገው ያቋስሉን ይሆናል እንጂ አያፈርሱንም።

**አዲስ ዘመን፡- የሀገራዊ ምክክርን በተመለከተ ምን ይላሉ?**

**ወ/ሮ አዜብ፡-** መዳን ያለባቸው ብዙ ቁስሎች መኖራቸውን አውቀን፤ እነዚህ በእኛ ብቻ ሳይሆን በውጪ ጠላቶች የተተከሉት ቁስሎች እንዲነቀሉ ሁሉንም ሀገራዊ ምክክር ላይ ለማሳተፍ ጥረት መድረግ አለበት። ለዘመናት እንድንለያይ ሲሰራብን ኖረናል። እኔ ቀዳማይ ኃይለስላሴ ይውረዱ ብዬ ሰልፍ መውጣቴ ትክክል ይመስለኝ ነበር። የኢትዮጵያ የውጪ ጠላቶች እየሠሩ መሆኑን በሰዓቱ አልገባኝም ነበር። ሀገሬን ወደ ኋላ ያስቀረው የራሴ መንግሥት ነው ብዬ ተቃወምኩ። አሁን ግን ካረጀሁ በኋላ ተረዳሁት።

እነርሱ የተፈጥሮ ሀብታቸውን ጨርሰውታል። አልበቃ ብሏቸው ጨረቃ ላይ እየወጡ ያሉት ሀብት ፍለጋ ነው። አፍሪካን መቦርቦር የእነርሱ የመኖር ዋስትና ነው። ይህንን መረዳት ያስፈልጋል። ኢትዮጵያን ለማፍረስ ከ60 ዓመታት በላይ የሰሩትም አፍሪካን የመዝረፍ ጉዟቸው እንዳይደናቀፍ ነው። ያጣሉን፣ አሁንም እያጣሉን ያሉ እና ወደ ፊትም ለማጣላት ጥረት የሚያደርጉ መኖራቸውን እስካልተገነዘብን ድረስ ሀገር ማደግ አትችልም። ሀገራዊ ምክክሩ እስከአሁን ሲያጣሉን የቆዩ እና አሁንም እያጣሉን ያሉ መኖራቸውን እንድንረዳ ያግዘናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

በሀገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ጥቅም በማግኘታቸው ሀገራቸውን ለጠላት አሳልፈው የሚሰጡ አሉ። ምክክሩ እነዚህ ምን እየሠሩ መሆኑን ለማወቅ ያግዘናል የሚል እምነት አለኝ። አሁን በዓለም ላይ ያለው የሀብት ሽሚያ ከፍተኛ ነው። ሀብታም ሀገሮች ከምን ጊዜውም በላይ የእኛ ሀብት ያስፈልጋቸዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ሀገራዊ ምክክር ላይ በሚካሔዱ ስብሰባዎች ተሳትፈው ነበር። ጅምሩን እንዴት አዩት ?**

**ወ/ሮ አዜብ፡-** ቀዳማይ ኃይለስላሴ ‹‹መጀመር እናውቃለን፤ ችግራችን መጨረስ ነው። ›› ብለው ነበር። ጅምሩ በጣም ጥሩ ነው። በጣም ተደስቻለሁ። ነገር ግን አንድ የውጪ ጠላት ገብቶ ከበጣጠሰን እንወድቃለን። ስጋቴ ይሔ ነው። ሌላው ግን ምክክሩ ላይ የሚሳተፉ ሰዎች ፍላጎት ያላቸው ቢሆኑ መልካም ነው። ቀስ ብሎ መሠረቱ የጠነከረ ነገር ወደ ላይ ሲወጣ ያድጋል እንጂ አይፈርስም።

ሀገራዊ ምክክሩ ላይ መሠራት ያለበት ሥር መሠረቱን በማጥበቅ ነው። ይሔ ውስጣዊ ስሜትን ይጠይቃል። ምን አገኛለሁ ብሎ የሚመጣ እና ምን ላድርግ ብሎ የሚመጣ ይለያያል። ዋናው ጉዳይ ፈጣሪ የኢትዮጵያ ዘመን ያድርግልን።

**አዲስ ዘመን፡- አሜን፤ ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ አመሰግናለሁ።**

**ወ/ሮ አዜብ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

## ትኩረትና ጥንቃቄ ለባህላዊ መድኃኒቶች አጠቃቀም

**እየሩስ ተስፋዬ**



በኢትዮጵያ ብዙ ሠዎች ድንገት ህመም ቢሰማቸው አልያም የህመም ስሜት ሲብስባቸው እንደመጀመሪያ መፍትሄ የሚወስዱት ባህላዊ መድኃኒቶችን መጠቀም ነው። ፌጦ፣ ዳማከሴ፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ዝንጅብል፣ ጤና አዳም፣ ሽፈራው (ሞሪንጋ)፣ተልባና የመሳሰሉ እፀዋቶችና አዝርእቶችን በተለያዩ መንገዶች በማዘጋጀት ከህመማቸው ለመፈወስ ይጠቀሙባቸዋል። ኢትዮጵያን ጨምሮ በአፍሪካና በሌላው ዓለም የሚገኙና 80 በመቶ የሚጠጉ ህዝቦች የባህል መድኃኒት እንደሚጠቀሙ መረጃዎች ያመለክታሉ። ባህላዊ መድኃኒቶች በቀላሉ የሚገኙ መሆናቸው፣ ብዙ ሰዎች «ፈዋሽነት» አላቸው የሚል እምነትና አስተሳሰብ መያዛቸው፣ በዋጋ ረገድም ተመጣጣኝ መሆናቸው በብዙዎች ዘንድ ተመራጭ ያደርጋቸዋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞም የባህላዊ መድኃኒቶች አወሳሰድና አጠቃቀም ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ መሆን እንዳለበት በጤና ባለሙያዎች ይመከራሉ። ይህ ሳይሆን ሲቀር ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያመዝን እንደሚችል ይነገራል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ የባህል መድኃኒትን በስፋት የማስተዋወቁ ተግባር በተለይም በማህበራዊ ሚዲያ በስፋት የመሰራጨቱና የመካሪዎች ቁጥር እየተበራከተ መምጣት በተደጋጋሚ ይታያል። ኢትዮጵያ በአዝርእት እና በእጽዋት የታደለች ሀገር ናት። ይህም ብዙዎች ባህላዊ መድኃኒቶችን በቀላሉ እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል። ይሁን እንጂ ፍቱነቱ እና ደህንነቱ የተረጋገጠ የባህል መድኃኒት ጥናትና ምርምር ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ይታወቃል። የባህል መድኃኒቶቹን አብዝቶ ያለጥንቃቄ የመጠቀሙ ነገር ሲበዛ ጉዳቱ የከፋ ሊሆን እንደሚችል በሚገባ ማጤን ያስፈልጋል።

የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በባህላዊና ዘመናዊ መድኃኒቶች ላይ የተለያዩ ምርምሮችን ያደርጋል። በኢንስቲትዩቱ የባህልና ዘመናዊ መድኃኒት ልማት እና ምርምር ዳይሬክተር ወይዘሮ ፍሬሕይወት ተካ እንደሚገልጹት፣ በባህላዊና ዘመናዊ መድኃኒቶች ዙሪያ የምርምር ሥራ ሁሌም እንደሚደረግ መታወቅ አለበት። ጥሩ ውጤት ከሚገኝባቸው የምርምር ውጤቶች ኅብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል የሚሰሩ ስራዎች አሉ። በተለይም የባህል መድኃኒት ላይ የሚደረጉ የምርምር ሥራዎች ላይ ፈታኝ ነገሮች አይጠፉም። «ማኅበረሰቡ የባህል መድኃኒት ላይ ያለው መረዳት እና ምርምሩ ምንድ ነው?» የሚለው እንደ አንድ ክፍተት ይጠቀሳል። ከዚህ አኳያም በፍጥነት አገልግሎት ላይ የሚውል የሚመስላቸውም ጥቂቶች አይደሉም።

ፍርዶስ አብዱልሀፊዝ በኢትዮጵያ የምግብ እና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን የመድኃኒት ምዝገባ ዳይሬክተር ክፍል ውስጥ ባለሙያ ሆነው ይሰራሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፣ ባለስልጣኑ ባህላዊውንም ሆነ ዘመናዊ መድኃኒት እየተቆጣጠረ ይገኛል። የሚቆጣጠርበት መንገድ ራሱን የቻለ ሂደቶች አሉት። ባለሙያዎች መጥተው የራሳቸውን መድኃኒት ይዘው ወደ ባለስልጣኑ በማቅናት መመዝገብ መቻል አለባቸው። ቁጥጥር የሚደረግባቸው መድኃኒቶችን በተመለከተም፤ በምን ሁኔታ ነው የተመረቱት? የሚሉትን እና የተለያዩ ሰነዶች እንዲሁም የሚደግፉ ጥናቶች ምንድን ናቸው? በትክክለኛው የአመራረት ሂደት ነው ወይ የተመረቱት? የማምረቻው ቦታ ምን ይመስላል? የሚጠቀሟቸው ግብአቶችስ? እንዲሁም ባሉሙያው ስለመድኃኒት ጥልቅ እውቀት አለው ወይ? የሚለውን አካቶ ፍቃድ በመስጠት ለብዙኃኑ እንዲመረት ይደረጋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች አማካኝነት ባለሙያ ሳይሆኑ እንደባለሙያ ሆነው ሰዎች ባህላዊ መድኃኒትን መጠቀም እንዳለባቸው የሚመክሩ ሰዎች ቁጥር ቀላል አይደለም። ይህንን በተመለከትም ፍርዶስ እንደሚያብራሩት፤ ዘመናዊም ሆነ ባህላዊ መድኃኒት በማህበራዊ ሚዲያም ይሁን በብዙኃን መገናኛ ማስተዋወቅ በኢትዮጵያ ምግብ እና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን አዋጅ ቁጥር 1112 የተከለከለ ነው። ይህንን የሚያስተዋወቁ ህገ ወጥ ናቸው። ማኅበረሰቡን ሊያደናግር ይችላል በሚል እሳቤ ክልከላ ተደርጎበታል።

ምርምር በባህሪው ረዥም ጊዜ የሚወስድ እንዲሁም ለአንድ ተመራማሪ የትኛውም ውጤት ቢሆን ውጤት እንደሆነ የሚገልጹት ወይዘሮ ፍሬሕይወት፤ የውጤት ቅበላ ላይ ያለውን ክፍተት ያነሳሉ። ችግሩን ለማቅለል ከባህል መድኃኒት አዋቂዎች ጋር በጋራ በመሆን የምርምር ሥራዎች ይሠራሉ። ነገር ግን ምርምር ሲደረግ እነርሱ ብቻ የፈለጉት እንዲሆን የመፈለግ፤ በተጨማሪም ውጤቱን ለመቀበል ብሎም ጊዜ የሚወስዱ የምርምር ውጤቶችን ታግሶ ያለመቀበል አዝማሚያ በስፋት ይታያል።

ሌላው ፈታኙ ነገር ከእርዳታ ሰጪዎች መካከል አብዛኞቹ በሀገር በቀል የምርምር ሥራን የመደገፍ ፍላጎት የላቸውም። በዚህም መንግሥት በሚሰጠው ገንዘብ ለመሥራት አስገዳጅ ስለሚሆን፤ ጥናቱን በስፋት ለመሥራትም የበጀት እጥረት አለ። በአሁኑ ወቅት መሻሻሎች ያሉ ሲሆን፤ ጤና ሚኒስቴርም ድጋፍ እያደረገ ይገኛል። ከተሠሩ ሥራዎች መካከል እንደ ሀገር የባህል መድኃኒት ፍኖተ ካርታ ተዘጋጅቷል። ከባህል መድኃኒት አዋቂዎች ጋር በመቀራረብና በመተማመን ቢሠራ ችግሩ ይፈታል። የባህል መድኃኒት አዋቂዎችም መንግሥትን ማመን ይኖርባቸዋል።

እንደ ባለሙያዋ ገለፃ፤ በተለያዩ ጊዜ በሚከሰቱ ወረርሽኞች እና የቅድሚያ ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚሠሩ ጉዳዮች በመኖራቸው ሥራውን ወደ ጎን በማድረግ፣ ባለሙያዎችን በማሰልጠን እና ሀብቱንም ከመጠቀም አንጻር አመርቂ ሥራዎች አልተሠሩም። የባህላዊ ሀኪሞችም ከባለሙያዎች ጋር በቅንጅት መሥራት ቢችሉ ጥሩ ነበር። በነበር ቁጭት ውስጥ ብቻ ከመኖር ይልቅ ከምርምር አካላት ጋር በጋራ ቢሠሩ የተሻለ እገዛ እንዲያገኙ ይረዳቸዋል።

«በባህል መድኃኒት ላይ ካደጉት ሀገራት መካከል ቻይናና ህንድ በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። ከአፍሪካ ደግሞ ደቡብ አፍሪካና ጋና ተጠቃሾች ሲሆኑ ፤ጋና የባህል መድኃኒት ዩኒቨርሲቲ አላት። በኢትዮጵያም ከሚመለካታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ካልተሠራ ብዙ ርቀት ለመጓዝ አዳጋች ይሆናል። » የሚሉት ወይዘሮ ፍሬሕይወት፤ በመተባበርና በመቀራረብ ቢሠራ ግን እንደሌሎቹ ሀገራት ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻል ያብራራሉ።

እንደ ባለሙያዋ ማብራሪያ፣ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ባህላዊ መድኃኒቶች እና ቁጥጥር የማይደረግባቸው ባህላዊ መድኃኒቶች ተብለው ተለይተዋል። ቁጥጥር ከማይደረግባቸው መካከልም ማንኛውም በቤት ውስጥ የሚወሰዱ ባህላዊ መድኃኒቶች ናቸው። ለአብነትም ጤና አዳም፣ዳማከሴ እና የመሳሰሉት ናቸው። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በባህላዊ ሀኪም የሚሠጥ ባህላዊ መድኃኒት ነው። ባህላዊ ሀኪሙ ራሱ ኃለፊነትን ወስዶ ፤ ራሱ ክትትል አድርጎ የሚሠጣቸው ሲሆን ፤በዚህም ባለሙያው ላይ ሳይሆን መድኃኒቶቹ ላይ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል።

ቁጥጥር የሚደረገው ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የጎንዮሽ ጉዳት ያለው የባህላዊ መድኃኒትችን ላይ ነው። ለብዙዎች ተመርቶ የሚቀርብ እንዲሁም በባለስልጣኑ የተመዘገበ ከሆነ ቁጥጥር ይደረግበታል። በዚህ ወቅት የሚያስፈልገው ምንድ ነው? የተጠኑ ጥናቶች፣ የመድኃኒቱ የጎንዮሽ ጉዳቱ ምን ነበር? እስካሁን ሲጠቀሙ ውጤቱ ምንድ ነው? የሚለውን አያይዘው ሊቀርቡ ይገባል።

ባለሙያዋ አክለው እንዳብራሩት፤ የጎንዮሽ ጉዳቱ ስጋት ውስጥ የሚከት (ክሊኒካል) ለሚባሉ ህመሞች ወይም ለረዥም ዓመታት ከታማሚው ጋር የሚቆዩ በሽታ ሲኖር የሚሰጥ ባህላዊ መድኃኒት ነው። እርሱም ቢሆን ጥልቅ የሆነ ጥናታዊ ጽሁፍ የሚያስፈልገው ሲሆን፤ ሰዎችም ላይ ይሁን እንስሳት ላይ የተደረገ ጥናት ውጤት አያይዘው እንዲመጡ ይደረጋል።

**‹‹ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች አማካኝነት ባለሙያ ሳይሆኑ እንደባለሙያ ሆነው ሰዎች ባህላዊ መድኃኒትን መጠቀም እንዳለባቸው የሚመክሩ ሰዎች ቁጥር ቀላል አይደለም። ››**

የባህል መድኃኒት ተብሎ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ሲዘዋወር በብዛት ይታያል። አንዳንዶች መንገድ ላይም ይሁን ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ያስተዋውቃሉ። ይህም ህጋዊ አይደለም። ስለሆነም ከህግ ባለሙያዎች ጋር በጋራ በመሆን እየሰራን እንገኛለን። ከዚህ በኋላም ተቋሙ ወደ እርምጃ ይሄዳል። ባህላዊ መድኃኒት በሀገር ደረጃ እስካሁን ያልተጠቀምነበት ሀብት ነው። ቁጭት ውስጥ ሊከተን የሚገባም ጉዳይ ነው። ስለዚህም ከዘመናዊ መድኃኒት ጋር እኩል በእኩል መጠቀም የሚቻልበት ሁኔታዎች መፈጠር መቻል አለበት። ኅብረተሰቡም ያልተመዘገቡ ባህላዊ መድኃኒቶችን ከመጠቀም ቢቆጠብ የተሻለ ይሆናል።

እንደ ባለስልጣን መስሪያ ቤት ከዚህ በኋላ ኅብረተሰቡ የተመዘገቡ ባህላዊ መድኃኒቶችን በቀላሉ እንዲያገኝ ይደረጋል። ከዚህ አንጻር ከኅብረተሰቡ ጋር አብሮ መሥራት ይገባል። ባህላዊ መድኃኒት ላይ ከፖሊሲ እና ከመመሪያ አንጻር ይሠሩ እንጂ ወደ መሬት አውርዶ ከመሥራት አንጻር ግን ገና ብዙ ጥረቶችን ይጠይቃል።

«አሁን ላይ ጥሩ ጅምሮች አሉ። ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም በጋራ እየተሠራ ሲሆን፤ በተለይም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመናበብ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው። አሁን ላይ መንግሥት ብዙ ድጋፍና ትኩረት የሰጠው ቢሆንም ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት መሠራት ይኖርበታል። ከሌላው በተለየ መንግሥት የተለየ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ዘርፉን መደገፍም ብዙኃኑን የባህል መድኃኒት ተጠቃሚውን ማኅበረሰብ የጤና ጥያቄውን ለመመለስ እድል የሚሠጥ በመሆኑ መንግሥት በገንዘብ መደገፍ ይኖርበታል።

ዳይሬክተሯ እንደሚያስረዱት፣ ብዙዎች የባህል መድኃኒት ያድናል የሚል እምነቱ አላቸው። በዚህም ምክንያት መድኃኒቱን እንጠቀማለን ነገር ግን ደህንነቱ እና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ እንዲሁም በቂ መረጃ ያለውን የባህል መድኃኒት መጠቀም ይኖርበታል። አንዳንዴም በዘመናዊ መድኃኒት መፍትሄ ያልተገኘላቸው በሽታዎች ያሉ በመሆናቸው የባህል መድኃኒትን ለመጠቀም የሚገደዱ ሰዎች መኖራቸውን ከግንዛቤ በማስገባት የህክምና ባለሙያዎችን ማማከር ይገባል። በተጨማሪም የባህል መድኃኒት ላይ ምርምር ለመሥራት ፍላጎት ካላቸው ተመራማሪዎች ጋር በጋራ በመሥራት ለሀገር አስተዋጽኦ ማበርከት እንደሚቻል በማመን በጋራ መስራት ያስፈልጋል።

«እኛ እስከዛሬ እየተጠቀምን ምንም አልሆንም» የሚሉ አሉ። ከዚህ በተቃራኒም ተጠቅመው ጉዳት እንደደረሰባቸው የሚገልጹ ጥቂቶች እንዳልሆኑ ያነሱት ፍርዶስ፤ በማህበራዊ ሚዲያም ይሁን በበሌሎች መገናኛ አማራጮች ኅብረተሰቡን የሚያደናግሩ በግለሰብም ይሁን በድርጅት ደረጃ ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ማድረግ ይገባል። ከዚህ ጎን ለጎንም የምርምር ተቋማት፣ብዙኃን መገኛኛ እና ከሚመለከታቸው ጋር አብሮ ካልተሠራ አመርቂ ውጤት ማምጣት አይቻልም። ስለዚህ ማህበረሰቡም እስካሁን ተጠቅሜ ምንም አልሆንኩም ብሎ ችላ ማለት የለበትም።

የጤና ሚኒስቴርም ጉዳዩን አስመልክቶ በማህበራዊ ትስስር ገጹ ላይ እንዳሰፈረው፤በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች በተለይም በቲክ ቶክ ሀሰተኛ የጤና መልእክቶች በብዛት በመሰራጨት ላይ ይገኛሉ። ይህ ድርጊት ኃላፊነት በጎደላቸው፣ የጤና ሙያ ሳይኖራቸው «የጤና ሙያዊ ምክር እንሰጣለን። » በማለት የኅብረተሰቡን ጤና ሊጎዳ በሚችል መልኩ ትክክለኛ ያልሆነ መልእክት እያሰራጩ ይገኛሉ። «የጤና መረጃዎችን ከትክክለኛ የመረጃ ምንጭና ከጤና ባለሙያ ብቻ ማግኘት እንደሚገባ አውቀው ፤ በማህበራዊ ሚዲያ ከሚሰራጩ ሃሰተኛ የጤና መረጃዎች እና ከሚያስከትሏቸው የጤና አደጋዎች ተጠበቁ» ሲል ማሳሰቡ ይታወሳል።

በጥቅሉ ኢትዮጵያ የባህል መድኃኒትን በመጠቀም የካበተ ልምድ ያላት ሀገር መሆኗን ከግንዛቤ በማስገባት የባህል መድኃኒታቸውን አዘምነው ከራሳቸው አልፈው ለብዙዎች እንደተረፉት ቻይና፣ህንድ እና የሌሎች ሀገራት ልምድ በመቅሰም ኅብረተሰቡ ጤናውን ከመጠበቅ ባሻገር ለመድኃኒት ግዢ የሚወጣውን ወጪ መቀነስ እንደሚቻል ብዙዎች ይስማማሉ። የህክምና ባለሙያዎችም በባህል መድኃኒት አጠቃቀም ዙሪያ ሰፊ እና ወቅቱን የጠበቁ ሥራዎችን መሥራት እንዳለባቸው ይጠበቃል።

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## ‹‹በሰላም ስለ ሰላም እንመካከር!››

**የሃይማኖት ተቋማት ተወካዮች ድምጽ፤**

የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ የአባል ቤተ እምነት ተወካዮች ኅዳር 19 እና 20፤ 2016 ዓ.ም ለሁለት ቀናት በአዳማ ሲመክሩ የሰነበቱት ወቅታዊውን የሀገራችንን የሰላም ህመም መንስኤና መፍትሔው ምን እንደሆነ በመፈተሽ ነበር። በዋናነትም ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል አሳታፊ እንደሚሆን ተስፋ የተጣለበት ብሔራዊ የመመካከሪያው ውጥን በስፋት ተዘርግቶ የምንመኘለትንና የምንጓጓለትን "ጣፋጭ ፍሬ" በማዝመር ለብሔራዊ እፎይታችን የማያዳግም ፈወስ እንዲገኝ የየሃይማኖቱ ተቋማትና ቤተሰቦች ምን ድርሻና ሚና እንደሚጫወቱም በግልጽነት የተመከረበት ውሎ ነበር።

በሁለቱ ቀናት ቆይታ "በሀገራዊ ምክክር ከሃይማኖት ተቋማት ምን ይጠበቃል?" በሚል ርዕሰ ጉዳይ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር የሆኑት ዶ/ር ዮናስ አዳዬ የመጀመሪያውን የመወያያ ሃሳብ ካቀረቡ በኋላ በተከታታይም ለሀገራዊ የሰላም ጽናትና በምክክሩ ሂደት ከሃይማኖት ተቋማትና ከምእመናኑ ምን እንደሚጠበቅ ከሃይማኖታዊ መጻሕፍታቸው፣ ከግል ተሞክሯቸውና ከንባብ ትሩፋታቸው ካካበቱት ሰፊ እውቀት እየቀዱ ያስተማሩት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጠበብት ዘውገ አስራት እና ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት የፈትዋ ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ የሆኑት ሼኽ ሙሐመድዘይ ዛህረዲን ነበሩ።

ይህ አምደኛም "የሃይማኖት ቤተሰቦች የሰላማዊ የሚዲያ አጠቃቀምና የኮሚዩኒኬሽን ልምምድና ባህላቸውን ከፍ በማድረግ ለሀገራዊ ምክክሩ ላቅ ያለ ሚናቸውን ሊወጡ በሚያስችላቸው" ሰፋፊ ጽንሰ ሃሳቦች፣ ሀገራዊና ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች ላይ አጽንኦት በመስጠት በሦስተኛነት የጥናት ጽሑፉን አቅርቧል።

ጉባኤው ወትሮ ሲደረግ እንደኖረው በጸሎት ተከፍቶ የመንፈሳዊ ድባብ በሰፈነበት አኳኋን ተጀምሮ ብቻ የተደመደመ አልነበረም። "ስለምን ሀገራዊ ሰላማችን ሊታወክ ቻለ? እውክታውስ ስለምን ፋታ ነስቶን መፍትሔው እስከ መወሳሰብ ደረሰ? ከጅማሬውስ ቢሆን ለሰላሙ መደፍረስ ዋነኛ ሰበበ ምክንያቱ ማንና ምን ነበር?"

"ስለ ሰላም የሚሰብኩና የሚያስተምሩ የሃይማኖት ቤተሰቦችና የየቤተ እምነቱ መሪዎችና ምእመናንስ በዚህ ጥፋት ውስጥ ምን ድርሻ ነበራቸው? ውስብስብ ባህርይ ያለው የሰላም ርሃባችን ጠልቆ ሥር እስኪሰድ ድረስስ የሰላም ሰባኪያኑ ተቋማት ምን ሲሰሩ ነበር? ችግሮቹ ከተከሰቱ በኋላስ "የደጀ ሰላሞቹ" ባለቤቶች ምን ሙከራ አድርገዋል? ምንስ ባለማድረጋቸው ሊወቀሱ ይገባል? ወዘተ." በጉባኤተኛው የተጠየቁትና በጎርፍ ሊመሰሉ የሚችሉ አስተያየቶችና ሃሳቦች ነበሩ።

የጥያቄዎቹ ዓይነትም ሆነ የጠያቂዎቹ ቋንቋና ስሜት ከአሁን ቀደም ከነበረውና እንደ ባህል ተወስዶ ከዳበረው "የትህትናና የመሽኮርመም ልምምድ" በእጅጉ የተለየና ጠጠር ያለ ነበር። "ታሚል እየተባለ የሚወቀሰው አንካሳው ፖለቲካ ለጊዜው እዚያው በህመም አልጋው ላይ እያቀሰተ እንደ ቢጤቱ ይሁን ‹እኛ› ስመ ፈጣሪ ከአፋችን የማይለየው የየሃይማኖቱ ቤተሰቦች ምን እየሠራን ቆየን? ኢትዮጵያ ጨንቋት ስትቃትት በጸሎታችን ‹ይማርሽ!› እያልን ከመማለድ ውጭ እንደ ሀገር ዜጎች ምን መፍትሔ አመንጭተን ከህመሟ ለመፈወስ ግንባር ቀደም ነበርን? በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የሰላም መልእክተኛነታችንን ዋነኛ ተልእኳ ዘንግተን እንደሆነስ?"

"በዚህ ጉባኤ ላይ ስለ ሰላማችን ስብራት ተሰባስበን የምንወያየው ነገሮችን ሳንሸፋፍን ራሳችንን በፈጣሪ ፊት አራቁተን ስለሆነ ብርታታችንን በማወደስ ‹እንዲህ ነበርን! ነንም› በማለት ብቻ ሊሆን አይገባም። "ተሞክሯችን እንዲህ ነበር፣ የቅዱስ መጻሕፍቱ ትምህርትም እንዲህና እንዲያ ስለሚል..." ማለቱ መልካም ቢሆንም ከዚህ እልፍ ብለን ግን ራሳችንና ቤተ እምነቶቻችን ባልተወጡት ጉዳዮች ላይ ጨክነን ልንመክርበትና በጎ በጎውን ልንወስን ይገባል። "

"እውነት እውነቱን በመነጋገርና ችግሮቻችንን በማፍረጥ የመፍትሔው ቀዳሚ ምክንያት እንድንሆንም እንደ ሃይማኖታችን ቀኖና በንስሃ ወደ ፈጣሪ በመማለድ፣ እንደ ሀገር ልጅነታችንም በግላችን በመጸጸት ራሳችንን አጽደተን ለተግባር እርምጃ መጨከንና መረባረብ ይኖርብናል። " የሚሉት ሃሳቦች በየትምህርቶቹና በውይይቶቹ ክፍለ ጊዜያት ጎልተውና ከፍ ብለው የተደመጡ ‹አስገምጋሚ› ቁጭት የወለዳቸው ድምጾች ነበሩ።

"ራሳችንን ብንመረምር ባልተፈረደብን"

ምን ያህሉ የኢትዮጵያ ዜጋ በአንድም ይሁን በሌላ ጎራ ከአንድ ቤተ እምነት ተጠግቶ "ምእመን" የሚሰኝ ቅጽል እንዳተረፈ ለጊዜው የቅርብ ጊዜ "የሕዝብ ቆጠራ" ውጤት እጃችን ላይ ስለሌለ ይህን ያህል ለማለት ያዳግታል። አዘውትረው የሚጠቀሱ ግምታዊ አሀዞችን እንደ መነሻ እንውሰድ ከተባለ ግን ምናልባትም ከአጠቃላይ የሀገሪቱ ዜጎች ወደ 98% የሚጠጋው ሕዝባችን በየራሱ ዐውደ ምህረት ሥር ተጠልሎ "የእከሌ ቤተ እምነት ምእመን" እንደሚባል ደፍረን ለመናገር አፋችንን አይዘንም።

የሁሉም የሀገራችን ዋና ዋና ሃይማኖቶች ማዕከላዊ ትምህርት ከሰላም ጋር የተያያዘ መሆኑ ተደጋግሞ ተተርኳል። ክርስቶስ በምድር ላይ የኖረው ሰላምን ለሰው ልጆች እየሰበከ መሆኑ በየምስባኮቻችን ሳይሰበክ ውሎ ማደሩ ያጠራጥራል። የኢስላም መሠረታዊ አስተምህሮም እንዲሁ በሰላም ላይ የተመሠረተ ነው። የአይሁድ እምነትም ቢሆን የሚያስተምረው ያህዌ የሰላም ምንጭና አምላክ መሆኑን ነው።

እውነታውም ሆነ ሃይማኖታዊ ትምህርቶች ዋና ትኩረታቸው ይህን መሰሉ የሰላም ጉዳይ ከሆነና አብዛኛው ሕዝብ የሃይማኖቶቹ ቤተሰብ ነው ብለን የምንናገር ከሆነ ስለምን የሰላም ርሃብተኛ ልንሆን ቻልን? የችግሩ መንስኤስ ምንድን ነው? ችግር ፈጣሪውስ ማነው? ነባሩ ብሂላችን እንደሚያስተምረን የኢትዮጵያ ችግር፡- "ሀዘንሽ ቅጥ አጣ ከቤትሽ አልወጣ፤ የገደለው ባልሽ የሞተው ወንድምሽ" ይሉት ብጤ ሊሆን የቻለውስ ስለምንድን ነው?

ጦር ይዞ የሚፋለመውም ሆነ ጋሻ ወድሮ የሚመክተው ያው ከኢትዮጵያ ማህጸን ወጥቶ አንድም "የክርስትናን ስመ ጥምቀት የተቀዳጀ"፣ አንድም ሙስሊም ተብሎ "የተለየ"፣ አንድም አይሁድ ተብሎ "የተባረከ"፣ ወይንም በባህላዊ እምነት "የታቀፈ" ዜጋ እንጂ ባዕድ ወራሪ ሳይመጣብን ስለምን እርስ በእርስ ቃታ እየሳብን እንድንተላለቅ በራሳችን ፈረድን? እንዲህ ዓይነቱ መራራ ጥያቄ መጠየቅ ያለበት በገደምዳሜ ጎንዮሽ ሳይሆን ጨክነ ብለንና ደፍረን ራሳችንን በራሳችን ልንሞግትበት የሚገባ መራራ ሐቅ እንደሆነ በተጠቀሰው ጉባኤ ላይ በስፋት ተንጸባርቋል።

በጋራ ከሚጠቀሱት የየሃይማኖቶቹ ብርቱ አስተምህሮች መካከል አንዱ "እውነት ሳትድበሰበስ በፍቅርና በጥበብ መገለጥ ይገባታል" የሚለው አገላለጽ በየቅዱሳት መጻሕፍቱ ውስጥ የተሰመረበት በጉልህ "ቀለማት" ነው። እናስ "አጥፊን ገስጾ፤ ተጎጂን አጽናንቶ ወደ ሰላም ለማምጣት ቤተ እምነቶች ስለምን ጉልበታቸው ላላ? በምን ምክንያትስ አቅማቸው ዛለ? ይህ ጉዳይ በጉባኤተኞቹ ውይይት ላይ በተለያየ መልኩ ተደጋግሞ የተንሸራሸረ መሪ ሃሳብ ነበር።

ሌላውና በቁጭት ሲሰነዘር የነበረው "የማሕበራዊ ሚዲያ አጠቃቀምን" የተመለከተው ሃሳብ ነበር። በየማሕበራዊ ሚዲያዎች ላይ ጦርነት እየጫሩ ሕዝብን ለቁጣና ለበቀል የሚያነሳሱትን "አፋላሚ ፊት አውራሪዎች" ሕግ አውጥቻለሁ ያለው መንግሥታዊ ተቋም ስለምን ዝምታን መርጦ "በተው ቻለ ሆዴ" መርህ ሊረጋጋ ቻለ? የሚለው አስተያየት የቀረበው "የሚመለከተው" አካል ያስብበት በሚል ምክረ ሃሳብ ብቻ ሳይሆን "የሚመለከተው አካል ራሱ ግዴታውን ባለመወጣቱ ሊጠየቅ ይገባል" የሚል ውሳኔ በማሳለፍ ጭምር ነበር።

የብሔራዊ ምክክር አደረጃጀቱ ላይ የጎደለ ነገር እንደነበርም በግልጽ ተመክሮበታል። በጉባዔው ላይ መልእክት ላስተላለፉት ኮሚሽነርም በግልጽ ተነግሯቸዋል። ቀደም ሲል እንደተገለጸው ወደ መቶ ፐርሰንት የሚጠጋ ሕዝቧ በአንድም ይሁን በሌላ በየሃይማኖቱ ጥላ ሥር የተሰባሰበ ነው በሚባልባት ሀገር ኮሚሽነሮች ሲሾሙና ቢሮው ሲደራጅ "ሕገ መንግስቱን ከጨበጡ ብቻ ይበቃል" ከማለት ይልቅ ቅዱሳት መጻሕፍትን በልባቸውና በእጃቸው የያዙ መካሪና አስተማሪ አባቶች፣ በጸሎትና በዱዓ ደጋፊ ተወካይ መሪዎች ስለምን እንዲኖሩ አልታሰበም? የሚለውም ጥያቄ ተነስቶ ውይይት መደረጉ አልቀረም።

በተለይም የእርቅና የሰላም ጉዳይ ሲታወስ "የጥንቱን ዘመን አስታውስ፤ የብዙ ትውልድንም ዓመታት አስተውል፤ አባትህን ጠይቅ ያስታውቅህማል፤ ሽማግሌዎችህንም ጠይቅ ይነግሩህማል" (ዘዳግም 32፡7) የሚለው የቅዱስ መጽሐፍ እውነታ በምክክር ኮሚሽኑ አደረጃጀት ላይ ቢታወስ ኖሮ መልካም አልነበረምን? ይህስ ባለመደረጉ አልተጎዳንምን? ጥያቄዎቹ የተቋጨት ሌላ ጥያቄ አስከትለው ስለነበር ከዚህ በዘለለ ብዙ ለማለት ያዳግታል።

ብዙ ሃሳቦች የተንሸራሸሩበት የሃይማኖት ቤተሰቦቹ ጉባኤ የተጠናቀቀው በአንድ የጋራ ሃሳብ ላይ ተደርሶ ነበር። ያለፈው አልፏል፤ የሆነውም ሆኗል። የትናንቱ ጉዳትና ዘርፈ ብዙ ስብራት ለምን ተፈጸመ? ብሎ መቆዘሙ ብቻ ውጤት የለውም። በዋናነት ሊታሰብ የሚገባው ጉዳይ የዛሬው ህመምተኛ የሰላም ስብራት እንዲፈወስ የሃይማኖት ቤተሰቦች ምን ሚና ሊጫወቱ ይገባል? ነገስ የዛሬው አበሳ ጎልብቶና የከፋ አሳር ወልዶና ተዋልዶ ዝቀን የማንጨርሰው፣ ገፍተን የማናስወግደው መከራ እያሳጨደን እንዳይሰነብት ምን እርምጃ ሊወሰድ ይገባል? የሚሉት ጥያቄዎች ብዙ ተመክሮባቸዋል ተዝክሮባቸዋልም።

የሃይማኖት መሪዎች፣ መምህራንና የምእመናን እረኞች የሀገሪቱ ሰላም ተፈውሶ ሕዝቡ በሰላም ውሎ እንዲያድር በጸሎትም ሆነ በዱዓ፣ በጾምም ሆነ በእግዚአታ ሕዝባቸውን እያበረታቱና አብረውም ፈጣሪን እየተማጸኑ ከሚፈጽሙት መንፈሳዊ ኃላፊነትና ተጋድሎ ጎን ለጎን አጥፊዎችን ለመገሰጽ፣ እምቢተኞችን ለማለዘብና ግትር ሃሳብ ያላቸውን ለማብረድ ሥልጣነ ክህነታቸውን በአግባቡ ሊወጡ እንደሚገባ ጉባኤተኞቹ በአሜንታ ተስማምተዋል። ይህንኑ የአደራ መልእክትም ወክለው ለላኳቸው መሪዎቻቸው ለማድረስ በይሁንታ ፈቃደኝነታቸውን አረጋግጠዋል።

በዚህ አምደኛ ትኩረት የተሰጠበት የሚዲያ አጠቃቀም አቅርቦትም በተዋያዮቹ በስፋት ተመክሮበታል። ቢያንስ እያንዳንዱ ቤተ እምነት ለራሱ ምእመን በተለይም በሶሻል ሚዲያ አጠቃቀም ላይ ገንቢ እንጂ አፍራሽና አደፍራሽ መልእክቶችን ከማስተላለፍ እንዲታቀቡ በየመንፈሳዊ ጉባዔዎቻቸው ላይ በዘርፉ ባለሙያዎች ትምህርትና ምክር መሰጠቱ አግባብ እንደሆነ ተማምነውበታል።

በመጨረሻም፡- "በሰላም ስለ ሰላም እንመካከር!" በሚለው የማጠቃለያ ሃሳብ ላይ ሁሉም የጉባኤው ተሳታፊያን ስምምነታቸውን አረጋግጠው እንደተለመደው ለሀገራቸው ሰላም፤ ለሕዝባቸውም በጎ ፈቃድ ተመኝተው ስብሰባቸውን አጠናቀዋል።

> **የሃይማኖት መሪዎች፣ መምህራንና የምእመናን እረኞች የሀገሪቱ ሰላም ተፈውሶ ሕዝቡ በሰላም ውሎ እንዲያድር በጸሎትም ሆነ በዱዓ፣ በጾምም ሆነ በእግዚኦታ ሕዝባቸውን እያበረታቱና አብረውም ፈጣሪን እየተማጸኑ ከሚፈጽሙት መንፈሳዊ ኃላፊነትና ተጋድሎ ጎን ለጎን አጥፊዎችን ለመገሰጽ፣ እምቢተኞችን ለማለዘብና ግትር ሃሳብ ያላቸውን ለማብረድ ሥልጣነ ክህነታቸውን በአግባቡ ሊወጡ እንደሚገባ ጉባኤተኞቹ በአሜንታ ተስማምተዋል**

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተናጋሪው ዶሴ

# የባልንጀርነትን ገመድ የበጠሰ ወንጀል



**አስመረት ብስራት**

“ብረት ብረትን ይስለዋል፥ ሰውም ባልንጀራውን ይስላል።” የሚል አባባል መልካም ጓደኝነት ለመጥቀስ ጥቅም ላይ ይውላል። መልካም ጓደኝነት በዕጣ ወይም በሒሳብ ቀመር ተጠቅመን የምናገኘው ነገር ባይሆንም የራሱ የሆኑ መመዘኛዎች ግን ይኖሩታል፡፡ እውነተኛ ጓደኝነት እንደ ወርቅና አልማዝ ብር ነው፡፡

ጓደኞች የችግር ተካፋይ፣ የሐዘን አጋሮች፣ ተስፋ የቆረጠውን ተስፋውን የሚያለመልሙ፣ የወደቀውን የሚያነሡ ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከሞት ወደ ሕይወት የሚመልሱ በአጠቃላይ ከጎናችን ሆነው የሕይወት ስንክሣራችንን የሚጋሩ ጓደኞች ዋጋቸው ከወርቅም ከዕንቁም የበለጠ ነው፡፡ አብሮን የዋለ አብሮን ያደረ በተለያየ እንቅስቃሴያችን ውስጥ የምናገኘው ሰው ሁሉ የልብ ጓደኛችን ሊሆን አይችልም፤ ነገር ግን ከእነዚህ ሰዎች መሀል ሃሳቡ ከሃሳባችን፣ ዓላማው ከዓላማችን፣ ሕይወቱ ከሕይወታችን የሚገጣጠመው ብቻ ባልንጀራችን ይሆናል፡፡

የዛሬዎቹ ባለታሪኮቻችን የጓደኝነትን ልክ ከወሬም አልፈው በተግባር የሚኖሩ አብረው ውለው አብረው አምሽተው የሚገቡ ነበሩ። ብዙ ሰዎች በጓደኝነታቸው የሚቀኑባቸው፤ መተማመናቸው የበረታ የጓደኝነት ትስስራቸው የጠበቀ በአጠቃላይ መልካም ጓደኛ መገለጫ ለሌሎች ጥሩ የጓደኞች ምሳሌዎች ነበሩ፡፡

ጓደኝነትን የመሠረቱት ጥቅም ለማግኘት ሆን ብለው አስበው፣ በሸንገላ ከንፈር አንደበታቸውን በማጣፈጥ፣ ለታይታ አልነበረም። የልብ ጓደኝነት ነበራቸው። ጓደኝነታቸውም በዘር፣ በቋንቋ፣ በአንድ አካባቢ ተወላጅነት ላይ የተመሰረተም አልነበረም፡፡ የሁለቱ ጓደኝነት በፍፁም ፍቅር ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡

መልካም ጓደኛሞች ለችግር ጊዜ ደራሽ፣ በመከራ፣ በሐዘን፣ በደስታ ተካፋይ፣ አማካሪና፣ ገመናን ሸፋኝ የኔ ሰው ነው የሚባባሉም ነበሩ፡፡

በአብዛኛው የእረፍት ቀናቸውን አብረው ነው የሚያሳልፉት። ዛሬም በጠዋት ተገናኝተው ቁርሳቸውን አብረው ፍርፍር በልተው፤ እስከ ምሳ ሰዓት የጋራ ጓደኞቻቸው ከሆኑ ሴቶች ጋር ቆይተው አንደኛው የጥበቃ ሥራ ስለሚሰራ የሥራ መግቢያው ሲደርስ ተሰናብቷቸው ሄዷል።

በኋላም አመሻሽ ላይ መጠጥ መቀማመስ የፈለገው ጓደኛ ካለ መጠጡ ባልንጀራው ከጉሮሮው አልወርድ ቢለው ሥራ ከጨረስክ ና አብረን እናምሽ ብሎ ይጠረዋል።

ሀብቴ መዝገቡ የተባለው የፊኒሽንግ ሥራ ላይ የተሰማራው ወጣት ዓለሙ ታረቀኝ አምባው የተባለውንና በጥበቃ ሥራ የሚተዳደረውን ጓደኛውን ከጠራው በኋላ ሥራ የቆየው ዓለሙ ምግብ አዞ እራታቸውን አብረው በልተው ጃንቦ ድራፍት እየጠጡ ነበር ያመሹት።

መጠጡ ሲደጋገምና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የግንባታ ሥራ በመቀዛቀዙ የገቢያቸው መቀነስ ሆድ ስያስብሳቸውና ስለ ጉዳዩ ሲወያዩ ያመሻሉ። ከዛ ሀብቴ “አንተ የምትጠብቀው ያላለቅ ሕንፃ ላይ ሥራ መኖሩን እያወክ ሳትነግረኝ ቀረህ” ይለዋል። ዓለሙም ባለማስተዋል ችላ ያለው መሆኑን ነግሮት ይቅርታ ቢጠይቀውም ሀብቴ ግን በስድብና በዘለፋ ምቀኝነት ነው በማለት ቃላት ይወራወሩ ጀመር።

ከቃላት ምልልስ በኋላ ዓለሙ ሥራ ስላለው መሄድ እንደሚፈልግ ተናግሮ ወደ ደጅ ሲወጣ ሀብቴ ተከትሎት ከመሳደብ አልፎ ለድብድብ መጋበዝ ጀመረ። ትዕግስቱ የተሟጠጠው ጓደኛው መለስ ብሎ አንገቱን በማነቅ ይደባደቡ ጀመር።

ገላጋይ ገላግሏቸው ተንፈስ እንዳሉ ነበር ንዴቱን መቆጣጠር የተሳነው ዓለሙ ከመንገዱ ዳር የኮብል እስቶን አንስቶ ግንባሩ ላይ በኃይል የመታው። መጠጥ ያዳከመው ሀብቴም ድንጋዩ እንዳረፈበት ነበር ወደ ኋላው የወደቀው። ወደ ኋላም ሲወድቅ የተቀበለው የአስፓልት ጠርዝ የራስ ቅሉን ከፉኛ በመጉዳቱ የተነሳ ወዲያውኑ ሕይወቱ ሊያልፍ ቻለ።

**ወጣት ሀብቴ መዝገቡ**

ሰሜን ሸዋ አካባቢ ተወልዶ ያደገ ወጣት ነው። ሀብቴ ገና በአስራዎቹ አጋማሽ እድሜ ላይ ነበር ያገባው። በልጅነቱ የትዳር ዓለምን የተቀላቀለው ወጣት እርሻው ብዙም አልሳካለት ሲል ከባለቤቱ ጋር አዲስ አበባ ሄደን ያገኘነውን እንሥራ በማለት ከትውልድ ቀያቸው ወጡ። በትምህርት ብዙም የገፉ ስላልነበሩ ከጉልበት ሥራ በቀር ሌላ ሥራ ማግኘት አልቻሉም ነበር።

ከቀን ሠራተኝነት ተነስተው የፊኒሽንግ ሥራ ላይ ባለሙያ እስኪሆኑ ድረስ ለዓመታት ለፍተዋል። ያገኟትን አጠራቅመው ለወላጆቻቸው ገጠር ቤት ሰርተዋል። ከዚህ በኋላ ለራሳችን ጥሪት እንያዝ በማለት ለቤታቸው ደፋ ቀና ማለት በጀመሩበት ወቅት ነበር የግንበታ ሥራ መቀዛቀዝ የጀመረው።

ትንሽ ጥሪት ይዘን ልጅ እንወልዳለን በማለት በእቅድ የሚመሩት ባልና ሚስት የሥራ መጥፋት ሁኔታው ከእቅድ ውጭ ስላደረጋቸው ይበሰጫጩ ነበር።

በፍቅር ሲመሩት የነበረው ቤታቸው በውሃ ቀጠነ መበጥበጥ ጀመረች። ገና ከሀገራቸው መጥተው አዲስ አበባን እንደረገጡ የተዋወቁት ጓደኛቸው ዓለሙ ታረቀኝ መሀል እየገባ የነበረ ፍቅራቸው እንዲቀጥል ጥረት ያደርግ ነበር።

በእለቱም ማልደው በመገናኘት ብዙ ከተመካከሩ በኋላ የሀብቴ ባለቤትና ሌሎች አብረው ሆነው ሀብቴና ባለቤቱን በማስመማት ደግም ፀብ እንዳይኖር በመመካከር ነበር የዋሉት።

የጥበቃ ሥራ የሚሰራው ዓለሙም እነ ሀብቴን ተሰናብቶ ወደ ሥራው ሲሄድ የሀብቴ ባለቤትና ጓደኞቿ ወደቤት ተመለሱ። ሀብቴም ሥራ ፍለጋ ዞር ዞር ሲል ቆይቶ አመሻሽ ላይ አንድ መጠጥ ቤት በመግባት አንድ ሁለት ለማለት ቢሞክርም ከልብ ጓደኛው ተነጥሎ መጠጣት አልሆን ሲለው ደውሎ ይጠራውና አብረው ያመሻሉ። እንግዲህ ከሞቀታ በኋላ ነው ሆድ የባውን ብቅል ያወጣዋል ይሉት ነገር ተቀስቅሶ ጓደኛሞቹን ግጭት ውስጥ የከተታቸው።

**ወጣት ዓለሙ ታረቀኝ**

የወሎ ላስታ አካባቢ ተወላጅ ነው። ዓለሙ ታረቀኝ አምባው እድሜው ሃያ ሲሆን የትምህርቱ ደረጃ 6ኛ ክፍል እና ሥራውም ጥበቃ ነበር። ትሁት ለጓደኝነት ሟች የሚባል ዓይነት ሰው ነበር። በጣም የዋህ ከመሆኑ የተነሳ በትንሽ ነገር የሚከፋ በትንሽም ነገር የሚደሰት ዓይነት ሰው ነው።

ነገሮችን በዝምታ ለማለፍ የሚጥር ቢሆንም ታግሶ ታግሶ ሲበቃው ግን ማንም የማይዘው ያልታወቀ ዓይነት ባህሪ የሚያሳይ ቁጡ ሰው ሆኖ ይቀየራል። ለመናደድ ጊዜ የሚፈጅበት ይህ ወጣት ከንዴት ውስጥ ለመውጣትም ሲታገል መመልከት የተለመደ ነበር።

በእለቱም ከጓደኛው ጋር ባልረባ ነገር እሰጣ ገባ ውስጥ ቢገቡም ነገሩን ለማብረድ ደጋግሞ ይቅርታ ሲጠይቅ ነበር። ምንም እንኳን ጓደኛው ይቅርታውን ተቀብሎ ሊተወው ባይፈልግም ለሰላም ሲል ታግሶ ቆይቷል።

ከቆይታ በኋላ ግን ትእግስቱ ተጠናቀቀ፤ ንዴቱ ገንፍሎ ወጥቶ ከቁጥጥር ውጭ ሆነ። ያን ጊዜ ያለምንም መስፈርት በፍቅር ብቻ የመሰረቱት ጓደኝነት ተናደ። ገበና ከታቹ የልቤ ሰው የተባባሉት ጓደኞች የአንዱ ሕይወት በሌላው እጅ እንዲጠፋ ሆነ። ለታላቁ ባልንጀራነት ማብቂያው ወንጀል ሆነ።

**ፖሊስ**

ምሽቱን ከደስታ ወደ ሀዘን የቀየረው አጋጣሚ እንደተፈጠረ ነበር የፀጥታ ኃይሎች በቦታው የደረሱት። እጅግ አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ፊቱ በሙሉ በደም የተሸፈነውን ወጣትና ፤ በንዴት ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ ነፍስ ያጠፋውን ባልንጀራውን ፊት ለፊት ተፋጠው ያገኟቸዋል። ያኔ አንዱን ወደ ሆስፒታል አንዱን ደግሞ ወደ ፖሊስ ጣቢያ በመውሰድ ምርመራቸውን ይጀምራሉ።

**የእምነት ክህደት ቃል**

‹‹እኔና ሟች ሀብቴ መዝገቡ የረጅም ጊዜ ጓደኛሞች ነን። በእለቱም ከባለቤቱ ጋር ተጋጭተው ስለነበር ለመመካከር በሚል በጠዋት ነበር የተገናኘነው። የተገናኘንበት ሻይ ቤት ቁርስ ፍርፍር አብረን በልተን ሁለታችንም ሥራ ስላልነበረን አብረን ቁጭ ብለን እስከ ስድስት ሰዓት የሟች ባለቤትና ለሎች በጋራ ከምናውቃቸው ሴቶች ጋር ስንጫወት ነበር የቆየነው።

ከዛ በኋላ ተለያይተን ከቆየን በኋላ ሟች ደወሎ የት ነው ያለኸው አብረን እንጠጣ ብሎ ስሄድ ድራፍት እየጠጣ አገኘሁት። እኔ ስደርስ ምግብ አዘዝኩና አብረን ምግብ ከበላን በኋላ ድራፍት ጠጣን። እኔ ጥበቃ ስለሆንኩ ልሂድ ሥራ አለኝ ብዬ ተነሳሁ።

ከዛ በድርጅታቸሁ ሥራ እያለ ለምን አልነገርከኝም በማለት መቆጣት ጀመረ፤ ሥራው የፊኒሽንግ ሥራ ስለነበር ባለማስተዋል ለጓደኛዬ ስላልነገርኩት ተጸጽቼ ይቅርታ ጠየኩት። ቢሆንም ግን እሱ እየተናደደ ሲናገር አንድ አንድ ስንባባል ቆይተን ተጣላን፤ ተያይዘን መደባደብ ጀመርን፡፡ ከዛ ዞር ብዬ ድንጋይ በማንሳት ግንባሩን ስለው ወደኋላ ስለወደቀ አስፓልቱ መቶት ሊሞት ችሏል።›› በማለት ተጠርጣሪውም በወንጀል ምርመራ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 127(2) መሠረት የወንጀል ድርጊቱን መፈፀሙን ለፖሊስ የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቷል።

**የፎረንሲክ ምርመራ**

አስክሬኑ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊንየም ሜዲካል ኮሌጅ የፎረንሲክ ሜዲስንና ቶክሲድ ትምህርት ክፍል በመሄድ ምርመራ የተደረገለት ሲሆን በቁጥር ጳሆ 8/3257 በቀን 18/06/14 በሟች ሀብቱ መዝገቡ የተሰጠው የአስክሬን ምርመራ እራስ ቅሉ ላይ በደረሰው ጉዳት መሞቱን የሚያስረዳ መረጃ ለፖሊስ ቀርቧል።

ፖሊስም የሰው ምስክሮችን፤ የተከሳሽ የእምነት ክህደት ቃልንና የሰነድ ማስረጃ ማለትም የፎረንሲክ ምርመራውን በማጠናቀር ለፌዴራል አቃቤ ሕግ ልኳል።

**የፌዴራል አቃቤ ሕግ ክስ**

ከሳሽ የፌዴራል አቃቤ ሕግ፤ ተከሳሽ ዓለሙ ታረቀኝ አምባው እድሜ 20 አድራሻ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር አዲስ ወንጀሉ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 540 ስር የተደነገገውን መተላለፍ ሲሆን የወንጀሉ ዝርዝር በዚህ መልኩ ቀርቧል።

የወንጀሉ ዝርዝር ተከሳሽ ሰውን ለመግደል በማሰብ በቀን 30/05/14 ከምሽቱ በአራት ሰዓት አካባቢ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ልዩ ቦታው ኮዬ ፈጬ ፕሮጀከት ቢ ተብሎ የሚጠራው ቦታ ላይ ሟችን ግንባሩ ላይ አንድ ጊዜ ወርውሮ በመምታት በራስ ቅሉ ላይ በደረሰው ጉዳት ምክንያት ሕይወቱ እንዲያልፍ ያደረገ በመሆኑ በፈፀመው ተራ ሰው የመግደል ወንጀል ተከሷል።

**ውሳኔ**

ተከሳሽ ዓለሙ ታረቀኝ የተከሰሱበት ተራ ሰው የመግደል ወንጀል በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ በ24/8/15 በዋለው ችሎት ክስና ማስረጃውን ከሕግ ጋር አገናዝቦ በሰጠው ውሳኔ መሠረት በ10 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል።

ለታሪኩ መነሻ ሃሳብ እንድናገኝ የተባበሩን የአዲስ አበባ ፖሊስ የመዝገብ ቤት አባላትን በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ወጣቱ የተለከፈበት አዲስ ሱስ!

ሚዛን

በስፖርት ውድድሮች ውጤት ላይ ተመስርቶ መወራረድ(ቢቲንግ) መነሻው ከጥንታዊ ሮማውያን ጋር እንደሚያያዝ የታሪክ ሰነዶች ላይ ሰፍሮ ይገኛል። ጥንታዊ ሮማውያን በሠረገላ ውድድር እና በግላዲያተሮች መካከል በሚደረጉ ግጥሚያዎች ላይ ውርርድ በማድረግ እንደጀመሩትም ይታመናል። ይህም በጊዜ ሂደት እያደገ መጥቶ በ19ኛው ክፍለ ዘመን በአውሮፓ የነበረው የእግር ኳስ እድገት አሁን የምናየውን የእግር ኳስ ውርርድ ወልዷል።

ከጥቂት ዓመታት በፊት ቢቲንግ በኢትዮጵያ እምብዛም የተለመደ ነገር አልነበረም። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን እንደ አሸን እየፈሉ የሚገኙ የስፖርት አወራራጅ ድርጅቶች የብዙ ወጣቶችን ቀልብ መሳባቸውን ቀጥለዋል። አቋማሪ ድርጅቶች መጀመሪያ አካባቢ ወደ ኢትዮጵያ መግባት እንደጀመሩ ከሕግ ጋር የተያያዙ በርካታ ውዝግቦች ተነስተው ዛሬም ድረስ መቋጫ አላገኙም። ያም ሆኖ በተለያዩ ከተሞች ሱቆች ጭምር እየተዘጉ በአንድ አዳር የቢቲንግ መቆመሪያ መሆናቸውን ቀጥለዋል። በአስገራሚ ፍጥነትም ቀደም ሲል የቢቲንግ ሰለባ የሆኑት ወጣቶች ቢሆኑም አሁን አሁን ያገኙትን ቋጥረው አቋማሪ ድርጅቶች በር ላይ አዛውንቶች ሳይቀሩ ሰልፍ ይዘው መታየታቸው ነው። ከተማሪ እስከ ፖሊስ ድረስም ችግሩ እንደዘለቀ እየተመለከትን ነው። ሰሞኑን የሃይማኖት አባት እንኳን ሰው አየኝ አላየኝ ሳይሉ የቁማሩን ትኬት ቆርጠው ከአንዱ አቋማሪ ድርጅት ሲወጡ የሚያሳይ ተንቀሳቃሽ ምስል በማህበራዊ ድረ ገፆች ተሰራጭቶ መነጋገሪያ መሆኑ ችግሩ ምን ያህል ስር እንደሰደደ ማሳያ እስከ መሆን ደርሷል።

በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 789 መሠረት ሎተሪዎችንና ውርርዶችን የሚመለከቱ ሕጎችን መጣስ አስመልክቶ "ውርርድ ፈቃድ ኖራቸውም አልኖራቸውም ማድረግ የተከለከለ እንደሆነ ያስቀምጣል"። ለመሰብሰቢያ በተዘጋጀ ስፍራ የቁማር ጨዋታ ወይንም ውርርዶችን ወይንም በመንግሥት ክልከላ የተደረገባቸው ሌሎች የዕድል ጨዋታዎችን ከልክሏል። በዚህም ቢቲንግ ወይንም የስፖርት ውርርድ ማድረግ እንደማይቻል ሕጉ አስቀምጧል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ እየተስፋፋ የመጣው የስፖርት ውርርድ (ቢቲንግ) ወጣቱን ኪሳራ ውስጥ እየጣለው እንደሚገኝ እየታየ ዝምታው ቀጥሏል።

ብሔራዊ ሎተሪ የስፖርት ውርርድ እንጂ ቁማር ስላልሆነ ፈቃድ ሰጥቻለሁ፤ እንደውም ለበርካቶች የሥራ እድል ፈጥሯል ይላል። የሕግ ባለሙያዎች "ውርርድ" በሚል ሽፋን ስሙን ለውጦ የመጣው ‹‹ቁማር›› ነው፤ እየተሰጠ ያለው ፈቃድም የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን የጣሰ ነው ሲሉ ይሞግታሉ። "በግምት ብቻ በአጭር ጊዜ በቀላሉ ሕይወትዎን የሚቀይሩበት ታላቁ ዘዴ" በሚል ማስታወቂያ ተስቦ ወደ ጨዋታው እየገባ የሚገኘውን ሕዝብ ቤቱ ይቁጠረው።

ለጨዋታው ህጋዊ ፈቃድ የሚሰጠው ብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ፤ የስፖርት ውርርድ ቁማር ባለመሆኑ ፈቃድ መስጠቱን ደጋግሞ ተናግሯል። ይህ የስፖርት ውርርድ ሎተሪ በመሆኑ በብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ማቋቋሚያ አዋጅ 135/1999 በመመሪያ 83/2005 መሠረት የሚሰጥ የፈቃድ እንደሆነም ተከራክሮበታል። በመመሪያውም ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ታዳጊዎች ውርርዱን ማድረግ እንደማይችሉ ስለፀደቀ ቤቶቹ ይህንን መሠረት አድርገው ይሠራሉ ነው የሚለው።

በአሁኑ ወቅት ይህ ጨዋታ እየተስፋፋና ገበያው እየሰፋ ሕብረተሰቡም እየተሳተፈበት በመሆኑም ከሰላሳ በላይ ድርጅቶች ፈቃድ ተሰጥቷል። በዚህም መንግሥት ከድርጅቶቹ በአማካይ በየወሩ እስከ ስድስት ሚሊየን ብር ገቢ እንደሚያገኝ መረጃዎች ይጠቁማሉ። አቋማሪ ድርጅቶቹ ካገኙት ትርፍ ላይ 20 በመቶ የሚሆነውን ሥራውን ሲጀምሩ ለተዋዋሉት በጎ አድራጎት ድርጅት ገቢ ለማድረግ መገደዳቸው እንደ አንድ ማምለጫ ተደርጎ ተቆጥሯል። ድርጅቶቹ ከአንድ ሺህ 200 ዜጎች በላይ የሥራ ዕድል እንደተፈጠሩና ከጉዳቱ ጠቀሜታው እንደሚያመዝን በመግለጽ ቅሬታ አቅራቢዎቹ የሚያነሱት ሃሳብ ውድቅ ይደረጋል።

ከዚህ በተጨማሪ የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ከድርጅቶቹ ገቢ 15 በመቶውን በኮሚሽን መልክ የሚወስድ ሲሆን ድርጅቶቹ ከደንበኞቻቸው ግብር ሰብስበውም ለመንግሥት ገቢ ያደርጋሉ። በተጨማሪ ዓመታዊ የግብር ግዴታቸውንም ይከፍላሉ።

የሕግ ባለሙያዎች ግን በተለምዶ ውርርድ በሚል ሽፋን ስሙን ለውጦ የመጣው ‹‹ቁማር›› ነው ይላሉ። ቁማር ማለት በአነስተኛ የገንዘብ ወጪ አንድን ያልተገባ ነገር ለማግኘት ማሰብ ነው የሚሉት ሞጋቾች፤ ውርርዱ የስፖርት ጨዋታዎችን በመገመት ግምቱ ትክክለኛ ከሆነ የሚገኝ ገንዘብ እንደመሆኑ ያልተገባ ክፍያ ለመውሰድ የሚደረግ ጥረት ውርርድ ወይንም ቁማር መሆኑን ያስረዳሉ።

"ውርርድ ፈቃድ ኖራቸውም አልኖራቸውም ማድረግ የተከለከለ እንደሆነ ያስቀምጣል"። ለመሰብሰቢያ በተዘጋጀ ስፍራ የቁማር ጨዋታ ወይንም ውርርዶችን ወይንም በመንግሥት ክልከላ የተደረገባቸው ሌሎች የዕድል ጨዋታዎችን ከልክሏል። በዚህም ቢቲንግ ወይንም የስፖርት ውርርድ ማድረግ እንደማይቻል ሕጉ አስቀምጧል።

በሕግ አተረጓጎምም አዋጅ ደንብ ቀጥሎም መመሪያ ነው ፤ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ አዋጅ በመሆኑ ማንኛውም ይህንን የሚጣረስ መመሪያ ተገቢነትም ሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም። ስለሆነም ፈቃድ ሰጪው አካል በምን አግባብ እንደሰጠ መመርመር ይገባል የሚሉ የማህበረሰብ ተቆርቋሪዎች ዛሬም ድምፃቸው አልተሰማም።

በስፖርታዊ ውድድሮች ገንዘባቸውን ለማስያዝ የሳምንቱ መጨረሻ ቀናትን በጉጉት የሚጠብቁ ጥቂት አይደሉም። የትምህርት ወጪያቸውን የተበሉ፣ ደመወዛቸውን አስረክበው በራሳቸውና በቤተሰባቸው ላይ ሌላ ጣጣ የመዘዙም እንዳሉ በተለያዩ አጋጣሚዎች ወሬው ተሰምቷል። እንደ ሀገር የጉዳዩን አሳሳቢነት ምን ደረጃ እንደደረሰ ጥናት የሚያደርግ ቢኖር ቢቲንግ እየፈጠረ የሚገኘው ማህበራዊ ቀውስ ከዚህም ልቆ ሊገኝ ይችላል።

በስፖርታዊ ውድድሮች መወራረድ ጋር አብሮ የሚነሳ አንድ ችግር አለ። እሱም እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ታዳጊዎችና ተማሪዎች በዚሁ ተግባር ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን ሊያጠፉ መቻላቸው ነው። አብዛኛዎቹ አወራራጅ ድርጅቶች ለመወራረድ ከሚመጡት ሰዎች መካከል ምን ያህሉ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች መሆኑን እንደማይቆጣጠሩ ዞር ዞር ብሎ መቃኘት በቂ ነው። አንድ ተማሪ ዩኒፎርም እስካለበሰ ድረስ ለመቋመር ደጅ ቢጠና እድሜህ ስንት ነው የሚለው የለም።

"በስፖርት ውድድሮች ይሄኛው ቡድን ያሸንፋል ሌላኛው ይሸነፋል እያሉ መወራረድ የተለመደና ሁሌም የነበረ ነገር ነው" የሚሉ ግን አይጠፉም። እንዲህ ዓይነት ክርክሮችን የሚያነሱ ሰዎች የስፖርት ውርርድ ድርጅቶች ተገቢውን ቅድመ ሁኔታዎች እስካሟሉ ድረስ ማህበረሰቡ ላይ የሚያሳድሩት ጫና እንደሌለ ይናገራሉ። ስለዚህም ቢቲንግ ቁማር አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል። ቁማር ሲሆን አንዱ የሚጎዳበት አንዱ ብቻ ደግሞ የሚጠቀምበት ነው። የስፖርት ውርርድ ባህሪው የሎተሪ ነው። ማህበረሰቡ በተለይም ወጣቶች ጊዜያቸውን በሌሎች ነገሮች ላይ ከሚያሳልፉ እየተዝናኑ እድላቸውን የሚሞክሩበት ነው የሚለው በብሔራዊ ሎተሪ ጭምር ድጋፍ ያለው እሳቤ ወጣቱን በዘመን አመጣሹ አዲስ ሱስ ተዘፍቆ እንዲቀር ትልቁን ሚና እየተጫወተ ነው።

የስፖርታዊ ውድድሮች ላይ የሚደረግ ውርርድ ዙሪያ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ታዳጊዎችን ድርጅቶቹ እንዳያጫውቱ የሚከለክል መመሪያ የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ባይኖረውም ውርርዱ ላይ ሕጻናት እንዳይሳተፉ ስምምነት አላቸው፣ ተግባራዊነቱን ግን ለመጠርጠር ከበቂ በላይ ምክንያት አለ።

ውርርድ ሱስ የማስያዝ ባህሪ ሊኖረው ስለሚችል ወደፊት የዘርፉን አካሄድ በመመልከትና ተያይዘው የሚመጡ ሌሎች ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢውን ርምጃ መውሰድ የግድ ነው። ከስፖርታዊ ውርርዶች ጋር በተያያዘ ከፍተኛ የወጣቶች ሥራ አጥነት፣ ለስፖርታዊ ውድድሮች ያለ ከፍተኛ ፍቅር፣ የላላ የቁማር ሕግና ቀላል የተንቀሳቃሽ ስልክ ክፍያ መንገዶች መብዛት እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ታዳጊ ሀገራት ትልቅ ፈተና ሊደቅኑ እንደሚችሉ ግን ማስታወስ ተገቢ ይሆናል።

# ዓለም አቀፍ

## ተመድ በሶማሊያ ላይ የጣለውን ለ30 ዓመታት የዘለቀ ማዕቀብ ሊያነሳ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

የተመድ የጸጥታው ም/ቤት በሶማሊያ ላይ የጣለውን ለ30 ዓመታት የዘለቀውን ማዕቀብ ለማንሳት ድምጽ ሊሰጥ ነው።

የተመድ የጸጥታው ምክር ቤት ለሶማሊያ መንግሥት እና የጸጥታ ኃይሎቹ የጦር መሳሪያ እንዳይሰጥ የሚከለክለውን ማዕቀብ ለማንሳት ድምጽ እንደሚሰጥ ሮይተርስ ዘግቧል።

የጸጥታው ም/ቤት በፈረንጆቹ 1992 በሶሚሊያ ላይ የጦር መሳሪያ ማዕቀብ የጣለው፣ የሀገሪቱን መሪ መሀመድ ሲያድ ባሬን ያስወገዱት ተቀናቃኝ ታጣቂዎች መሳሪያ እንዳይደርሳቸው ለማድረግ ነበር።



ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼህ መሀሙድ

15 አባላት ያሉት የጸጥታው ምክር ቤት በእንግሊዝ የቀረቡለትን ሁለት የውሳኔ ሃሳቦች ያጸድቃል ተብሎ ይጠበቃል።

በሶማሊያ ላይ ተጥሎ የነበረው ሁሉም ዓይነት የጦር መሳሪያ ማዕቀብ እንዲነሳ እና በአልሸባብ ላይ የጦር መሳሪያ ማዕቀብ እንዲጣል የሚሉ የውሳኔ ሃሳቦች ናቸው በእንግሊዝ የቀረቡት።

በሶማሊያ መንግሥት ላይ ምንም ዓይነት የጦር መሳሪያ ማዕቀብ መኖር እንደሌለበት በአንደኛው ረቂቅ የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተጠቅሷል።

በሀገሪቱ ደህንነቱ የተጠበቀ የመሳሪያ ማከማቻ ቦታ ቁጥር ላይ ስጋቱን የገለጸው የውሳኔ ሃሳቡ ግንባታ እንዲደረግ እና ሌሎች ሀገራት ርዳታ እንዲያደርጉ ጠይቋል።

ሶማሊያን በእስላማዊ የሼሪአ ሕግ ለማስተዳደር የሚፈልገው አልሸባብ ከፈረንጆቹ 2006 ጀምሮ ደምአፋሳሽ ግጭት ውስጥ ከቷታል።

የሶማሊያ መንግሥት ማዕቀቡ እንዲነሳለት ለረጅም ጊዜ ሲጠይቅ ቆይቷል።

የጸጥታው ም/ቤትም ከ2013 ጀምሮ ማዕቀቡን በከፊል ማንሳት ጀምሯል።

የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼህ መሀመድ ባለፈው ሳምንት እንደተናገሩት ሶማሊያ የአፍሪካ ህብረት ሰላም አስከባሪ ከሚወጣበት በፊት አልሸባብን ለማጥፋት አንድ ዓመት ብቻ ነው የቀራት ሲሉ ተናግረዋል።

## አረብ ኢምሬትስ ለአየር ንብረት መፍትሔዎች የ30 ቢሊዮን ዶላር ፈንድ አቋቋመች

በጋዜጣው ሪፖርተር

የአረብ ኢምሬትስ ፕሬዚዳንት ሼክ ሞሃመድ ቢን ዛይድ ሀገራቸው ለአየር ንብረት ለውጥ መፍትሔዎች የ30 ቢሊዮን ዶላር ፈንድ ማቋቋሟን አስታወቁ።

ሼክ ሞሃመድ ቢን ዛይድ ይህንን ያሉት 28ኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባዔ (ኮፕ28) በመሪዎች ደረጃ ሲከፈት ባደረጉት ንግግር ነው።

በዚሁ ወቅትም ሼክ ሞሃመድ ቢን ዛይድ አል ናህንያን ለአየር ንብረት መፍትሔዎች ፈንድ የተቋቋመው የአየር ንብረት ፋይናንስ ክፍተቱን ለመሙላትና እና ገንዘቡ በተገቢው መልኩ ተደራሽነቱን ለማመቻቸት ነው ብለዋል።

ሼክ ሞሃመድ ቢን ዛይድ አክለውም የገንዘብ እጥረት በዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ርምጃዎች ላይ ትልቁ እንቅፋት መሆኑንም አብራርተዋል።

አረብ ኢምሬትስ በታዳሽ እና ንጹህ የኃይል ምንጭ መጠቅሟ ላይ ትኩረት እንደምታደርግም ፕሬዚዳንቱ አስታውቀዋል።

በዚሁ ወቅትም ሼክ ሞሃመድ ቢን ዛይድ አረብ ኢምሬትስ በቀጣይ 7 ዓመታት ውስጥ ለአየር ንብረት ለውጥ ርምጃ በታዳሽ እና ንጹህ የኃይል ምንጭ ዘርፍ ተጨማሪ 130 ቢሊየን ዶላር ኢንቨስት እንደምታደርግም አስታውቀዋል።

የተመድ ዋና ፀሐፊው በኮፕ28 ጉባኤ ባደረጉት ንግግር፥ የአየር ንብረት ለውጥ ከአንታርቲካ እስከ ኔፓል ጉልህ ተጽዕኖውን እያሳየ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

"ከፍተኛው የዓለም የሙቀት መጠን በዚህ ዓመት ተመዝግቧል፤ ወደ ከባቢ አየር የተለቀቀው ካርበንም ከፍተኛው ነው፤ ድርቅና ጎርፉም እየተባባሰ ሄዷል" ያሉት አንቶኒዮ ጉቴሬዝ፥ በፓሪስ የተደረሰውን ስምምነት መፈጸም አለመቻሉ ፈተናውን እያከበደው መሄዱን አብራርተዋል።

በመሪዎች ደረጃ የሚካሄደው 28ኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባዔ ዛሬ



መካሄድ የጀመረ ሲሆን፤ እስከ ነገ ይቀጥላል።

በዚሁ የመሪዎች ጉባዔ ላይ የ137 ሀገራት እና መንግሥታት መሪዎች ንግግር እንደሚያደርጉም የወጣው መርሃ ግብር ያመለክታል ሲል የዘገበው አል ዓይን ነው።

# ራስን መሆን

አስናቀ ፀጋዬ

መቼም በዚህ ምድር ላይ ራስን እንደመሆን የሚያስደስት ነገር የለም። የብዙ ሰዎች ችግር ግን ራስን አለመሆን ነው። ራስን መሆን ቢያቅት እንኳን ራስን ለመሆን የሚደረግ ብርቱ ጥረት በብዙ ሰዎች ዘንድ አይታይም። ብዙዎችም ራስን ከመሆን ይልቅ ሌላውን መምሰል የሚፈልጉት በደፈናው ነው። ራስን ከመሆን ይልቅ ሌላውን ለመምሰል የሚደረገው ጥረትም ቢያንስ ያ ሰው እንዴት ራሱን መሆን እንደቻለና የራሱን ስብእና እንደገነባ ጥያቄ ውስጥ ባስገባ መልኩም አይደለም።

ስለዚህ አንተም ‹‹እኔስ መቼ ነው እንደራሴ የምሆነው? እንደልቤ የአዕምሮ ነፃነት ኖሮኝ ሕይወቴን እንደፈለኩ የምመራው እንዴት ነው? መቼ ነው ሰዎች ምን ይሉኝ ይሆን፣ ሰዎች ስለኔ ምን ያስባሉ የሚለውን የማቆመው?›› እያልክ ይሆናል። ያንተን መኪና የሚነዳው ማነው? ቤተሰብ ነው? ጓኛህ ነው? ወይስ በዙሪያህ ያለ ሰው ነው? በርግጥ መኪና ለሁለት አይነዳም። መኪና ማለት ሕይወትህ ነው። ሕይወትህን ለሁለት የምትመራው ከሆነ፣ በሌሎች አስተሳሰብ የምትመራው ከሆነ ወደ ገደል ነው የምትገባው።

ስለዚህ በአንተ ሕይወት የሚያዘው ማነው? ገንዘብህንና ጉልበትህን የሚያዝበት ማነው? አንተና ፈጣሪህ ካላዘዛችሁበት ሰዎች እንደጥላ ናቸው፤ ፀሐይ ሲገባ ይሰወራሉ። አንተ ስትደምቅና ሲኖርህ ነው የሚከተሉህ። ከሌለህ አጠገብህ ማንም የለም። ስለዚህ በራስህ ላይ አንተ ራስህ እዘዝበት። ራስህን ሁን። እንዴት? ካልክ ጥሩ ጥያቄ አንስተሃል። እነሆ መልሱ።

ሰዎች የሚወዱህ ጥንካሬ አስካለህ ድረስ ብቻ ነው። ምን ይሉሃል መሰለህ? እሱ እኮ ያመነበትን ነው የሚያደረርገው ይሉሃል። ለምን? ስትጠነክር፤ ራስህ ላይ ስታተኩር ሁሉም ያከብሩሃል። ባይወዱህ እንኳን በልባቸው እነርሱም እንዳንተ መሆን ይፈልጋሉ። ለራስህ ቅድሚያ ስጥ። እሳቱ ላይ የምትጣደው እኮ አንተ ነህ። ምንም ቢሆን ብትታመም፣ ችግር ቢደርስብህና ብትከስር ቤተሰብና ጓኛህ አይዞህ ሊልህ ይችላል እንጂ ሕመምህን አብሮ አይታመምም። አብሮህ ገደል አይገባም። ግን አይዞህ ይልሃል። እንዴ! ሬሳ መቃብር ሲገባ አብሮ የተቀበረ ሰው አይታችሁ ታውቃላችሁ? ማንም አብሮ አልተቀበረም። ይሸኛል እንጂ አብሮ ማንም የሚቀበር ሰው የለም። የሞተ ሰው ከትንሽ ጊዜ በኋላ ይረሳል።

ስለዚህ ለራስህ መኖር መጀመር አለብህ። ለራስህ የምትሰጠውን ቦታ መቀየር አለብህ። ቅድሚያ ለራስህ ስጥ። የምታደርገውን ነገር ታምንበታለህ? ለሕይወትህ በጣም ወሳኝ ነው? አንተ ካመንክበት ሌሎች ምንስ ቢሉህ! አላማህን ካላወክ ግን ሰዎች ይነዱሃል። ወደፈለጉበት አቅጣጫ ይመሩሃል። በቃ ስላንተ አያስቡም። ዞር ብለው አያዩህም። አየህ! ሰዎች የሚወዱህ ጥንካሬህን አይተው ነው። ምን ዓይነት ጎበዝ ነው፣ ምን ዓይነት ደፋር ነው ሲሉ ይሰይሙሃል፣ ያከብሩሃል፣ ለራስህ የምትሰጠውን ቦታ ያዩና እነሱም መልሰው አንተን ያከብሩሃል። ያመንክበትን እንድታደርግ እድል ይሰጡሃል። አንተ ግን ለራስህ የምትሰጠው ቦታ መቀየር ይኖርበታል።

በጣም ታዋቂው ባለሀብት ቢል ጌትስ ‹‹ራስህን መናቅ የጀመርከው ከሰዎች ጋር መወዳደር ስትጀምር ነው›› ይላል። ለማን ብለህ ነው ራስህን የምታወዳድረው? ራስህን እንዳትንቀው። ካወዳደርከው ራስህን እየናከው ነው። አንተ እኮ ትልቅ ህልም ነው ያለህ፤ ትልቅ ፍላጎት ነው ያለህ። ጊዜያዊ ነገር እያየህ እኔ እኮ ከእሱ አንሻለሁ ወይም ከእሱ በልጫለሁ አትበል። ትልቅ ህልም ካለህ መወዳደር ላንተ አይገባም። ላንተ ማንንም ማነፃፀር የለብህም። ሕይወትህን ከራስህ አንፃር ቃኘው። ከራስህ አንፃር እየው። ትልቅ ህልም ካለህ ራስህን በፍፁም ከሰዎች ጋር አታነፃፀር።

ራስህን ማነፃፀር አቁም! ይህን ካደረክ በፍፁም ሰላም አይኖርህም። ከሰዎች ጋር ሕይወትን እያወዳደርክ ልትደሰት አትሞክር። ብትበልጣቸው ራሱ ገና መቼ መጥተው በለጡኝ ብለህ ስትሰጋ ነው የምትኖረው። ሲበልጡህ ደግሞ መቼ ነው የምበልጣቸው ብለህ ትጨነቃለህ። ውድድርና ንፅፅር ውስጥ ከገባህ ያ ሰው ምን ያስባል ምን ያደርጋል ብለህ የሰው ኑሮና ውድድር ውስጥ ነው የምትገባው። ለማን ብለህ ነው ታዲያ ራስህን የምታወዳድረው?

ሰዎችን ማስደሰት አቁም! ሁሉንም ማስደሰት አትችልም። መጀመሪያ ራስህን አስደስት። ከዚህ በተቃራኒ ግን ሁሉንም ሰዎችን አስደስታለሁ ብለህ ስትጋጋጥ እነሱ ብቻ ሳይሆኑ አንተ ራሱ መደሰት ታቆማለህ። ሀዘንተኛ ትሆናለህ። ባዶ እጅህን ትቀራለህ። መጀመሪያ አንተ በሕይወትህ ተደሰትበት።



**አንተ ድንቅ እንደሆንክ መጀመሪያ ለራስህ ንገረው። ከዛ ማመን ጀምር። በሂደት ድርጊቶችህ ይቀየራሉ። ማንነትህ የድንቅ ሰዎች ብቻ ይሆናል። አስታውስ! የትኛውም ስኬታማ ሰው በሰዎች ከመደነቁ በፊት ራሱን ያደንቅ ነበር**

ሁሉንም ስለማስደሰት አታስብ። ራስህን የማትሆነው እኮ ለዛ ነው። እንዲህ ባደርግ ሰዎች ያዝኑብኝ ይሆን? ይከፋ ይሆን? ስትል መቼም ደስተኛ አትሆንም። ሕይወት ትከብድሃለች። ለምን? አንተ ለሰዎች ደስታ መስዋትነት እየከፈልክ ነዋ! ነገር ግን አንድ ነገር አትርሳ። ለምትወዳቸው ስትል የምትከፍለው መስዋትነት ድንበር ያስፈልገዋል። ‹‹በቃ! ከዚህ በላይ ዋጋ አልከፍልም›› ማለት አለብህ። ‹‹ለራሴ ነው ዋጋ የምከፍለው፤ ለራሴ ነው የሆነ ነገር የማደርገው›› ብለህ ራስህን ማስቀደም አለብህ።

እንደውም ይህ የማደግ ምልክት ነው። ከፍ ስትል ዓይን ውስጥ ትገባለህ። ‹‹ሰዎች ምንድን ነው እሱ›› ይሉሃል። ይበሉህ! ችግር የለውም ከፍ ባልክ ቁጥር እነሱን ማስደሰት አይጠበቅብህም። ሊጠሉህም ይችላሉ። ይጥሉህ! ችግር የለውም። አንድ የዛፍ ችግኝ መሬት ላይ እያለ ማንም ሰው ዞር ብሎ አያየውም። ሲያድግ፣ ዋርካና ጥላ ሲሆን ግን ሁሉም ቀና ብሎ ያየዋል። የሚወድ ይወደዋል፤ የሚጠላው ይጠላዋል። መብታቸው ነው መውደድም መጥላትም። አንተ ግን ዝቅ ማለትን አትውደድ። ይወዱኛል ብለህ ዝቅ አትበል። አንተ ደስ ያለህንና የምታምንበትን አድርግ። ከዛ እነሱ ቢወዱህ፤ ቢጠሉህ የእነርሱ ምርጫ ነው።

ማጨድ የምትፈልገውን ብቻ ዝራ። ስንዴ ከዘራህ ስንዴ ነው የምታጭደው። ጤፍ ከዘራህ ጤፍ ታጭዳለህ። ምንም ካልዘራህ ግን አረም ታበቅላለህ። ሰዎች እንዲያከብሩህ ከፈለክ ራስህን አክብር። አንተ ራስህን ስታከብር አይተው እነሱም መልሰው ያከብሩሃል። በሕይወትህ እነዚህን ነገሮች ቀይር። ለራስህ የምትሰጠውን ቦታ መቀየር አለብህ። ጊዜና ገንዘብህን የምታጠፋበትን ሁኔታ መቀየር አለብህ። ውሎህን መቀየር አለብህ። ከነተረቱ ‹‹አንድ ዓይነት ቀለም ያላቸው ወፎች አብረው ይበራሉ›› ይባል አይደል።

‹‹ባለቤቱ የናቀውን አሞሌ ማንም አይገዛውም›› ይባላል። አዎ! የራስህን ሕይወት ማራከስና ዝቅ ማድረግ የለብህም። ‹‹ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ›› የሚባልም ተረት አለ። አዎ! ሰዎች ባንተ ሕይወት ጣልቃ የሚገቡት ለራስህ የምትሰጠውን ክብር አይተው ነው። ራስህን ከናክ ሌሎች ሰዎችም ይንቁሃል። ራስን ካከበርከው እነርሱም ያከብሩሃል። ለራስህ የምትሰጠው ቦታ ከፍ ማለት አለበት። ራስህን አክብረው። የዘራኸውን ነው የምታጭደው። ለራስህ ክብር ከዘራህ ክብር ታጭዳልህ።

ከሚንቁህ፣ ከሚተቹህና እንደማትችል እየደጋገሙ ከሚነግሩህ ሰዎች ጋር ለምን ትውላለህ? ለዛ እኮ ነው እየደጋገምክ እንዲህ ባደርግ ምን ይሉኛል? ያዝኑብኝ ይሆን? ይስቁብኝ ይሆን? ይቀልዱብኝ ይሆን? የምትለው ውሎህ ከማይጠቅሙ ሰዎች ጋር ስለሆነ ነው። የበታችነት እንዲሰማህ ከሚያደርጉህ ሰዎች ጋር አትዋል። ማጨድ የምትፈልገውን ብቻ ዝራ። መከበር ከፈለክ ራስህን ብቻ አክብር።

ነገሮችን አክብደህ የምታያቸው በጣም ከባዱ ስላልገጠመህ ነው። የዛሬ ሳምንት ትሞታለህ ብትባል አሁን የሚያስጨንቅህ የሰዎች ምን ይላሉ፣ ምን ያስባሉ የሚለው የሚያሳስብህ ይመስልሃል? የዛሬ ሳምንት እንደምትሞት ባሰብክ ቁጥር ‹‹እንዴት ልደሰት፣ እንዴት አድርጌ ወደፈጣሪዬ ልቅረብ?›› ነው የምትለው። አየህ! ከትልቁ ችግር አንፃር ይህ በጣም ቀላል ነው። ሰዎች ስላንተ የሚያስቡት ነገር አንተን ሊያሳስብህ አይገባም።

መሳሳትን አትፍራ። ምንም ካልሞከርክ፤ ቁጭ ካልክ የማሳካት እድልህ ዜሮ ነው። ከሞከርክ ግን የሆነ እድል ይኖርሃል። የሆነ እጣ ፈንታ ይኖርሃል። መጥፎውን አስብና ተነስ። ‹‹ደሃ ሆኜ ከምቀር ቢዝነሱን ሞክሬ ብከስር አይሻልም? እንደዚህ ስሜቴ እየተጎዳና ውስጤ እያዘነ ከምቀጥል የልቤን ተናግሬ እፎይ ብል አይሻልም? እንደዚህ ሆኜ እስከመቼ እቀጥላለሁ?›› ብለህ ማሰብ መጀመር አለብህ። ሕይወትህ ውስጥ ጥያቄ ማንሳት አለብህ። እስከመቼ ሰዎች እንደፈለጉ ያሽከረክሩኛል? እስከመቼ ይጠቀሙብኛል? እስከመቼ ገንዘቤን ለእነሱ እየሰጠሁ እነሱን ብቻ አስደስታለሁ? ..... እስከመቼ?? ማለት አለብህ።

ለአንተ አርአያ የሚሆንህ፣ የምታከብረው፣ የሆነ ነገር ከሕይወቱ የምትኮርጅለት፣ የምታደንቀው፣ አንተ የምትፈለገውን ነገር ቀድሞ ያሳካና የምትማርበት ሰው ያስፈልግሃል። ምክንያቱም እርግጠኛ ሁን ያ ሰው ራሱን ነበር። ለሰዎች ደስታ ሳይሆን ለራሱ ደስታ ሲል ሲሮጥ ነበር። እርሱን ባየኸውና ስለርሱ በሰማህ ቁጥር አንተም ለራስህ መሆን እንዳለብህ ይሰማሃል። ከሰዎች ኮርጅ። ከሰዎች የሆነ የሚጠቅምህን ነገር ስረቅ። ለራስህ አድርገው። እመንበት። ከዛ ራስህን ሁን።

የሰዎችን አድናቆት እንደትልቅ መስፈርት መውሰድ ከጀመርክ ባንተ ላይ ሙሉ ሥልጣን እየሰጠሃቸው ነው። ዛሬ የሰጡህ አድናቆት በደስታ ሰማይ ድረስ ሊያንሳፍፍህ ይችላል። ነገ ግን ከባድ ትችት ሊያጋጥምህና ስድባቸው ሞራልህን መሬት ሊፈጠፍጠው ይችላል። ራስህን እንድትጠላ ሊያደርግ ይችላል። ስለዚህ ሰዎች አደነቁህ አላደነቁህ ቦታ አትስጠው። የእነሱ አድናቆት የእነርሱ ምልከታ እንጂ አንተ ያለህበትን ትክክለኛ ቦታ አያሳይም። አስተያየቶችን ግን ራስህን ለማሻሻል ልትጠቀምባቸው ትችላለህ። ነገር ግን አምነህ አትደገፍባቸውም።

አንተ ድንቅ እንደሆንክ መጀመሪያ ለራስህ ንገረው። ከዛ ማመን ጀምር። በሂደት ድርጊቶችህ ይቀየራሉ። ማንነትህ የድንቅ ሰዎች ብቻ ይሆናል። አስታውስ! የትኛውም ስኬታማ ሰው በሰዎች ከመደነቁ በፊት ራሱን ያደንቅ ነበር። አንተም ድንቅ እንደሆንክ ሌሎች እስኪነግሩህ ድረስ አትጠብቅ፤ ራስህን ድንቅ ነኝ በማለት ጀምር። ምክንያቱም ድንቅ ስለሆንክ።

ሰዎች ባንተ ከማመናቸው በፊት አንተ በራስህ ማመን አለብህ። ያኔ ነው ሰዎች የሚደገፉህ። ጠንካራ ካልሆንክ ማንም አይፈልግህም። ዓላማ ከሌለህ፣ ማን እንደሆንክ ለማሳየት እንደምትፍጨረጨር ካላሳየህ ሁሉም ይንቅሃል። እርሱ ምን ቁም ነገር ያውቃል? ስለሕይወት ምን የተሻለ አረዳድ አለው? ሲቀልድ አይደል እንዴ የሚውለው፤ ትባላለህ። ስለዚህ ለራስህ የምትሰጠው ቦታ መቀየር አለበት። ሰዎች የሚሉህን እርሳው። ራስህን ብቻ አድምጥ። ያኔ ሰዎች ያደምጡሃል። አንተን መከተል ይጀምራሉ። ‹‹እርሱ እኮ ዓላማና ልበ ሙሉነት አለው፤ ያመነበትን ያደርጋል›› ይሉሃል።

ሕይወት አጭር ናት። ያለችህ እድሜም እንደዛው። ሰዎች ታዲያ ይህችን አጭር እድሜ እንደፈለጉ ሲነዷት ዝም ብለህ ልታያቸው ነው የፈለከው? አንድ ዓይን ያለው በአፈር አይጫወትም። አንተ እኮ አንድ ሕይወት ነው ያለህ። አንተ ከሌለህ እኮ ምንም የለም። ለማን ብለህ ነው ለዚች አጭር እድሜ ለሰዎች ደስታ ብለህ የምትሮጠው? ሰዎችን ላለማስከፋት ብለህ የማታምንበትን ነገር የምታደርገው?

ስለዚህ የምትፈልገውን ዓይነት ሰው ሁን። የሚያስደስትህን ኑር። ለማንም ስትል ያላመንክበትን ነገር አታድርግ። ሕይወትህ የሚቀየረው ራስህን ከሆንክ ብቻ ነው። ሕይወትህ እንዲቀየር ታዲያ መጀመሪያ አንተ መቀየር አለብህ። በዚህ ዓለም የሚገጥሙህ ማንኛውም ነገሮች የአንተና የአመለካከትህ ነፀብራቅ ናቸው። ደስ የሚለው ግን ያለንበት ክፍለ ዘመን አመለካከታችንን በመቀየራችን ብቻ ሕይወታችንን እንድንቀይር ያስችለናልና አንተም አመለካከትህን ለመቀየር ተዘጋጅ፤ ከዛም ራስህን ሁን፤ ያኔ ሕይወትህ ይቀየራል።

# ራስን መሆን

አስናቀ ፀጋዬ

መቼም በዚህ ምድር ላይ ራስን እንደመሆን የሚያስደስት ነገር የለም። የብዙ ሰዎች ችግር ግን ራስን አለመሆን ነው። ራስን መሆን ቢያቅት እንኳን ራስን ለመሆን የሚደረግ ብርቱ ጥረት በብዙ ሰዎች ዘንድ አይታይም። ብዙዎችም ራስን ከመሆን ይልቅ ሌላውን መምሰል የሚፈልጉት በደፈናው ነው። ራስን ከመሆን ይልቅ ሌላውን ለመምሰል የሚደረገው ጥረትም ቢያንስ ያ ሰው እንዴት ራሱን መሆን እንደቻለና የራሱን ስብእና እንደገነባ ጥያቄ ውስጥ ባስገባ መልኩም አይደለም።

ስለዚህ አንተም ‹‹እኔስ መቼ ነው እንደራሴ የምሆነው? እንደልቤ የአዕምሮ ነፃነት ኖሮኝ ሕይወቴን እንደፈለኩ የምመራው እንዴት ነው? መቼ ነው ሰዎች ምን ይሉኝ ይሆን፣ ሰዎች ስለኔ ምን ያስባሉ የሚለውን የማቆመው?›› እያልክ ይሆናል። ያንተን መኪና የሚነዳው ማነው? ቤተሰብ ነው? ጓኛህ ነው? ወይስ በዙሪያህ ያለ ሰው ነው? በርግጥ መኪና ለሁለት አይነዳም። መኪና ማለት ሕይወትህ ነው። ሕይወትህን ለሁለት የምትመራው ከሆነ፣ በሌሎች አስተሳሰብ የምትመራው ከሆነ ወደ ገደል ነው የምትገባው።

ስለዚህ በአንተ ሕይወት የሚያዘው ማነው? ገንዘብህንና ጉልበትህን የሚያዝበት ማነው? አንተና ፈጣሪህ ካላዘዛችሁበት ሰዎች እንደጥላ ናቸው፤ ፀሐይ ሲገባ ይሰወራሉ። አንተ ስትደምቅና ሲኖርህ ነው የሚከተሉህ። ከሌለህ አጠገብህ ማንም የለም። ስለዚህ በራስህ ላይ አንተ ራስህ እዘዝበት። ራስህን ሁን። እንዴት? ካልክ ጥሩ ጥያቄ አንስተሃል። እነሆ መልሱ።

ሰዎች የሚወዱህ ጥንካሬ አስካለህ ድረስ ብቻ ነው። ምን ይሉሃል መሰለህ? እሱ እኮ ያመነበትን ነው የሚያደረርገው ይሉሃል። ለምን? ስትጠነክር፤ ራስህ ላይ ስታተኩር ሁሉም ያከብሩሃል። ባይወዱህ እንኳን በልባቸው እነርሱም እንዳንተ መሆን ይፈልጋሉ። ለራስህ ቅድሚያ ስጥ። እሳቱ ላይ የምትጣደው እኮ አንተ ነህ። ምንም ቢሆን ብትታመም፣ ችግር ቢደርስብህና ብትከስር ቤተሰብና ጓኛህ አይዞህ ሊልህ ይችላል እንጂ ሕመምህን አብሮ አይታመምም። አብሮህ ገደል አይገባም። ግን አይዞህ ይልሃል። እንዴ! ሬሳ መቃብር ሲገባ አብሮ የተቀበረ ሰው አይታችሁ ታውቃላችሁ? ማንም አብሮ አልተቀበረም። ይሸኛል እንጂ አብሮ ማንም የሚቀበር ሰው የለም። የሞተ ሰው ከትንሽ ጊዜ በኋላ ይረሳል።

ስለዚህ ለራስህ መኖር መጀመር አለብህ። ለራስህ የምትሰጠውን ቦታ መቀየር አለብህ። ቅድሚያ ለራስህ ስጥ። የምታደርገውን ነገር ታምንበታለህ? ለሕይወትህ በጣም ወሳኝ ነው? አንተ ካመንክበት ሌሎች ምንስ ቢሉህ! አላማህን ካላወክ ግን ሰዎች ይነዱሃል። ወደፈለጉበት አቅጣጫ ይመሩሃል። በቃ ስላንተ አያስቡም። ዞር ብለው አያዩህም። አየህ! ሰዎች የሚወዱህ ጥንካሬህን አይተው ነው። ምን ዓይነት ጎበዝ ነው፣ ምን ዓይነት ደፋር ነው ሲሉ ይሰይሙሃል፣ ያከብሩሃል፣ ለራስህ የምትሰጠውን ቦታ ያዩና እነሱም መልሰው አንተን ያከብሩሃል። ያመንክበትን እንድታደርግ እድል ይሰጡሃል። አንተ ግን ለራስህ የምትሰጠው ቦታ መቀየር ይኖርበታል።

በጣም ታዋቂው ባለሀብት ቢል ጌትስ ‹‹ራስህን መናቅ የጀመርከው ከሰዎች ጋር መወዳደር ስትጀምር ነው›› ይላል። ለማን ብለህ ነው ራስህን የምታወዳድረው? ራስህን እንዳትንቀው። ካወዳደርከው ራስህን እየናከው ነው። አንተ እኮ ትልቅ ህልም ነው ያለህ፤ ትልቅ ፍላጎት ነው ያለህ። ጊዜያዊ ነገር እያየህ እኔ እኮ ከእሱ አንሻለሁ ወይም ከእሱ በልጫለሁ አትበል። ትልቅ ህልም ካለህ መወዳደር ላንተ አይገባም። ላንተ ማንንም ማነፃፀር የለብህም። ሕይወትህን ከራስህ አንፃር ቃኘው። ከራስህ አንፃር እየው። ትልቅ ህልም ካለህ ራስህን በፍፁም ከሰዎች ጋር አታነፃፅር።

ራስህን ማነፃፀር አቁም! ይህን ካደረክ በፍፁም ሰላም አይኖርህም። ከሰዎች ጋር ሕይወትን እያወዳደርክ ልትደሰት አትሞክር። ብትበልጣቸው ራሱ ገና መቼ መጥተው በለጡኝ ብለህ ስትሰጋ ነው የምትኖረው። ሲበልጡህ ደግሞ መቼ ነው የምበልጣቸው ብለህ ትጨነቃለህ። ውድድርና ንፅፅር ውስጥ ከገባህ ያ ሰው ምን ያስባል ምን ያደርጋል ብለህ የሰው ኑሮና ውድድር ውስጥ ነው የምትገባው። ለማን ብለህ ነው ታዲያ ራስህን የምታወዳድረው?

ሰዎችን ማስደሰት አቁም! ሁሉንም ማስደሰት



> **አንተ ድንቅ እንደሆንክ መጀመሪያ ለራስህ ንገረው። ከዛ ማመን ጀምር። በሂደት ድርጊቶችህ ይቀየራሉ። ማንነትህ የድንቅ ሰዎች ብቻ ይሆናል። አስታውስ! የትኛውም ስኬታማ ሰው በሰዎች ከመደነቁ በፊት ራሱን ያደንቅ ነበር**

አትችልም። መጀመሪያ ራስህን አስደስት። ከዚህ በተቃራኒ ግን ሁሉንም ሰዎችን አስደስታለሁ ብለህ ስትጋጋጥ እነሱ ብቻ ሳይሆኑ አንተ ራሱ መደሰት ታቆማለህ። ሀዘንተኛ ትሆናለህ። ባዶ እጅህን ትቀራለህ። መጀመሪያ አንተ በሕይወትህ ተደሰትበት።

ሁሉንም ስለማስደሰት አታስብ። ራስህን የማትሆነው እኮ ለዛ ነው። እንዲህ ባደርግ ሰዎች ያዝኑብኝ ይሆን? ይከፉ ይሆን? ስትል መቼም ደስተኛ አትሆንም። ሕይወት ትከብድሃለች። ለምን? አንተ ለሰዎች ደስታ መስዋትነት እየከፈልክ ነዋ! ነገር ግን አንድ ነገር አትርሳ። ለምትወዳቸው ስትል የምትከፍለው መስዋትነት ድንበር ያስፈልገዋል። ‹‹በቃ! ከዚህ በላይ ዋጋ አልከፍልም›› ማለት አለብህ። ‹‹ለራሴ ነው ዋጋ የምከፍለው፤ ለራሴ ነው የሆነ ነገር የማደርገው›› ብለህ ራስህን ማስቀደም አለብህ።

እንደውም ይህ የማደግ ምልክት ነው። ከፍ ስትል ዓይን ውስጥ ትገባለህ። ‹‹ሰዎች ምንድን ነው እሱ›› ይሉሃል። ይበሉህ! ችግር የለውም ከፍ ባልክ ቁጥር እነሱን ማስደሰት አይጠበቅብህም። ሊጠሉህም ይችላሉ። ይጥሉህ! ችግር የለውም። አንድ የዛፍ ችግኝ መሬት ላይ እያለ ማንም ሰው ዞር ብሎ አያየውም። ሲያድግ፣ ዋርካና ጥላ ሲሆን ግን ሁሉም ቀና ብሎ ያየዋል። የሚወድ ይወደዋል፤ የሚጠላው ይጠላዋል። መብታቸው ነው መውደድም መጥላትም። አንተ ግን ዝቅ ማለትን አትውደድ። ይወዱኛል ብለህ ዝቅ አትበል። አንተ ደስ ያለህንና የምታምንበትን አድርግ። ከዛ እነሱ ቢወዱህ፤ ቢጠሉህ የእነርሱ ምርጫ ነው።

ማጨድ የምትፈልገውን ብቻ ዝራ። ስንዴ ከዘራህ ስንዴ ነው የምታጭደው። ጤፍ ከዘራህ ጤፍ ታጭዳለህ። ምንም ካልዘራህ ግን አረም ታበቅላለህ። ሰዎች እንዲያከብሩህ ከፈለክ ራስህን አክብር። አንተ ራስህን ስታከብር አይተው እነሱም መልሰው ያከብሩሃል። በሕይወትህ እነዚህን ነገሮች ቀይር። ለራስህ የምትሰጠውን ቦታ መቀየር አለብህ። ጊዜና ገንዘብህን የምታጠፋበትን ሁኔታ መቀየር አለብህ። ውሎህን መቀየር አለብህ። ከነተረቱ ‹‹አንድ ዓይነት ቀለም ያላቸው ወፎች አብረው ይበራሉ›› ይባል አይደል።

‹‹ባለቤቱ የናቀውን አሞሌ ማንም አይገዛውም›› ይባላል። አዎ! የራስህን ሕይወት ማራከስና ዝቅ ማድረግ የለብህም። ‹‹ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ›› የሚባልም ተረት አለ። አዎ! ሰዎች ባንተ ሕይወት ጣልቃ የሚገቡት ለራስህ የምትሰጠውን ክብር አይተው ነው። ራስህን ከናክ ሌሎች ሰዎችም ይንቁሃል። ራስን ካከበርከው እነርሱም ያከብሩሃል። ለራስህ የምትሰጠው ቦታ ከፍ ማለት አለበት። ራስህን አክብረው። የዘራኸውን ነው የምታጭደው። ለራስህ ክብር ከዘራህ ክብር ታጭዳልህ።

ከሚንቁህ፣ ከሚተቹህና እንደማትችል እየደጋገሙ ከሚነግሩህ ሰዎች ጋር ለምን ትውላለህ? ለዛ እኮ ነው እየደጋገምክ እንዲህ ባደርግ ምን ይሉኛል? ያዝኑብኝ ይሆን? ይስቁብኝ ይሆን? ይቀልዱብኝ ይሆን? የምትለው ውሎህ ከማይጠቅሙ ሰዎች ጋር ስለሆነ ነው። የበታችነት እንዲሰማህ ከሚያደርጉህ ሰዎች ጋር አትዋል። ማጨድ የምትፈልገውን ብቻ ዝራ። መከበር ከፈለክ ራስህን ብቻ አክብር።

ነገሮችን አክብደህ የምታያቸው በጣም ከባዱ ስላልገጠመህ ነው። የዛሬ ሳምንት ትሞታለህ ብትባል አሁን የሚያስጨንቅህ የሰዎች ምን ይላሉ፣ ምን ያስባሉ የሚለው የሚያሳስብህ ይመስልሃል? የዛሬ ሳምንት እንደምትሞት ባሰብክ ቁጥር ‹‹እንዴት ልደሰት፣ እንዴት አድርጌ ወደፈጣሪዬ ልቅረብ?›› ነው የምትለው። አየህ! ከትልቁ ችግር አንፃር ይህ በጣም ቀላል ነው። ሰዎች ስላንተ የሚያስቡት ነገር አንተን ሊያሳስብህ አይገባም።

መሳሳትን አትፍራ። ምንም ካልሞከርክ፤ ቁጭ ካልክ የማሳካት እድልህ ዜሮ ነው። ከሞከርክ ግን የሆነ እድል ይኖርሃል። የሆነ እጣ ፈንታ ይኖርሃል። መጥፎውን አስብና ተነስ። ‹‹ደሃ ሆኜ ከምቀር ቢዝነሱን ሞክሬ ብከስር አይሻልም? እንደዚህ ስሜቴ እየተጎዳና ውስጤ እያዘነ ከምቀጥል የልቤን ተናግሬ እፎይ ብል አይሻልም? እንደዚህ ሆኜ እስከመቼ እቀጥላለሁ?›› ብለህ ማሰብ መጀመር አለብህ። ሕይወትህ ውስጥ ጥያቄ ማንሳት አለብህ። እስከመቼ ሰዎች እንደፈለጉ ያሽከረክሩኛል? እስከመቼ ይጠቀሙብኛል? እስከመቼ ገንዘቤን ለእነሱ እየሰጠሁ እነሱን ብቻ አስደስታለሁ? ..... እስከመቼ?? ማለት አለብህ።

ለአንተ አርአያ የሚሆንህ፣ የምታከብረው፣ የሆነ ነገር ከሕይወቱ የምትኮርጅለት፣ የምታደንቀው፣ አንተ የምትፈለገውን ነገር ቀድሞ ያሳካና የምትማርበት ሰው ያስፈልግሃል። ምክንያቱም እርግጠኛ ሁን ያ ሰው ራሱን ነበር። ለሰዎች ደስታ ሳይሆን ለራሱ ደስታ ሲል ሲሮጥ ነበር። እርሱን ባየኸውና ስለርሱ በሰማህ ቁጥር አንተም ለራስህ መሆን እንዳለብህ ይሰማሃል። ከሰዎች ኮርጅ። ከሰዎች የሆነ የሚጠቅምህን ነገር ስረቅ። ለራስህ አድርገው። እመንበት። ከዛ ራስህን ሁን።

የሰዎችን አድናቆት እንደትልቅ መስፈርት መውሰድ ከጀመርክ ባንተ ላይ ሙሉ ሥልጣን እየሰጠሃቸው ነው። ዛሬ የሰጡህ አድናቆት በደስታ ሰማይ ድረስ ሊያንሳፍፍህ ይችላል። ነገ ግን ከባድ ትችት ሊያጋጥምህና ስድባቸው ሞራልህን መሬት ሊፈጠፍጠው ይችላል። ራስህን እንድትጠላ ሊያደርግ ይችላል። ስለዚህ ሰዎች አደነቁህ አላደነቁህ ቦታ አትስጠው። የእነሱ አድናቆት የእነርሱ ምልከታ እንጂ አንተ ያለህበትን ትክክለኛ ቦታ አያሳይም። አስተያየቶችን ግን ራስህን ለማሻሻል ልትጠቀምባቸው ትችላለህ። ነገር ግን አምነህ አትደገፍባቸውም።

አንተ ድንቅ እንደሆንክ መጀመሪያ ለራስህ ንገረው። ከዛ ማመን ጀምር። በሂደት ድርጊቶችህ ይቀየራሉ። ማንነትህ የድንቅ ሰዎች ብቻ ይሆናል። አሰታውስ! የትኛውም ስኬታማ ሰው በሰዎች ከመደነቁ በፊት ራሱን ያደንቅ ነበር። አንተም ድንቅ እንደሆንክ ሌሎች እስኪነግሩህ ድረስ አትጠብቅ፤ ራስህን ድንቅ ነኝ በማለት ጀምር። ምክንያቱም ድንቅ ስለሆንክ።

ሰዎች ባንተ ከማመናቸው በፊት አንተ በራስህ ማመን አለብህ። ያኔ ነው ሰዎች የሚደገፉህ። ጠንካራ ካልሆንክ ማንም አይፈልግህም። ዓላማ ከሌለህ፣ ማን እንደሆንክ ለማሳየት እንደምትፍጨረጨር ካላሳየህ ሁሉም ይንቅሃል። እርሱ ምን ቁም ነገር ያውቃል? ስለሕይወት ምን የተሻለ አረዳድ አለው? ሲቀልድ አይደል እንዴ የሚውለው፤ ትባላለህ። ስለዚህ ለራስህ የምትሰጠው ቦታ መቀየር አለበት። ሰዎች የሚሉህን እርሳው። ራስህን ብቻ አድምጥ። ያኔ ሰዎች ያደምጡሃል። አንተን መከተል ይጀምራሉ። ‹‹እርሱ እኮ ዓላማና ልበ ሙሉነት አለው፤ ያመነበትን ያደርጋል›› ይሉሃል።

ሕይወት አጭር ናት። ያለችህ እድሜም እንደዛው። ሰዎች ታዲያ ይህችን አጭር እድሜ እንደፈለጉ ሲነዷት ዝም ብለህ ልታያቸው ነው የፈለከው? አንድ ዓይን ያለው በአፈር አይጫወትም። አንተ እኮ አንድ ሕይወት ነው ያለህ። አንተ ከሌለህ እኮ ምንም የለም። ለማን ብለህ ነው ለዚች አጭር እድሜ ለሰዎች ደስታ ብለህ የምትሮጠው? ሰዎችን ላለማስከፋት ብለህ የማታምንበትን ነገር የምታደርገው?

ስለዚህ የምትፈልገውን ዓይነት ሰው ሁን። የሚያስደስትህን ኑር። ለማንም ስትል ያላመንክበትን ነገር አታድርግ። ሕይወትህ የሚቀየረው ራስህን ከሆንክ ብቻ ነው። ሕይወትህ እንዲቀየር ታዲያ መጀመሪያ አንተ መቀየር አለብህ። በዚህ ዓለም የሚገጥሙህ ማንኛውም ነገሮች የአንተና የአመለካከትህ ነፀብራቅ ናቸው። ደስ የሚለው ግን ያለንበት ክፍለ ዘመን አመለካከታችንን በመቀየራችን ብቻ ሕይወታችንን እንድንቀይር ያስችለናልና አንተም አመለካከትህን ለመቀየር ተዘጋጅ፤ ከዛም ራስህን ሁን፤ ያኔ ሕይወትህ ይቀየራል።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# በማዕድን ልማት እየተጋ ያለው ዋዳፍ ኢትዮጵያ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በርካታ ሀገራት በከርሰ ምድር ውስጥ ያለውን ማዕድን በአግባቡ አውቀው፣ ለይተውና አልምተው መጠቀም በመቻላቸው ማደግና መበልጸግ እንደቻሉ መረጃዎች ያሳያሉ። ይህ ዕውነታ በኢትዮጵያም ተመሳሳይ መሆኑ ዕሙን ነው። ኢትዮጵያ ለኢኮኖሚ እድገት የማይተካ ሚና ያለውን የማዕድን ሀብት በአግባቡ ለማወቅና አልምቶ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችላትን ጉዞ ከጀመረች ሰነባብታለች። በተለይም ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ መንግሥት ለሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ትኩረት ከሰጠባቸው አምስት ዘርፎች መካከል አንዱ ማዕድን ነው። በመሆኑም ሀብቱ ያለበትን አካባቢ የመለየትና የማጥናት ሥራ ሲሰራ ቆይቶ በአሁን ወቅትም ማዕድን የማልማት ሥራው ተጠናክሮ ቀጥሏል።

ኢትዮጵያ ያላትን የማዕድን ሀብት ለመለየትና ለማልማት በምታደርገው ጥረት ከውጭ ሀገራት የሚገቡ ማዕድናትን በሀገር ውስጥ መተካትና የተለያዩ ማዕድናትን ወደ ተለያዩ ሀገራት በመላክ ለሀገሪቷ የውጭ ምንዛሪን ማምጣት ተችሏል። ሀገሪቷ ያላትን የማዕድን ሀብት አጥንተው መለየት የቻሉና አልምተው ጥቅም ላይ በማዋል እነሱም ተጠቅመው በሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ግኘት ላይ የላቀ ድርሻ እያበረከቱ ያሉ የዘርፉ ተዋናዮች በርካቶች ናቸው።

ከእነዚህም መካከል ‹‹ዋዳፍ ኢትዮጵያ›› የማዕድን ሥራዎች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት አንዱ ነው። ድርጅቱ የተለያዩ ማዕድናትን አልምቶ ለገበያ እያቀረበ ይገኛል። ድርጅቱ በሶስት ዋና ዋና ሥራዎች ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ ሲሆን፤ እነሱም ማዕድን ፍለጋ፣ ምርመራና ማዕድን ማውጣት ናቸው። ድርጅቱ በማዕድን ፍለጋ ከፍተኛ ትኩረት አድርጎ በመሥራት በዘርፉ የተገኙ መረጃዎችን ቀምሮ በቀጣይ ለሚመጣው ትውልድ ማሻገር እንዳለበት ያምናል።

የድርጅቱ መስራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ገመዳ ወርቁ ይባላሉ። አቶ ገመዳ፤ በኦሮሚያ ክልል ሰበታ ከተማ ተወልደው አርሲ አካባቢ አድገዋል። እንደ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ ወላጆቻቸውን በእርሻ ሥራ እያገዙ አድገዋል። ገና በለጋ ዕድሜያቸው የግብርና ሥራን ጠንቅቀው የሚያውቁት አቶ ገመዳ፣ የሕይወት አጋጣሚ ከውትድርናው ዓለም አድርሷቸዋል። በውትድርና ውስጥ በቆዩበት ጊዜ ታዲያ ለመሬት ያላቸው ዕውቀትና ቁርኝት ይበልጥ ተጠናክሮ ወደ ማዕድን ዘርፍ እንዲገቡ በር የከፈተላቸው መሆኑን ነው ያጫወቱን።

መሬት የሰጠናትን አንድ ፍሬ አብዝታና አባዝታ በብዙ እጥፍ የምትመልስ ባለውለታ መሆኗን በግብርና ሥራቸው ጠንቅቀው የሚያውቁት አቶ ገመዳ፤ ለ18 ዓመታት ሀገራቸውን በውትድርና ባገለገሉበት ወቅት ደግሞ በወታደራዊ ሳይንስ የመሬት ገጽታን የማወቅና የመረዳት ዕድል አግኝተዋል። ‹‹መሬት ለተጠቀመባት እናት፤ ላልተጠቀመባት ደግሞ ጠላት›› እንዲሉ፤ የእናትነት ባህሪ ልጇን በጉያዋ ሸሽጋ የምታኖር አሳልፋ የማትሰጥና ለሕይወትዋ የማትሳሳ እንደመሆኗ በተመሳሳይ መሬትም በውስጧ ያለውን ሀብት ሸሽጋ በመያዝ ለሚጠቀምባት እናት ናት›› በማለት ነው የመሬትን ጠቀሜታ ያስረዱት።

አንድ ወታደር ሲንቀሳቀስ የሚንቀሳቀስበት መልከዓ ምድር ምን እንደሚመስል ጠንቅቆ ማወቅ አለበት የሚሉት አቶ ገመዳ፤ በዚሁ ጊዜ የመሬትን ስሪትና ይዘት የማወቅና የመመርመር አጋጣሚያቸውን አስፍተዋል። የዕለት ውሏቸውን የመመዝገብ ልምድም አዳብረዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ በአንድ ወቅት አፋር አካባቢ የገጠማቸው ክስተት እጅግ አስገርሟቸዋል። ጊዜው ምሽት ነው፤ ግዳጅ ላይ እያሉ ይወድቃሉ፤ በዚህ ጊዜ ታዲያ ያነገቡት ክላሽ ከድንጋይ ጋር ሲላተም የተፈጠረው እሳት ከባድ ነበር። በወቅቱ ከፉኛ ድንጋጤ ውስጣቸውን ቢያርደውም ለማረጋገጥ ደግመው በማላተም ብልጭታውን አስተውለዋል። ከዚህ ጊዜ ጀምረው ታዲያ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸውን በመመዝገብ አካባቢያቸውን ሲያስተውሉ ቆዩ።

በዚሁ ጊዜ አፈራማ፣ ድንጋያማ፣ አለታማ ወይም ጥቁር ድንጋይ ያለባቸውን አካባቢዎች በመለየት የዕለት ውሏቸውን ይመዘግቡ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ገመዳ፤ ሀገሪቷ ዕምቅ የሆነ የማዕድን ሀብት ያላት ስለመሆኗም በዚሁ ጊዜ ተረድተዋል። ከመረዳት ባለፈም ይህንኑ ወደ ቢዝነስ ለመቀየር ባደረጉት ጥረት ዋዳፍ የማዕድን ልማት ሥራዎች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅትን አቋቁመው የተለያዩ ማዕድናትን በመፈለግ፣ በመመርመርና በማውጣት ሥራ ላይ ትኩረት በማድረግ ሥራቸውን ቀጥለዋል።




አካባቢያቸውን ለማወቅና ለመረዳት የነበራቸው አጋጣሚና ተነሳሽነት ከጥረታቸው ጋር ተደምሮ የማዕድን ዘርፉን መቀላቀል የቻሉት አቶ ገመዳ፤ የማዕድን ፈቃዳቸውም ብዙ ጊዜያቸውን በውትድርና ባሳለፉባቸው አካባቢዎች ነው። ይህም ለሀገር ማገልገል መልሶ የሚከፍል መሆኑን በተግባር ማየት የቻሉበት እንደሆነ ገልጸው፤ ከዚህ አንጻር እያንዳንዱ ሰው የተሰጠውን መክሊት አውቆ በትክክለኛና በቅንነት ሀገሩን ማገልገል ከቻለ እራሱን ጠቅሞ ሀገርንም ወደ ከፍታ ማምጣት እንደሚቻል አስገንዝበዋል።

በማዕድን ልማት አምስት ዓመታትን ያስቆጠሩ ሲሆን፤ በዚሁ ጊዜ ውስጥ በ14 የተለያዩ የማዕድን ዓይነቶች 28 የማዕድን ፈቃድ አግኝተዋል። ከእነዚህ መካከልም የድንጋይ ከሰል በዋነኝነት የሚጠቀስ እንደሆነ አቶ ገመዳ ሲያስረዱ፤ ድርጅታቸው ዋዳፍ የማዕድን ሥራዎች ሀገሪቷ ከዚህ ቀደም የውጭ ምንዛሪ በማውጣት ወደ ሀገር ውስጥ ታስገባ የነበረውን የድንጋይ ከሰል ለማልማት ብቻ አራት ፈቃዶችን አግኝተዋል። ከአራቱ ፈቃዶች መካከልም በሁለቱ የከሰል ድንጋይ ፈቃዶች ውጤታማ ሥራ እየሠራ እንደሆነ ነው። በዚህም የውጭ ምንዛሪ ከሀገር እንዳይወጣ ማዳን ተችሏል።

በሀገር ውስጥ እየለማ ያለው የድንጋይ ከሰል ከውጭ ይገባ ከነበረው በብዙ እጥፍ የተሻለና ጥራት ያለው ስለመሆኑ የጠቀሱት አቶ ገመዳ፤ በሀገሪቷ የተለያዩ አካባቢዎች ከፍተኛ የሆነ የድንጋይ ከሰል ክምችት መኖሩን ጠቅሰው፤ ድርጅታቸው ዋዳፍ ኢትዮጵያ የማዕድን ሥራዎች በኦሮሚያ ክልል ሁለት ቦታዎች፣ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልልም እንዲሁ ሁለት ቦታዎች እና በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች አርባ ምንጭ አካባቢ የድንጋይ ከሰል በስፋት እያመረተ መሆኑን ይገልፃሉ።

የድንጋይ ከሰልን በስፋት እያመረተ የሚገኘው ዋዳፍ ኢትዮጵያ የማዕድን ሥራዎች ባለፉት ሶስት ወራት ብቻ 67 ሺ ሜትሪክ ቶን የድንጋይ ከሰል ማምረት የቻለ ሲሆን፤ ይህም ወደ ገንዘብ ሲለወጥ አምስት መቶ ሁለት ሚሊዮን ብር የሚደርስ ነው። ምርቱን በሀገር ውስጥ በማልማት ለዚሁ ተግባር ይወጣ የነበረውን የውጭ ምንዛሪ ከማዳን ባለፈ ድርጅቱ ለኮሪያና ለባንግላዴሽ የድንጋይ ከሰል ማቅረብ የሚያስችለውን የቅድመ ዝግጅት ሥራውን አጠናቅቋል። ይህም የውጭ ምንዛሪን ወደ ሀገር ውስጥ በማምጣት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ምሰሶ እንደሚሆን ይታመናል።

ለሲሚንቶ ምርት ግብዓት የሚሆነው የድንጋይ ከሰል ከዚህ ቀደም ከውጭ ሀገር የሚገባ መሆኑን ያስታወሱት አቶ ገመዳ፤ በአሁኑ ወቅት በሀገር ውስጥ እየተመረተ መሆኑን ጠቅሰው ድርጅታቸው ዋዳፍም ሲሚንቶ አምራች ለሆኑ ፋብሪካዎች ለአብነትም ለዳንጎቴ፣ ለሙገርና ለሌሎችም በስፋት እያቀረበ እንደሆነና እስካሁን ያላቸው ግብረ መልስም ጥሩና የሚያበረታታ መሆኑን ገልጸዋል።

ድርጅቱ ከድንጋይ ከሰል በተጨማሪም በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ ኩርሙክ ወረዳ የወርቅ ሳይቶች ያሉትና ወርቅ ማምረት የሚያስችለውን የቅድመ ዝግጅት ሥራ ያጠናቀቀ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ገመዳ፤ ወርቅም አንዱ የሀገሪቷ ሀብት እንደመሆኑ በዚህም ሰፋፊ ሥራዎችን በመሥራት በአሁን ወቅት የምርመራ ፈቃድ ጨርሰው ማሽኖችን በመትከል ወደ ምርት ሊገቡ ጫፍ መድረሳቸውን ነው የገለጹት። ከከበሩ ማዕድናት መካከል የሚጠቀሰው ኮፐርንም እንዲሁ እያመረቱ ሲሆን ፍሎራይት የተሰኘውን ማዕድን ማልማት የሚያስችላቸውን የዝግጅት ሥራም አጠናቅቀዋል።

ዋዳፍ ኢትዮጵያ የማዕድን ሥራዎች በፍለጋ ካገኛቸው ማዕድናት መካከል ተጠቃሽ የሆነው ሌላኛው ማዕድን ማይካ ነው። ይህ ማዕድን የሚገኘው በሱማሌ ክልል ሲሆን ለዚህም አስፈላጊውን ጥናት በማድረግ ሙሉ ምርመራ አድርጎ ወደ ሥራ ገብቷል። ታይአሊን የተባለ ማዕድንም እንዲሁ በሀገሪቱ ጥሩ ክምችት ስለመኖሩ በጥናት ተረጋግጦ መልማት የሚችልበትን የቅድመ ዝግጅት ሥራ በማጠናቀቅ ወደ ሥራ የገባ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ገመዳ፤ ኢትዮጵያ በማዕድን ዕምቅ ሀብት ያላት መሆኑን ጠቅሰው፤ በዚሁ ዘርፍ ጠንካራ ሥራ በመሥራት ሀገር እንድታድግ ሕዝቦቿም ከድህነት እንዲወጡ ማድረግ ይቻላል ብለዋል።

የማዕድን ፍለጋ ሥራ ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ ትልቅ ኢንቨስትመንት መሆኑን በመጥቀስ ባሳለፉት አምስት የማዕድን ፍለጋ ዓመታት ድርጅቱ ከ40 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ማድረጉን የጠቀሱት አቶ ገመዳ፤ ከዘርፉ ከሚገኘው ገቢ በበለጠ ማዕድኑ መኖር አለመኖሩን መለየት በራሱ ትልቅ ስኬት ነው ይላሉ። ምክንያቱም ለመጪው ትውልድ ትክክለኛውን መረጃና ዳታ ሰርቶ ማስተላለፍ ያስፈልጋል። ትውልዱም ባገኘው መረጃ የተወሰነ ጥረት በመጨመር ዘርፉን ማሳደግ እንደሚችል ጠቅሰው፤ ለዚህም ድርጅታቸው ዋዳፍ ኢትዮጵያ የማዕድን ሥራዎች ለማዕድን ሥራ ትልቅ ትኩረት በመስጠት በተለይም በማዕድን ፍለጋ፣ በምርመራና በማውጣት ሥራ ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

የማዕድን ልማት በባህሪው ብዙ የሰው ኃይል የሚፈልግ ባይሆንም ዋዳፍ ኢትዮጵያ የማዕድን ሥራዎች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በተለያዩ የቢሮ አገልግሎት ሥራዎች 30 ለሚደርሱ ሠራተኞች የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል። ከቢሮ ሠራተኞች ባሻገር ድርጅቱ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ባሉት 13 ሳይቶች በእያንዳንዳቸው 50 ጊዜያዊና ቋሚ ሠራተኞች አሉት። በእያንዳንዱ ሳይት የሚገኙ 50 ሠራተኞች፣ በተለያዩ የሥራ መስኮች የተሰማሩ ሲሆን፤ በዋናነት ባለሙያ የሆኑ ተመራማሪዎች፣ ፎርማኖችና ኦፕሬተሮች ይገኛሉ። ድርጅቱ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ጨምሮ በድምሩ 680 ለሚደርሱ ሠራተኞች የሥራ ዕድል በመፍጠር ኢኮኖሚያ አበርክቶ እያደረገ ይገኛል።

ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድም የተለያየ አበርክቶ እያደረገ ያለው ዋዳፍ ኢትዮጵያ በተለይም ማዕድ በማጋራት ብዙ አቅመ ደካሞችን መድረስ ችሏል። ቢሮው ከሚገኝበት አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ለሚገኙ አቅመ ደካሞች ማዕድ የማጋራቱን ተግባር በበዓላት ወቅት ይከውናል። በማምረቻ ቦታዎችም እንዲሁ የአካባቢውን ማህበረሰብ በመመገብ ድጋፍ ያደርጋል። ከዚህ ባለፈም ያዘመሙ ጎጆዎችንም የማቅናት በጎ ሥራ እየሠራ የሚገኝ ሲሆን፤ ጅማ ዞን ዴዶ ወረዳ ላይ ለአራት አባወራዎች ቤት ለመሥራት ዕቅድ ይዞ አንዱን ቤት አጠናቆ አስረክቧል።

በቀጣይም ይህንኑ ተግባር አጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን የጠቀሱት አቶ ገመዳ፤ በአካባቢው ትምህርት ቤትና መንገድ ለመገንባት እንዲሁም ንጹህ የመጠጥ ውሃ ለማውጣት ዕቅድ ይዘው እየተንቀሳቀሱ ሲሆን፤ በአሁን ወቅትም በማምረቻ አካባቢዎች ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች መብራትና ውሃ ማጋራት ችለዋል። መንግሥት ለሚያደርጋቸው ጥሪዎችም እንዲሁ ምላሽ በመስጠት ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ እንደሆነ ተናግረዋል።

ድርጅቱ በቀጣይ የማዕድን ሥራዎቹን አጠናክሮ በመቀጠል ማዕድኑን በጥሬው ለገበያ ከማቅረብ ይልቅ እሴት በመጨመር ያወጣውን ማዕድን ለመጨረሻ ተጠቃሚ ተደራሽ የማድረግ ዕቅድ አለው። ይህን ዕቅድ ለማሳካትም አስፈላጊ የሆኑ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን እየሠራ እንደሆነ አቶ ገመዳ ገልጸዋል። እሳቸው እንዳሉት በተለይም የማዕድን ዘርፉ የብዙ አካላት ፍላጎት ያለበት እንደመሆኑ ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ያስፈልጋል። ለዚህም ነው መንግሥት በአሁን ወቅት ለማዕድን ዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑ የሚበረታታ ነው። በቀጣይም ሀገሪቷ ተዝቆ ከማያልቀው የማዕድን ሀብቷ ተጠቃሚ መሆን ትችላለች።

በማዕድን ዘርፉ በርካታ ችግሮች የሚያጋጥሙ እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ገመዳ፤ ሰዎች ራዕያቸውን ለማሳካት የሚገጥማቸውን ማንኛውንም ችግር በጽናት ማለፍ እንዳለባቸው ጠቅሰው በተለይም በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚስተዋለው የሰላም መደፍረስ ለማዕድን ዘርፉ ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም ሥራ እንቅፋት መሆኑን ተናግረዋል። ይሁንና አልጋ በአልጋ የሆነ ሥራ ባለመኖሩ ማንኛውንም ችግር አቅም በፈቀደ መጠን በመቋቋም የጀመሩትን ሥራ ወደፊት የሚያራምዱ እንደሆነ ገልጸው፤ እያንዳንዱ ማህበረሰብም ለሰላም ቅድሚያ ሰጥቶ ነገሮችን በጥንቃቄ መከወን እንዳለበትም አሳስበዋል።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የጥቁር ድንጋይ ቴክኖሎጂ- ለኮንስትራክሽን ግብዓት

በኃይሉ አበራ

የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን በሀገር ውስጥ ተኪ ምርቶች መጠቀም ተገቢና ሊደገፍ የሚያሻው ጉዳይ ነው። ለኮንስትራክሽን ዘርፍ ግብዓት መሆን ከሚችሉ ጥሬ ዕቃዎች መካከልም ባዛልት ወይም ጥቁር ድንጋይ አንዱ ነው። ይህ ባዛልት ወይም ጥቁር ድንጋይ ለኮንስትራክሽን ዘርፍ ከፍተኛ እገዛ እንዳለውና በሀገሪቱ በስፋት እንደሚገኝ መረጃዎች ያሳያሉ። በተለይም በሰሜን፣ በደቡብ፣ በኦሮሚያ ክልል እና በሌሎች አካባቢዎችም ይገኛል።

አገልግሎቱም ከአስፓልት ሥር ንጣፍ በመሆን አስፓልቱን ከመሰንጠቅ ይታደገዋል። በተጨማሪም በርካታ የፋይበር ምርቶችን ለማመረት፣ ለጂኦቴክስታይል እና ለተለያዩ የኮንስትራክሽን አገልግሎት በግብዓትነት ያገለግላል። ይሁን እንጂ የትኛው ባዛልት ወይም ጥቁር ድንጋይ ለየትኛው አገልግሎት ይውላል የሚለውን ናሙና ወስዶ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል።

ለኮንስትራክሽን ግብዓት የሚውለውን ባዛልት ወይም ጥቁር ድንጋይ በጥናት ለይቶ በመጠቀም ከውጭ የሚገቡ የግንባታ ግብዓቶችን በሀገር ውስጥ መተካት ያስችላል። በዚህም ለዘርፉ ይወጣ የነበረውን የውጭ ምንዛሪ ማዳን ይቻላል። ከዚህ ባለፈም ምርቱን ወደ ውጭ በመላክ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን ማግኘት እንደሚቻልና የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችል እንደሆነ የዘርፉ ባለሙያዎች ይስማማሉ።

የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩትም ከሰሞኑ ባዘጋጀው መድረክ ይህንኑ አመላክቷል። ትኩረቱን የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን አሟጦ መጠቀም ላይ ባደረገው ጉባኤ የተገኙት አቶ ነብዩ ነጋሽ በኢትዮጵያ የባዛልት ወይም የጥቁር ድንጋይ ኮንቲኒየስ ፋይበር እና ውህድ አካላት ቴክኖሎጂ ተወካይ ናቸው። የባዛልት ወይም ጥቁር ድንጋይን ለኮንስትራክሽን ግብዓት ለማዋል እየተደረገ ያለውን እንቅስቃሴ አስመልክተው ገለፃ አድርገዋል።

አቶ ነብዩ እንደሚሉት፤ የባዛልት ወይም ጥቁር ድንጋይ ቴክኖሎጂን በመጠቀም በበለጸጉት ሀገራት በተለይም በምዕራባውያን ባለፉት 40 ዓመታት በስፋት በግንባታ ግብዓትነት የዋለ ሲሆን ከሚበላ እና ከሚጠጣ ውጭ ለበርካታ አገልግሎቶች መዋል የሚችል እንደሆነ ያስረዳሉ። እሳቸው እንዳሉት የባዛልት ወይም ጥቁር ድንጋይ ቴክኖሎጂን ለግንባታ ግብዓትነት በስፋት መጠቀም እና በኢትዮጵያ ተግባራዊ እንዲደረግ ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት ተከታታይ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይቷል።

አሁን ሀገሪቷ በውጭ ምንዛሪ እጥረት ባለችበት ጊዜ ያሏትን የግንባታ ግብዓቶች ወደ ተሻለ ደረጃ ማሳደግ እና እሴት ጨምሮ መጠቀም ተገቢ ነው። ከዚህም ባለፈ ምርቱን ወደ ውጭ በመላክ የምንዛሪ እጥረቱን መደገፍ ይገባል። ጥራታቸውን የጠበቁ የግንባታ ግብዓቶችን ከማምረት ረገድ የቻይናን ምሳሌ መውሰድ ተገቢ እንደሆነ ጠቁመው፤ ቻይናውያን በሀገራዊ እቅድ (National Program) አካትተው የያዙት መሆኑን አንስተዋል።

ከፋይበርነት ጀምሮ የተለያዩ ዓይነት የማኑፋክቸሪንግ ሲስተሞችን በመጠቀም ጨርቃጨርቅን ጨምሮ በርካታ ነገሮችን ለማምረት የሚያስችል አዲስ ምዕራፍ እንደሆነም ተናግረዋል። ከዚህ አኳያ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ማስተካከል ከተቻለ ማህበራዊ ችግሮችንም በዚያው ልክ ለማስተካከል የራሱ ጉልህ ድርሻ አለው ብለዋል። ለምሳሌ ቤት መግዛት ባለመቻላቸው ወጣቶች ትዳር ሊመሰርቱ አልቻሉም የሚሉት አቶ ነብዩ፤ ምርቱ የቤት ግንባታን ጨምሮ ለአልባሳትና ለሌሎች ምርቶችም የሚያገለግል ነው በማለት፤ ለሀገሪቷ ከፍተኛ የኤክስፖርት እድል ሊፈጥር የሚያችልና ኢኮኖሚያዊ እድገት ማስመዝገብ የሚችል ትልቅ አብዮት ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ነብዩ ማብራሪያ፤ ከዚህ ቀደም የጥቁር ድንጋይ ቴክኖሎጂ በመጠቀም በቻይና፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ካዛኪሲታን፣ ዩክሬን፣ ኡዝቤክስታን ሀገራት ጥቅም ላይ የዋለ ነው። እንዲሁም እንደ BMW፣ ቮልስዋገን ያሉ መኪና አምራች ካምፓኒዎችም ለኤሌክትሪክ መኪና ምርት ቀላልና ጠንካራ በመሆኑና የባትሪያቸውን እድሜ ለመጨመር የሚገለገሉበት መሆኑንም አመላክተዋል። የኮንስትራክሽን ዘርፉ በርካታ ወጪዎች ያሉበት እና በሚሊዮን የሚቆጠሩ የውጭ ምንዛሪዎችን ከሀገር ውስጥ የሚያስወጣ ነው። በመሆኑም ይሄንን ችግር ለመቅረፍ የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን አሟጦ መጠቀም እና በሀገር ውስጥ ምርቶች መተካት ይገባል። በሀገር ውስጥ መተካት



ለኮንስትራክሽን ግብዓት የሚውሉ የባዛልት ወይም ጥቁር ድንጋይ ናሙናዎች

ሲባልም ጥራቱ ቀንሶ ወይም ለሕንፃ ግንባታ እድሜው አጥሮ ሳይሆን በተሻለ ሁኔታ ማምረት እና የውጭ ምንዛሪ ወጪውን ማስቀረትና በምትኩም ጥራታቸውን የጠበቁ የግንባታ ግብዓቶችን ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሪ ማምጣት ያስችላል።

ባዞልት ወይም ጥቁር ድንጋይ አንደኛ በዘልማድ "ፌሮ" የሚባለውን ጨምሮ ኮንስትራክሽን ላይ ሊገቡ የሚችሉ ብረት፣ እንጨት እና ፕላስቲክ ውስጥ ገብቶ ሊመረት ይችላል። ሁለተኛነትም "ቾፕ ፋይበር" የሚባለውን ከሲሚንቶ እና አሸዋ ጋር በመቀላቀል ጥንካሬ እንዲኖረው ተደርጎ የሚመረት እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ነብዩ፤

በሶስተኛነት ደግሞ "ጂኦ ቴክስታይል ሜሽ" የሚባለውን መረብ የሚመስለውን ዓይነት በማምረት በተለይ ቁልቁለታማ በሆኑ አካባቢዎች ላይ አስፓልት በሚሰራበት ጊዜ ከስር በማንጠፍ አስፓልቱ እንዳይሸሽ፣ እንዳይቆራረጥ እንዲሁም መሬቱ እንዳይሸረሸር እንደ ማጠንከሪያ የሚያገለግል መሆኑን ገልጸው፤

በአስፓልት ብቻም ሳይሆን ማንኛውንም መሰንጠቅ ሊከሰትባቸው የሚችሉ ግንባታዎችን ከአደጋ ለመከላከል መረቡ ከስር ተደርጎ ከላይ ሲሚንቶ ወይም ልስን በማድረግ ለማጠናከርና እድሜውን ለማሳደግ ያግዛል ብለዋል። በተጨማሪም ማዳበሪያ ሊመረትበት እንደሚችል ጠቁመዋል።

ቴክኖሎጂው በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም መጠቀም ከጀመረ ገና 40 ዓመት ያስቆጠረና አዲስ ቴክኖሎጂ በመሆኑ መንግሥት የግል ባለሀብቱን በማሳተፍ በፕሮግራሙ አስገብቶ ቢጠቀምበት ሀገሪቷ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ ትሆናለች ነው ያሉት። እሳቸው እንዳሉት፤ ባዛልት ወይም ጥቁር ድንጋይ ከምግብና ከመጠጥ ውጭ ባሉ በማንኛውም ነገር ውስጥ ሊገባ የሚችል በመሆኑ በተለያየ ሁኔታ በመጠቀም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በመተካት በቢሊየን የሚቆጠር ዶላር ማስቀረት ይቻላል። በተመሳሳይ ቴክኖሎጂው በአውሮፓ እና በቻይና ሳይቀር ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው መሆኑም ምርቱን ወደ ውጭ በመላክ የሀገሪቷን የውጭ ምንዛሪ ግኝት ማሳደግ እንደሚቻል ጠቁመዋል።

ቴክኖሎጂው ነገሮችን በተሻለ ሁኔታ የሚተካ ነው ያሉት አቶ ነብዩ፤ ድንጋዩ በባህሪው የሚዝግ ባለመሆኑ ብረትን በተሻለ ሁኔታ እንዲሁም እንጨትንና ፕላስቲክን በተሻለ ሁኔታ የሚተካ እንደሆነ ገልጸዋል። ሀገሪቷ ለተለያዩ ምርቶች ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የምታወጣ ሲሆን፤ ከምታወጣው ወጪ ቢያንስ 15 ቢሊየን ዶላር ያለ ወጪን የሚቀንስ እንደሆነ አመላክተው፤ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት በተደረገው ጥናትም 10 ቢሊየን ዶላር ያህል ወደ ውጭ ኤክስፖርት ማድረግ የሚያስችል እንደሆነ ተናግረዋል።

ባዞልት ወይም ጥቁር ድንጋይ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኝ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ነብዩ፤ በተለይም በረሃማ በሆኑ እና ለእርሻ አመቺ ባልሆኑ ቦታዎች የሚገኝ ሲሆን፤ በግብርናው ቋንቋ እነዚህን ቦታዎች ምርታማ ማድረግ እንደሆነ አስረድተዋል።

ከዚህ አንፃርም በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ዜጎች የሥራ እድል በመፍጠር ገቢ እንዲኖራቸው ማድረግ የሚቻል እንደሆነ ጠቅሰው፤ ወጣቶች ባዞልት ጥቁር ድንጋዩን ፋይበር ከተመረተ በኋላ እየገዙ ሞልድ በማድረግ ወይም ቅርጽ በማስያዝ የቤት እቃ እንዲሁም የተለያዩ ነገሮችን እየሰሩ በከተማም ሆነ በገጠር ላለው ወጣት ከፍተኛ የሥራ እድል መፍጠር የሚያስችል እንደሆነ አመላክተዋል።

ቴክኖሎጂው ላይ ምንም ጥያቄ አለመኖሩን ያነሱት አቶ ነብዩ፤ ሰዋዊ በሆኑ ምክንያቶች ሲጓተት ቢቆይም አሁን ግን ናሙናዎችን ወደ ማምረት ደረጃ ተደርሶ በዝግጅት ላይ መሆኑን ተናግረዋል። ቴክኖሎጂው በዓለም ላይ በተለይም በምስራቅ አውሮፓ 40 ዓመት ያልቆየ እና የደረጀ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከኢትዮጵያ የተወሰዱ የጥቁር ድንጋይ ናሙናዎችም በጣም ጥሩ ጥራት ያላቸው ፋይበሮች እንደወጣቸው ገልጸዋል።

የአዋጭነት ጥናቱን በተመለከተ በጥቅሉ በተሰራው ጥናት መሠረት በአሁን ወቅት አንድ ኪሎ ብረት 150 ብር አካባቢ የሚሸጥ መሆኑን አመላክተው ይህን ከ28 እስከ 30 ብር ማውረድ እንደሚቻል ገልጸዋል። እስካሁንም ወደ ተግባር ለመግባት ያልተቻለበት ሁኔታ በሀገራችን ለአዲስ ነገር ይሰጥ የነበረው ትኩረት አናሳ መሆን፣ የመንግሥታት መቀያየር እና ከፍተኛ ኢንቨስትመንት የሚያስፈልገው መሆኑን እንዲሁም ለዘርፉ ተገቢ የሆኑ ባለድርሻ አካላት ሥራዎቻቸውን በንፁህ ልብ ማከናወን ባለመቻላቸው ተግባራዊነቱን እንዳጓተተው አንስተዋል።

የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት የዚህ ዓይነት መድረኮችን አዘጋጅቶ ተገቢው የመንግሥት አካላትን በመጋበዝ መሰል መድረኮችን ማመቻቸቱን አንድ ርምጃ መሆኑን ገልጸው፤ ይህም ቀጣይነት ሊኖረው ይገባል ብለዋል። አሁንም በቀጣይ መንግሥት እጁን አስገብቶ እንደ ፕሮግራም ይዞ ሊሰራበት እንደሚገባ ጠቁመው፤ ጉዳዩ የእያንዳንዱን ኪስ የሚነካ ጉዳይ በመሆኑም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል በማለት መልዕክት አስተላልፈዋል።

የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ኢንጂነር ፈለቀ አሰፋ በበኩላቸው፤ ብዙ የግንባታ ፍላጎቶች በሀገሪቱ ስለመኖሩ አንስተው በዚያው ልክ ከፍተኛ የኮንስትራክሽን ግብዓት ችግሮች በየቦታው እንደሚስተዋሉ ተናግረዋል።

በመሆኑም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሌሎች ሀገራት የተሰሩ የኮንስትራክሽን ግብዓት ቴክኖሎጂ ተሞክሮዎች ወደ ሀገራችን እንዲገቡ እና ሀገር ውስጥ መመረት እንዲችሉ ኢንስቲትዩቱ መደላድሎችን እየሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የሀገሪቱ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች በብዛት እየተጓተቱ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ለአብነት ብረት የመሳሰሉት የውጭ ምንዛሪ ላይ መሠረት ያደረጉ በመሆናቸው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚጠይቁ እንደሆነ ገልጸዋል። በተመሳሳይ የሲሚንቶም ዋጋው እየተወደደ የሄደበት ሁኔታ መኖሩን አንስተው፤ አሁን ላይ ፍላጎታችን እየሰፋ የሚገኝ በመሆኑ እነዚህን በማስታረቅ ሂደት በስፋት እየተሰራ ነው ብለዋል።

"ችግሩን ለመፍታትም ቢያንስ ሀገሪቷ ውስጥ ያሉ ግብዓቶችን መልሶ መጠቀምና በተፈጥሮ ፕሮሰስ ማድረግ የሚቻለውን ደግሞ ፕሮሰስ በማድረግ ወደ ግንባታ ግብዓትነት በመቀየር የሥራ እድል መፍጠር፣ የውጭ ምንዛሪ ወጪን መቀነስ፣ የግንባታ ወጪን መቀነስ የሚል አሰራርን ማጸደቅ፣ አካባቢንም ተስማሚ ማድረግ እና የአካባቢንም ብክለት በመቀነስ ተስማሚ የኮንስትራክሽን ዘርፉን መገንባት ላይ ታሳቢ ተደረጎ እየተሰራ ነው" ብለዋል።

አንዳንዶቹ የኮንስትራክሽን ግንባታ ግብዓቶች በቀጥታ ከተፈጥሮ ሀብት ጋር የሚያያዙ ናቸው ያሉት ኢንጂነር ፈለቀ፤ "የፋይበር ግላስ ሪኢንፎርስመንት እንዲሁም የባሳልቲክ ፋይበር ሪኢንፎርስመንት በየቦታው ሀብት ያለበት በመሆኑ ተግባራዊ ሽራዎችን ማፋጠን እና በሚገባ ከተሰራ አምርቶ ወደ ውጭ መላክ የሚቻልባቸው እድሎች ሰፊ ናቸው፤ በቀጥታም የግንባታ ወጪዎችን በመቀነስ፣ የግንባታ ጥራትን ማስጠበቅና በተያዘለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ የሚል ዓላማ ተይዞ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት ጥረት ሲደረግ የነበረው የባዛልት ቴክኖሎጂ እስካሁን ተግባራዊ አለመደረጉ በመንግሥት በኩል የነበረው እገዛ እና ምላሽ ፈጣን አለመሆኑን አንስተው ለምን ለሚለው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ላይ እንደገለጹት የጉዳዩ ባለቤት ማነው ከሚለው አንፃር ለይቶ ካለማወቅ የመጣ እንደሆነ ገልጸዋል። አያይዘውም ከማይመለከተው ባለድርሻ ጋር የመሄድ እና ተገቢውን ምላሽ ያለማግኘት ችግሮችም በስፋት ተስተውለዋል ነው ያሉት።

ለግንባታ ግብዓት የሚውሉ ቴክኖሎጂዎችን ይዘው ወደ የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ለሚመጡ ቴክኖሎጂው አሳማኝ መሆኑን ለማሳየት ባለሙያዎች በቂ ግምገማ ያደርጋሉ። በዚህም ኢንስቲትዩቱ ስታንዳርድ ማውጣት የሚችልበት እና በግብዓትነት እንዲጸድቁ መደገፍ የሚችል መሆኑንም ጠቁመዋል።

የከተማ እና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ኢንጂነር ወንድሙ ሴታ በበኩላቸው ኮንስትራክሽን ሰፊ የሥራ እድል የሚፈጠርበት እና ለሀገር ግንባታ ያለው ፋይዳ የላቀ ቢሆንም 60 በመቶ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ከውጭ የሚገቡ መሆኑ ዘርፉን እየፈተነ ይገኛል ብለዋል። ይህን ችግር ለማቃለልም በዘርፉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም እና በሀገር ውስጥ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ለመተካት እየተሰራ መሆኑን አመላክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኤች አይቪ ኤድስ ዛሬም ልዩ ትኩረትን ይሻል!

የኤች አይቪ ኤድስ ቫይረስ ዛሬም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ስጋት ሆኖ ቀጥሏል። በሁለት አስርት ዓመታት ብቻ በዓለም የ40 ሚሊዮን ሰዎችን ህይወት የቀጠፈው ኤች አይ ቪ ኤድስ፤ በኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከጫፍ ጫፍ አካልሎ 134 ሺህ ሰዎችን ህይወት አሳጥቷል።

ቫይረሱ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደተገኘ በይፋ ከተነገረ አራት አስርት ዓመታት ተቆጥረዋል። በእነዚህ ዓመታትም እስከ 2014 ብቻ ከ744 ሺህ በላይ ሕፃናትን ያለወላጅ ያስቀረው ይሄው በሽታ በኢትዮጵያ የቫይረሱ የስርጭት ፍጥነት ጣሪያ የነካው በ1988 ነበር።

የስርጭቱ ፍጥነት በሀገር አቀፍ ደረጃ ለተወሰኑ ዓመታት የመቀነስ አዝማሚያ ማሳየቱን ቢነገርም፤ አሁን ላይ ከ610 ሺህ በላይ ዜጎች ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖሩ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በቫይረሱ እየተያዙ ካሉት ዜጎች 70 መቶ የሚሆኑት ደግሞ አምራች ኃይሎች መሆናቸው ችግሩን እጅግ አሳሳቢ ያደርገዋል።

በአዲስ መልክ ከሚያዙት የኅብረተሰብ ክፍሎች ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 30 ያሉ ዜጎች 70 በመቶውን መያዛቸው ወጣቱ ትውልድ ምን ያህል እንደተዘናጋ ማሳያ ነው። ስርጭቱን ይበልጥ አስከፊ ያደረገው ደግሞ ሴቶች ለዚሁ ችግር ይበልጥ ተጋላጭ መሆናቸው ነው። የቅርብ ጥናቶች የሚጠቁሙት ስርጭቱ 1 ነጥብ4 በመቶ በሴቶች፤ 0.8 በመቶ በወንዶች መሆኑ ነው።

ከ15 እስከ 19 ዓመት እድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሴቶች 0.2 በመቶዎቹ ቫይረሱ በደማቸው ይገኛል። በተመሳሳይ የእድሜ ክልል የሚገኙ ወንዶች በአንፃሩ ተጋላጭነታቸው ዜሮ ነው። በወጣትነት እድሜም ቢሆን በሴቶች የሚኀላው የቫይረሱ ስርጭት ከ25 እስከ 29 የእድሜ ክልል ያሉ ወጣት ሴቶች ላይ ሲሆን፣ 2.9 በመቶዎቹ ቫይረሱ በደማቸው እንዳለ ሲረጋገጥ በተመሳሳይ እድሜ በወንዶች የታየው ስርጭት መጠን 0.9 በመቶ ነው።

በኢትዮጵያ ቫይረሱን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ባለፉት 30 እና 40 ዓመታት ብዙ ሥራዎች ተሰርተዋል። በተሠራው ሥራ ልክም ስርጭቱን መቀነስ ቢቻልም በአሁኑ ወቅት ቫይረሱ እንደጠፋ የሚያስበው በተለይም የወጣቱን መዘናጋት ለማመላከት ከተጠቀሰው ቁጥር የበለጠ ማሳያ አይኖርም። የቫይረሱ ስርጭት ወጣት እና አፍላ እድሜ ላይ የሚገኙ ዜጎች ላይ እየጨመረ የመጣበት ዋነኛ ምክንያትም መዘናጋት ነው።

የቫይረሱ ሥርጭት በሀገር ደረጃ ከአንድ በመቶ በታች መሆኑን የሚጠቁሙ መረጃዎች ቢኖሩም በአንዳንድ ክልሎች ስርጭቱ እያደገ መጥቷል። ስርጭቱ አምራች ዜጎችና ሴቶች ላይ መጨመሩ እንዲሁም ወደፊት እንደ ወረርሽኝ መልሶ እንዲያገረሽ ይበልጥ ዕድል መስጠቱ አስከፊው ጉዳይ ነው።

ስለቫይረሱ ሁለገብ እውቀት በበቂ ሁኔታ አለመዳረስ ለስርጭቱ ማገርሸት ትልቁን ድርሻ ይወስዳል። ለዚህም ኤች አይ ቪን በተመለከተ በቂ የሚባል ግንዛቤ እና እውቀት ያላቸው ሴቶች ከጠቅላላው ቁጥራቸው 19 በመቶ ብቻ መሆኑን ልብ ይላል። ልቅ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፣ ኮንዶምን ሁልጊዜና በአግባቡ አለመጠቀም ብዙዎችን ለቫይረሱ ተጋላጭ አድርጓል። በሴተኛ አዳሪዎች የቫይረሱ ስርጭት 25 በመቶ የደረሰ ሲሆን፤ አሁንም ግብረስጋ ግንኙነት ከሚፈፅሙ ወንዶች መካከል 64 በመቶዎቹ ሴተኛ አዳሪዎችን እንደሚኀበኙ በጥናት የተደገፉ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ኤች አይ ቪ በኢትዮጵያ መልሶ ሊያገረሽ ወደማይችልበት ደረጃ አልወረደም። ለዚህ ደግሞ ወጥ የኮንዶም ማሰራጨት አሰራር አለመዘርጋት እና የማሰራጫ ጣቢያዎች የክትትል ሥርዓት አለመኖር ችግሩን በበቂ መንገድ መከላከል እንዳይቻል አድርጓል።

በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምርመራ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ቁጥር አነስተኛ መሆንና የፀረ ኤች አይቪ መድኃኒት ከሚያስፈልጋቸው ለ13 በመቶዎቹ ብቻ መድረስ የቫይረሱን ተጠቂነት ችግር እንዳይቀረፍ ተጨማሪ ምክንያቶች ናቸው።

ዛሬ ላይ ተጋላጭነቱ እየጨመረ የሚገኘውን ወጣቱን ትውልድ ለማንቃት የግንዛቤ ማስጨበጫና የባህሪ ለውጥ ሥራዎች በተለያዩ ጊዜና በተለያዩ አካባቢዎች በልዩ ሁኔታ መስጠት የግድ የሚልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። ከዚህ ቀደም ማኅበረሰቡን በማንቃት ረገድ ከሚሰራው አንጻር አሁን ላይ በጣም ተቀዛቅዟል። በመሆኑም የመንግሥት ተቋማት፣ ኅብረተሰቡና የሚዲያ አካላት ከጤና ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ጋር በመሆን ከምርመራ ባሻገር የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎችን በስፋት ሊሰሩ ይገባል!

በተለየ ሁኔታ ለቫይረሱ ተጋላጭ ናቸው በተባሉት ዜጎች ማለትም ሴተኛ አዳሪዎች፣ አደንዛዥ ዕጽ ተጠቃሚዎችና የረጅም ርቀት ሹፌሮች ላይ የሚያተኩር ሥራ ከምንጊዜውም በላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል። ቫይረሱ ያለባቸውን ሰዎች በምርመራ የመለየት፣ ተገቢውን ሕክምና እንዲያገኙ የማድረግና የቅድመ-መከላከል ሥራዎች ይበልጥ ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል።

ፍትሐዊ የኤች አይቪ ሕክምና አገልግሎትን ለሁሉም ተደራሽ ለማድረግም ከመቼውም ጊዜ በላይ በትኩረት ሊሰራ ይገባል። ጥቂት መዘናጋት እኤአ በ2030 ኤች አይ ቪ ኤድስ የጤናና የማህበራዊ ችግር እንዳይሆን የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት እንቅፋት ይሆናል። መዘናጋትም እንደ ሀገር ትልቅ ዋጋ ያስከፍላልና ዛሬም ትኩረት ለኤች አይቪ ኤድስ!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## አብሮ የማደግ የልማት ጥያቄ

**አስማየሁ ግዛው**

የባህር በር/ወደብን ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገትን ሆነ የተሟላ ሉአላዊ ሀገር ለመፍጠር የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብም እንደ አንድ አቅም ይወሰዳል። ከዚህ የተነሳም የባህር በር ያላቸው ሀገራት ከሌላቸው 20 ከመቶ እድገት እንደሚኖራቸው ጥናቶች ያመላክታሉ።

ኢትዮጵያ በማደግ ላይ ካሉ የአፍሪካ ሀገራት አንዷ ስለመሆኗ ዓለም አቀፍ ተቋማት ሳይቀር እያረጋገጡት ያለው እውነታ ነው፤ ይህም ሆኖ ግን የባህር በር አልባ መሆኗ ዜጎቿ በሚመኙት ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ላይ ሆነ በሉዓላዊነቷ ላይ ተግዳሮት ከሆነ ከሶስት አስርት ዓመታት በላይ ተቆጥረዋል።

ሀገሪቱ በሕዝብ ብዛታቸው ቀዳሚ ከሆኑ / ከ120ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያላት / እና የባህር በር ከሌላቸው የዓለም ሀገራት የመጀመሪያ እንደሆነች መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም በሀገሪቱ ዛሬዎች ሆነ ነገዎች ላይ ሊኖረው የሚችለው አሉታዊ ተጽእኖ መላውን ሕዝብ አደጋ ውስጥ ሊከት እንደሚችል ይታመናል።

የባህር በር አልባ መሆን ሀገራትን ከውሃ አካላት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት የሚያገል ፤ በአቅራቢያቸው ከሚገኙ ትላልቅ የንግድ መዳረሻዎች ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚያደርግ ነው፤ ከዚህ ባለፈ የኢኮኖሚ ነጻነት እንዲያጡ በማድረግ ረገድ ቀዳሚውን ድርሻ እንደሚይዝ ጥናቶች ያመለክታሉ።

ይህ ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ በማደግ ላይ ያሉ እና የህዝብ ብዛታቸው ከፍተኛ የሆኑ ሀገራትን በእጅጉ የሚፈትን ስለመሆኑ ብዙም ለጥያቄ የሚቀርብ አይሆንም። “በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” እንደሚባለው ባልተመጣጠነው የወጪ እና ገቢ ንግድ ላይ ተዳምሮ ሀገራዊ ኢኮኖሚው እንዳይረጋጋ ማድረጉ የማይቀር ነው።

አሁን ላይ ሀገሪቱ ወደ ውጪ ከምትልካቸው ምርቶች ይልቅ ከውጪ የምታስገባቸው ምርቶች ከፍተኛውን ቦታ ይይዛሉ፤በዚህ ላይ ለወደቦች ኪራይ ልታወጣው የምትችለው ወጪ ሲታከል እንደ ሀገር በዜጎች የእለት ተእለት ሕይወት ላይ ሊፈጥር የሚችለው ጫና እጅጉን ከፍተኛ ነው።

ሀገሪቱ የጅቡቲን ወደብ በኪራይ መጠቀም ከጀመረች ሶስት አስርት ዓመታት ተቆጥረዋል። በነዚህ ዓመታትም ለጅቡቲ በበርካታ ቢሊዮን ዶላሮች እየከፈለች ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥና ወደ ውጪ ስታጓጉዝም ቆይታለች። ይህም በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ /በተለይም ኢኮኖሚዋ እያደገ በመጣ ቁጥር እያስከተለ ያለው ጫና ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ነው።

አሁን በተጨባጭ ሀገሪቱ ለወደብ ኪራይ በቀን 3 ሚሊዮን ዶላር ለጅቡቲ ትከፍላለች። ይህ ደግሞ በዓመት ሲሰላ ወደ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ገደማ ይሆናል። ይህ ለአንድ ወደብ ኪራይ የሚከፈል ገንዘብ በውጪ ምንዛሬ መሆኑ ደግሞ ችግሩ የቱን ያህል የከፋ ስለመሆኑ ማሳያ ነው።

ገቢ ንግድ ሚዛን ከፍ በሚልባቸው፤ ከዚህም ባለፈ ኢኮኖሚያቸው በግብርና ላይ መሰረት ላደረጉ ሀገራት ዶላር ማግኘት የቱን ያህል ፈተና እንደሆነ ለመግለጽ የሚያዳግት አይደለም። ከዚህ የተነሳም ሀገራችን በየጊዜው የሚያጋጥማትን የዶላር እጥረት እና በወደብ ኪራይ መጨመር የሚመጣውን ጫና ተቋቁማ የ120 ሚሊዮን ሕዝብ ፍላጎትን በቅጡ ማርካት ይቻላታል ብሎ ማሰብ ቀላል አይሆንም።

ከዚህ የተነሳ አሁን ላይ እያነሳች ያለው የአማራጭ ወደብ ጉዳይ፤ የሉአላዊነትና የህልውና ጉዳይ መሆኑን ለመገንዘብ አይከብድም። የወደብ ጥያቄው / የባህር በር / ጦረኛ ሆና ሳይሆን የባህር በር የዜጎቿ የህልውና ጥያቄ በመሆኑ ነው ። ይህን ለመረዳት ደግሞ አለም አቀፉም ህብረተሰብ ሆነ ጎረቤት ሀገራት የሚከብዳቸው አይሆንም።

አሁን ላይ ያለው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ሀገሪቱ ከ90 ፐርሰንት በላይ የሚሆነውን የወጪ ገቢ ንግዷን የምታከናውነው በጅቡቲ ወደብ ላይ ነው። ይህ ደግሞ ለወደቡ ኪራይ ከሚወጣው ከፍተኛ ገንዘብ በተጨማሪ ኢትዮጵያዊያን ላይ ሊፈጥር የሚችለው የደህንነት ስጋት ቀልሎ የሚታይ አይደለም።

> **ኢትዮጵያ የምሥራቅ አፍሪካ የሰላም ዘብ ነች፤ የራሷንና ጎረቤቶቿን ሰላም ስታስጠብቅ የኖረች የሰላም አምባሳደር ነች፤ የአማራጭ ወደብ ጥያቄዋም ከዚህ ማንነቷ የሚመነጭና ሰላማዊ አማራጮችን ታሳቢ ያደረገ ነው**

ከወደቡ ጋር በተያያዘ ለአንድ ቀን እንኳ ችግር ቢፈጠር፤ በኢትዮጵያዊያን ህልውና ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ የቱን ያህል አደገኛ ሊሆን እንደሚችል ለመገመት የሚከብድ አይደለም፤የተለየ እውቀት የሚጠይቅ አይሆንም።

ይህ ማለት ሌላ አማራጭ ወደብ ባለመኖሩ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ ሥራ የሚያቆም ይሆናል ማለት ነው። ከነዳጅ ጀምሮ ኢኮኖሚውን የሚያንቀሳቅሱ ሸቀጦችን በቀላሉ ማግኘት የማይቻል ሁኔታ ሲፈጠር የ120 ሚሊዮኑ ሕዝብ ህልውና ጥያቄ ውስጥ ከመግባትም የሚያልፍ ይሆናል።

ኢትዮጵያ የምሥራቅ አፍሪካ የሰላም ዘብ ነች ፤ የራሷንና ጎረቤቶቿን ሰላም ስታስጠብቅ የኖረች የሰላም አምባሳደር ነች ፤ የአማራጭ ወደብ ጥያቄዋም ከዚህ ማንነቷ የሚመነጭና ሰላማዊ አማራጮችን ታሳቢ ያደረገ ነው።

ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ ከጎረቤቶቿ ጋር በጋራና በሁለትዮሽ ትብብር አማራጭ ወደቦችን ለማልማት የምታደርገውን ጥረት በአዎንታዊ መልኩ ተረድተው፤የጋራ ተጠቃሚነትን መርህ ባደረገ መልኩ ምላሽ ሊሰጧት ይገባል።

ከዓለም አቀፍ ህግ አንፃር ኢትዮጵያ የባህር በር ለእድገቷ እና ለልማቷ ከማስፈለጉም በላይ፤ ጉዳዩ የህገሬው ዜጋ የዳቦ ጥያቄም ጭምር በመሆኑ ሁሉን አቀፍና የሁሉንም ሀገራት ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ ምላሽ ሊሰጠው ይገባል።

ለዚህም የወደብ ባለቤት የሆኑ ጎረቤት ሀገራት በቀረበው የውይይት እና የንግግር ጥሪ መሰረት ቁጭ ብሎ በመወያየት ለጥያቄዋ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል። አፍሪካዊ ችግሮችን በአፍሪካዊ መፍትሔ ለመፍታት የተጀመሩ ጥረቶችን በማጠናከር፤አብሮ ለማደግ የቀረበው ጥሪ ለቀጣናው ሀገራት የሚኖረውን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት በማጤን ፈጥኖ ምላሽ መስጠት ተገቢ ነው።

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሴሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታተሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፣ˆአስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ቀን የጣለው ዕድሜ ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

የቀትሯ ፀሀይ «እናት ትበሳለች» ይሏት አይነት ከእግር እስከ ግንባር ዘልቃለች ። በዚህ ሰአት ርቆ ለሚሄድ እግረኛ መንገዱ ፈተና ነው ። በዚህ ሰአት አንዳች የምህረት ንፋስ «ሽው» ይል አይመስልም ። የበጋው ሙቀት ደርሶ መላ አካልን ያስጨንቃል።

በዕለተ ቅዳሜ ተሲያት ሰፈረ መገናኛ ልቡ ላይ ደርሻለሁ ። በዚህ ቦታ ትርምሱ ይለያል ። ኪስ ዳባሹ፣ ጎሽሞ አላፊው ይበረታል። የመንገድ ገበያው ለእግረኞችና ለመኪኖች ምቹ አይደለም። እዚህም እዚያም የተዘረጋው የጎዳና ላይ ንግድ መሄጃ መራመጃ እያሳጣ ነው። እንዲያም ሆኖ የሚጠይቅ፣ የሚገዛው ጥቂት አይደለም።

ከዚህ ተቃርኖ ስፍራውን የለወጡት ትላልቅ ህንፃዎች በዘመናዊ ዕቃዎች ተውበው እይታን ይማርካሉ። በነዚህ ቦታዎችም ገዥና ጎብኚው በእኩል ይጋፋል። አይቶ የሚወጣው ፣ ገዝቶ የሚያስጭነው፣ ዕለት በዕለት ይጎርፋል። መገናኛ የብዙ እይታዎች ፣ የበርካታ ትርምሶች ስፍራ ነው።

**የሐረሯ እማማ ...**

ዓይን ከምትወጋው ደማቅ ፀሀይ ሳልሸሽ ለወጉ ከቆምኩበት አንድ ጥግ የሰአቱን መድረስ እጠብቃለሁ ። የእግሬ መምጣቱ አጋጣሚ ከእንግዶች ጋር የነበረኝ ቀጠሮ ነው። አሁንም ከትርምሱ መሀል ቆሜያለሁ። አስተውሎቴ በአግራሞት እንደቀጠለ ነው ። ለደህንነቴ ስል ሀሳቤን አልጣልኩም። የትከሻ ቦርሳዬን እንዳጠበኩ



ከወዲያ ወዲህ እቃኛለሁ።

ዓይኖቼ አያዩት የለም። የመገናኛ ጎዳና በመልከ ብዙ ገጽታ መገለጡ እንዳስገረመኝ ቀጥሏል ። በድንገት እይታዬ ከአንዲት እናት ላይ አረፈ። ዕድሜቸው ገፍቷል። አለባበሳቸው ለየት አለብኝ። አንገታቸው ላይ ‹‹ጉፍታ›› የሚባለውን ሻሽ ጣል አድርገዋል። እሱም እንደሳቸው እድሜ በልቶታል።

ልብሳቸው ከማርጀት አልፎ በላያቸው ቆሽሿል። ይህ ሁሉ ለተመልካቹ እንጂ ለእሳቸው ምንም ማለት አይደለም ። ለአቀማመጣቸው ቦታ አይመርጡም ። አፈሩ አቧራውና ጠጠሩ ደንታ አይሰጣቸውም። ባገኙበት ስፍራ አረፍ ይላሉ።

እማማ አሁንም ለአፍታ ቁጭ ካሉበት ተነስተው አለፍ ብለው ተራመዱ። ብዙ አልቆዩም። ተመልሰው መጡና ከነበሩበት ቦታ ተቀመጡ። ነገሩን ሲደጋግሙት ዓይኔ ተከተላቸው። ካሉበት ሆነው የአንድን መንገደኛ ወጣት እጅ እየሳሙ ሲያመሰግኑት፣ ሲመርቁት አየኋቸው። ጉዳዩ የገባኝ ዘግይቶ ነበር ።

አሁን አጠገቤ ደርሰው ጭውውት ጀምረናል። ብስል ቀይ ናቸው። ቀረብ ሲሉኝ የአዳፋ ልብሳቸውን መልክ አየሁት። ቀለል ያለ ሺቲ ነው። እሳቸው እያወሩኝ ገጽታቸውን አስተዋልኩ ። ግንባራቸውን ይዞ መላ ፊታቸውን የከበቡ ቀጫጭን መስመሮች ብዙ ይናገራሉ። ዘለግ ያለ ቁመናቸው ፣ አሳዛኝ አንደበታቸው፣ ጎስቋላው ማንነታቸው ብዙ ይናገራል።

ለጊዜው ስማቸውን አልጠየኩም። እሳቸውም ለዚህ ትውውቅ አልፈጠኑም። ሊያወጉኝ የፈለጉት ጉዳይ እንዳለ አውቄአለሁ። ውስጤ ሊያዳምጣቸው ቸኩሏል። ከእጃቸው የገቡትን ጥቂት ብሮች ከሳንቲሙ እየለዩ ወደ ጉያቸው ቋጠሩ ። ሄድ ብለው ያመጡት ምንዳ መሆኑን ተረዳሁ።

አሁንም ዓይናቸው ከላይ ታች ያማትራል። ደግነቱ ያየ አያልፋቸውም። የእጁን እየጣለ ፣የአቅሙን ያደርጋል። የሰጣቸውን ይመርቃሉ፣ያመሰግናሉ።

እማማ የሐረር ሴት ናቸው። ተወልደው ያደጉት፣ ትዳር ይዘው የከበዱት እዛው መሆኑን አወጉኝ። ጨዋታ ሲጀምሩ ንግግራቸው ቀለል ይላል። እየሰማኋቸው መሆኑን ሲያውቁ የልባቸውን እውነት ቀጠሉ። የሐረር ኑሯቸው ከቤተሰብ ጋር ነበር። ዓመታትን በገፉበት አገር ክፉ ደግን አልፈዋል። ከልጅነት እስከ ሽበት የበቁበት ስፍራ ለእሳቸው የማንነት አሻራ ነው።

እማማ የሐረሯ ባገር በቀያቸው ያሻቸውን ቢሆኑ ከብዷቸው አያውቅም። እንዲህ እንደዛሬው ዕድሜ ሳይጫናቸው ጉልበታቸው የፈቀደውን ሰርተው አድረዋል። ቢቸገሩ፣ ቢያጡ፣ ቢነጡ ደግሞ ከወዳጅ ዘመድ የጠየቁትን አያጡም። ማንነታቸውን የሚያውቁ ሁሌም ከጎናቸው ይሆናሉ ። ዕድሜያቸውን በገፉበት ሐረር ህይወት ዓለማቸውን ትተውት ወጥተዋል። ዛሬ በአዲስ አበባ ሰማይ ስር ባቆማቸው አጋጣሚ ክፉ ደጉን ቢያዩም ከአንደበታቸው ምስጋና አይጠፋም። ሁሌም «ተመስገን» ማለት ልምዳቸው ነው ።

**ከሁለት ዓመት በፊት...**

እማማ ራሳቸውን አዲስ አበባ ሳያገኙት በፊት ከሐረር የሚወጡበት ምክንያት አልነበረም ። ቢሾፍቱ የሚኖረው ልጃቸው የአቅሙን እየረዳ «አለሁሽ» ሲላቸው ቆይቷል ። ልጃቸው መተዳደሪያው የግንባታ ስራ ነው። የሚሻውን ባገኘ ጊዜ ሙያውን እየከፈለ የወር ደሞዝ ያገኛል። ከሚከፈለው ገንዘብ ለእናቱ

... ወደ ገጽ 17 ዞሯል

## ከአማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# በሁለት የተለያዩ የስሜት ፅንፎች የመገኘት ህመም /ባይፖላር ዲስኦርደር/

ባይፖላር የሚለው ቃል ከእንግሊዝኛ ቋንቋ የተወሰደ ሲሆን ቃሉም የሁለትቃላት ውህድ ነው። ባይ ማለት ሁለት ሲሆን ፖላር ማለት ዋልታ ወይም ፅንፍ ማለት ነው። በአንድ ላይ ሲሆኑ ሁለት ጫፍ ወይም ዋልታ የሚል ትርጓሜ ይሰጣል። ለዚህ ህመም ይህ ስያሜ የተሰጠበት ምክንያት በሁለት የተለያዩ የስሜት ፅንፎች ግለሰቡ እንዲገኝ የሚያደርግ በመሆኑ ነው።

አንደኛው የስሜት አይነት ከመጠን ባለፈ የደስታ ስሜት ውስጥ መገኘት ሲሆን “ማንያ” ወይም ሽቅለት ይባላል። ሁለተኛው አይነት ስሜት ደግሞ ከመጠን ባለፈ የድብርት ስሜት ውስጥ መገኘት ነው።

በሁለቱ ሁኔታዎች መካከል ግለሰቡ እንደማንኛውም ጤነኛ ሰው ስራውን እየሰራ ሊኖር ይችላል። ሆኖም ህመሙ ደጋግሞ የሚያገረሽ ከሆነ በሁለት ስሜቶች መካከል ያለው ግለሰቡ ጤነኛ የሚሆንበት የጊዜ ገደብ ሊለያይ ይችላል።

ይህ የስሜት መታወክ ህመም ከ100 ሰዎች በአንዱ ላይ የሚገኝ ነው። የባይ ፖላር ህመም በሴቶች እና በወንዶች ላይ በእኩል ሁኔታ የሚገኝ ሲሆን ከሌሎቹ የስሜት ህመሞች በተለየ በወጣትነት የእድሜ ክልል ይጀምራል፤ ይህም ሲባል ህመሙ የሚጀምረው በአማካይ በአስራዎቹ የእድሜ መጨረሻ ሲሆን በህጻናት ላይም ሊከሰት ይችላል።

በወንዶች ላይ ከመጠን ያለፈ የደስታ ስሜት ጎልቶ ሲታይ ሴቶች ግን በአብዛኛው በድብርት ስሜት ውስጥ ይሆናሉ። ይህ ህመም ያለባቸው ወንዶች በሱስ የመጠቃት እድላቸው ሲሰፋ ሴቶች ግን በጭንቀት ህመም ይጠቃሉ።

**የህመሙ መንስዔ**

የባይፖላር ህመም እንደሌሎች የአዕምሮ ህመሞች አንድ ብቸኛ ምክንያት የለውም። ይህም ሲባል ከሚከተሉት ውስጥ በአንዱ ወይም በሁሉም ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል። መንስኤውም ተፈጥሮአዊ፤ ስነልቡናዊ እና ማህበራዊ ሊሆኑ ይችላሉ።

**ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች**

ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች የምንላቸው በዋናነት በዘር የመተላለፍ ሁኔታዎችን ነው። በቤተሰብ ውስጥ የባይፖላር ህመም ያለበት ሰው ለምሳሌ እናት፣ አባት፣ እህት ወይም ወንድም ያለው ሰው በህመሙ የመጠቃት እድሉ ከሌላው ማህበረሰብ ከፍ ያለ ነው። ሌላው ደግሞ በአንጎል ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ንጥረ-ነገሮች በተገቢው ሁኔታ ያለመገኘት ነው።

**ስነልቡናዊ እና ማህበራዊ**

የተለያዩ ሥነ-ልቡናዊ ጫና የሚያስከትሉ ማህበራዊ ክስተቶች በግለሰቡ ላይ የባይፖላር ምልክት እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል፤ ለምሳሌ አካላዊ እና ስነ-ልቡናዊ ስቃይ የሚያደርሱ ሁኔታዎች የተከሰቱበት ግለሰብ በከፋ የድባቴ ወይም በሽቅለት ስሜት ውስጥ ሆኖ ሊገኝ ይችላል።

**የባይፖላር ህመም ምልክቶች ምን ምን ናቸው?**

የባይፖላር ህመም በሁለት ዋና ዋና የስሜት ምልክቶች ስብስብ ይታያል

**ሀ) ሽቅለት/ከመጠን ያለፈ የደስተኝነት ስሜት**

ከሳምንት ላላነሰ ጊዜ የሚቆዩ ምልክቶች ሲኖሩት ምልክቶቹም የሚከተሉት ናቸው።

- ነገሮች በቀና ሁኔታ እየሄዱ ባይሆን እንኳን ያለአግባብ የሚሰማ የደስተኝነት ስሜት
- ከተገቢው እና ከወትሮው የተለየ ንቁነት እና ታታሪነት
- ከወትሮው የተለየ ቁጡነት፣ ነጭናጫነት
- ከተገቢው በላይ ከፍ ያለ በራስ መተማመን ወይም ስለራስ የሚሰማ ስሜት መጨመር
- ብዙ በፍጥነት እና ያለማቋረጥ ማውራት ከሃሳብ ወደሃሳብ፣ ከርዕስ ወደ ርዕስ መዝለል
- በቀላሉ የሃሳብ መሰረቅ ወይም መበታተን
- እንቅለፍ የመተኛት ፍላጎት መቀነስ ወይም አለመተኛት
- በእራስ እና በህይወት ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሁኔታዎች ውስጥ መገኘት፤ ለምሳሌ ጠጥቶ ማሽከርከር፣ ጥንቃቄ ያልታከለበት ወሲብ ውስጥ መገኘት፣ገንዘብ ማባከን
- ከወትሮው የተለየ ተግባቢነት እና ማህበራዊ ግንኙነት
- ሀይለኝነት እና ተከራካሪነት

**ለ)የድብርት ስሜትየ የድባቴ ጽንፍ ምልክቶች**

የሚከተሉት ምልክቶች ከሞላ ጎደል በየቀኑ አብዛኛውን ጊዜ እየታዩ ቢያንስ ለሁለት ሳምንት መቆየት ይኖርባቸዋል። ምልክቶቹም የሚከተሉት ናቸው።

- የድብርት /የሀዘን ስሜት ወይም በህይወት የመኖር ፍላጎት ማጣት
- የምግብ ፍላጎት ማጣት ወይም መጨመር
- የሰውነት ክብደት መቀነስ ወይም መጨመር
- እንቅልፍ ማጣት ወይም መብዛት
- የሃሳብ እና የአነጋገር ዘገምተኛ ወይም ቀሰስተኛ መሆን
- የድካም ስሜት መሰማት
- ራስን ዋጋ-ቢስ አድርጎ ማየት ወይም የጥፋተኝነት ስሜት መሰማት
- ትኩረት ማጣት፣ በነገሮች ለመወሰን መቸገር
- ራስን ከማጥፋት ጋር የተያያዘ ሃሳብ ወይም ሞትን መመኘት
- በስራ፣ በትምህርት፣ በማህበራዊ ሕይወት ላይ ከፍተኛ መዛባት መኖር

የባይቦላር ህመም ህክምናና ክትትል የሚያስፈልገው የህመም አይነት ነው። የባይፖላር ህምም ህክምና በሚከተሉት ግቦች የአለመ መሆን አለበት። የመጀመሪው የግለሰቡን ደህንነት ማረጋገጥ ወይም ከአደጋ መከላከልን ታሳቢ ማድረግ ሲኖርበት ሌላኛው ደግሞ ጊዜያዊ ስሜቶችን መቀነስ ብቻ ሳይሆን ተከታታይነት ባለው ህክምና የግለሰቡን በጤንነት ሰርቶ የመኖር ብቃት ማረጋገጥ የሚሉት ናቸው።

የባይፖላር ታማሚዎች በተኝቶ ህክምና እና የመድኃኒት ህክምና እንዳስፈላጊነቱ ይሰጣቸዋል። ሆስፒታል ተኝቶ መታከም አገልግሎት የሚሰጠው ህመምተኛው ለራሱ ወይም ለሌሎች አደገኛ ሆኖ ሲገኝ እና የተመላላሽ ህክምና ለውጥ ካላመጣ አስፈላጊውን ምርመራ ለማከናወን እና ለማጠናቀቅ አስተኝቶ ተኝቶ መመርመር አስፈላጊ ሲሆን ነው።

በመድኃኒት ህክምና በኩል ባይፖላር ዲስኦርደር የተለያዩ ውጤታማ ሕክምና ያለው ሲሆን ህክምናውም ሁለት ደረጃዎች አሉት

- የአፋጣኝ/ አጣዳፊ የሆነ ህክምና እና
- ተከታታይነት ያለው የረጅም ጊዜ ህክምና ሲሆኑ በሁለቱም ሁኔታዎች ውስጥ የመድኃኒት ህክምና ዋናውን ቦታ ይይዛል።

የመድኃኒት ህክምናው እንደህመሙ ደረጃ እና ህመምተኛው እንዳለበት ሁኔታ የተለያዩ መድሃኒቶችን በተለያየ መጠንና ጊዜ በማዘዝ ባይፖላር ህመምን ማከም ይቻላል። ፍቱንነታቸው የተረጋገጠ የተለያዩ ዓይነት መድኃኒቶች አሉ። እነዚህም መድኃኒቶች በሃኪም አስፈላጊው ክትትል እየተደረገ የሚሰጡ ናቸው።

የአእምሮ ህክምና ስፔሻሊስቶች የመድሀኒቱን አይነት እና መጠን በማስተካከል ከመድሀኒቶቹ ጋር ተያይዘው የሚመጡ የጎንዮሽ ውጦቶችን መቀነስ ወይም ከናካቴው እንዳይፈጠሩ ማድረግ ይቻላል።

ከመድሐኒት ህክምና በተጓዳኝ የንግግር ህክምና ወይም ሳይኮቴራፒ ባይፖላር ዲስኦርደር ላለባቸው ህመምተኞች የጎላ ጥቅም አለው የህክምናውም ውጤታማነቱ እንዲጨምር ያደርጋል።

**ምንጭ ፦ በአማኑኤል አእምሮ እስፔሻላይዝድ ሆስፒል አእምሮ ጤና እና የአእምሮ ህመም የማስተማሪያ መምሪያ የተወሰደ**

# ቀን የጣለው...

ከ16ኛ ገጽ የዞረ

አይሰስትም ። ሲሰጠው እየሰጠ ከምርቃቸው ይቀበላል ።

ከቀናት በአንዱ የለመደውን የግንባታ ሥራ ሊከውን ከአንድ ህንጻ ላይ ተገኘ። እንደወትሮው ከመወጣጫው ደርሶ የሙያው ድርሻውን ሊወጣ ከላይ ታች አለ። ዕለቱ ከወትሮው የተለየ አልነበረም። ሌሎች ሰራተኞች ልክ እንደሱ በስራ ገበታቸው ውለዋል። ከደቂቃዎች በኋላ የሆነው እውነት ግን ብዙ ታሪክ ቀየረ። የእማማ ልጅ የቆመበት እንጨት ድንገት ከእግሩ ከዳው። ራሱን ማዳን፣አካሉን መጠበቅ አልቻለም። እየተምዘገዘገ ወደ ታች ወረደ። ከመሬት ሲደርስ የተቀበለው ብረት አልማረውም። ከላዩ ሲወድቅበት ከግራ ጎኑ ጠልቆ ተመሰገ።

አወዳደቁን ከላይ ከታች ሆነው ያዩ ሊያነሱት ተጣደፉ። በደም የራሰው ተጎጂ አስትንፋሱ ይሞቃል። ህይወቱ እንዳለ ሲታወቅ ለህክምና ርዳታ ሩጫው ፈጠነ። ቁስለኛው ዕለቱን አፋጣኝ እርዳታ አገኘ። ሀኪሞቹ ተስፋ አልቆረጡም ። ለቀጣይ ክትትል አልጋ ይዞ እንዲታከም ወሰኑ ።

**እናትና ልጅ...**

ከቀናት በኋላ እናቱ ከሐረር ተጠርተው አዲስ አበባ ገቡ። ልጃቸው ዘንድ ሲደርሱ መላ አካሉ ተጎድቷል ። ውስጣቸው እያነባ ጎንበስ ቀና ብለው አስታመሙት ። ጥቂት የጭንቅ ቀናቶች አለፉ። የእማማ ልጅ ቁስል በዋዛ አልሻረም። ውሎ አድሮ ህመሙ ባሰ ። ጎኑን አልፎ ኩላሊቱ የዘለቀው ብረት መጨረሻውን አሳዛኝ አደረገው። ታታሪው የግንባታ ሰራተኛ ህይወቱ አልተረፈም።

**እንግድነትን በሀዘን ...**

የእማማና የአዲስ አበባ አጋጣሚ መልካም አልሆነም። ልጃቸውን ቀብረው በሀዘን አንገታቸውን ደፉ። ታሪካቸውን የሰማ ሁሉ ከልብ አዝኖ ደገፋቸው። የዕድሜያቸው መግፋት ከዕውቀት ማነስ ተዳምሮ ስለልጃቸው መብት አልጠየቁም። አንዳንዴ አንዳንዶች የልጃቸውን በአደጋ መሞት እያስታወሱ አሰሪውን በህግ እንዲጠይቁ ይመክሯቸዋል። መውጫ መግቢያውን ለማያውቁት አቅመ ደካማ ይህን ማሰብ ከባድ ነበር ።

ቀን አልፎ ቀን ሲተካ ብቸኝነት ዋጣቸው ። በልቶ ለማደር እጅ አነሳቸው። የሚሰጣቸውን ጥሪት ይዘው ቀናት ቆጠሩ። እማማ ተመልሰው አገራቸው አልገቡም። እንደዋዛ የለመዱት እጅ መዘርጋት ከብዙዎች አስተዋውቆ ምጽዋዕት መቀበሉን ተለማመዱት ።

ዛሬ ኑሯቸው ሀና ማርያም በተባለ ሰፈር ነው። ጎዳና ላለመውደቅ የተከራይዋት ትንሽዬ ቤት ለጎን ማረፊያ አትበቃም። እስከዛሬ በልመና ከሚያገኙት ገንዘብ የአቅማቸውን ከፍለው ኖረዋል። በቅርቡ ግን አከራዮቻቸው ቤቱን አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር አድርገውታል።

ውሏቸው መገናኛ፣ አዳራቸው ሀና ማርያም የሆነው ትልቋ ሴት ዛሬ ልመናን መተዳደሪያ አድርገው ህይወትን መግፋት ይዘዋል። ቀርቦ ላናገረ ላዋያቸው ሁሉ የልጃቸውን ታሪክ ይመዛሉ። ዛሬ ላሉበት የከፋ ህይወት የዳረጋቸው የእሱ ድንገቴ ሞት መሆኑን ሲያወጉ ፊታቸው ይጠይማል፣ በጎደጎደ ዓይናቸው ዕንባ ይሞላል ።

ከእማማ ጋር የነበረኝ ቆይታ አጭር የሚባል ነው። በዚህ አፍታ ግን ማንነታቸውን አውቄአለሁ። አሁንም ውስጤ ማዘኑን ቀጥሏል። ዕድሜያቸውን ከቀደመ ኑሯቸውና አሁን ካሉበት ህይወት እያነጻጸርኩ አርቄ አሰብኩ። ብዙ ቢያወሩኝ እወድ ነበር ። ሥራ አስፈትቼ ራታቸውን ላሳጣቸው አልፈለኩም። ተሰናብቻቸው ተለያየን።

**ሴላው ጥግ...**

ቀጠሮዬን አልረሳሁም ። አሁንም ግን ወደ እንግዶቼ እንዳልሄድ ካስገደደኝ ሌላ አጋጣሚ ጋር ተፋጠጥኩ። እማማ የሐረሯን ተሰናብቼ ራመድ ከማለቴ ዓይኖቼ በአንዲት ወይዘሮ ዓይኖች ላይ አረፉ። በንጹህ ልብሳቸው ቆሸሽ ያላየውን ንጹህ ነጠላ ደርበዋል። ጸአዳነታቸውን እያየሁ ውስጣቸውን አጤንኩት። ተክዘዋል ። ካፋቸው ጣል ያደረጉት መሸፈኛ ማስክ የፊታቸውን ገጽታ አልደበቀውም።

በአንድ ታዋቂ የገበያ ማዕከል ደረጃ ስር የተቀመጡትን ወይዘሮ በሀዘኔታ ማየት ቀጥያለሁ። ሁኔታቸው አሳዝኖኛል። እየለመኑ ነው ለማለት ግን ፈጥኜ አልደፈርኩም ። ሳላስበው አጠገባቸው ደርሻለሁና በእጄ ያለውን ጥቂት ብር በእጃቸው ላይ አኖርኩ ። ምስጋናውን ያደረሱኝ ከማቋርጥ ዕንባ ጋር ሆነ። ወትሮም ሁኔታቸው ገርሞኝ ነበርና ቀርቤ ላወጋቸው አልዘገየሁም።

በትካዜ የተዋጡት ወይዘሮ የሰውን ፊት ለማየት እየሸሹ ነው ። እጃቸውን በልመና መዘርጋት እንደተሳቀቁ ተረዳሁ። ከበረከቱት እግረኞች መሀል ጥቂቶቹን እየለዩ «እርዱኝ » ይላሉ ። የደከመ ድምጻቸው እምብዛም አይሰማም። ብርድ ከሀሩር የማያውቅ ፊታቸው ውሎውን የቻለው አይመስልም ። መጥቆርና መጎሳቆል ይዟል። በእናታቸው የዘለቀችው የቀትር ፀሀይ አላዘነችላቸውም። ያለአንዳች ከለላ አግኝታ እያንገላታቻቸው ነው።

ወይዘሮዋን ስመለከት ለልመና ህይወት አዲስ መሆናቸው ገባኝ። ልቀርባቸው አልቸገረኝም። አጠገባቸው ሆኜ ገና ጨዋታ ስጀምር ዳግም በዓይናቸው ውሀ ሞላ ። በነጠላቸው ጫፍ የሚሞዥቁት ፊት ከትኩስ ዕንባ ተዳምሮ ገጽታቸውን ለወጠው። እንዳሻቸው እንዲሆኑ ተውኳቸው።

ወይዘሮዋ የአዲስ አበባ ላይ ኑሮ ዓመታት አስቆጥሯል። አብራቸው የምትኖረው ልጃቸው ጤና አጥታ ከእጃቸው ከወደቀች ቆይቷል ። እሷን በማስታመም የቆየ አቅማቸው ዛሬ ከእሳቸው አይደለም። እግራቸውን፣ ወገባቸውን ያማቸዋል።

ህይወትን ለመግፋት ብዙ ሲደክሙ ቆይተዋል። በቤት ኪራይና በብቸኝነት ህይወት ያላዩት ፈተና የለም። አሁን እጃቸው ቢያጣ ቢነጣ የሰውን ፊትን ሊያዩት ግድ ሆኗል። እንደአባባሉ ደግሞ «የሰው ፊት እሳት ነው» ይፋጀል፣ያስፈራል። ቀናትን የቆጠረው የእሳቸው ውሎ ከዚህ እውነታ እየታገለ ነው ።

**አሥመራ ላይ ...**

ወይዘሮዋ ራሳቸውን በጎዳናው ልመና ከማግኘታቸው በፊት መልካም ህይወት ነበራቸው። አስመራ ላይ ከዶክተሩ ባለቤታቸው ጋር በደስታና በክብር ኖረዋል። ባለቤታቸው በጦር ሰራዊቱ ከሚታወቁት ሀኪሞች መሀል አንዱ ነበሩ። ዛሬ በህይወት የሉም። ከዓመታት በፊት በነበረው ውጊያ መሰዋታቸውን ወይዘሮዋ በሀዘኔታ ያወሱታል።

ይህ እውነት የሆነው ደርግ ሥልጣን ለቆ መንግሥት በተለወጠበት ጊዜ ነበር። የዛኔ እሳቸውን ጨምሮ በርካቶች ከአገረ- ኤርትራ በስደት ሊወጡ ተገደዋል። በጦርነቱ አምስት ወንድሞቻቸውን በሞት የተነጠቁት ወይዘሮ የጊዜው መዳረሻቸው አዲስ አበባ ሆነ ።

ሀኪሙ ባለቤታው ሀገራቸውን በሙያቸው አገልግለዋል ። ካለፉ በኋላ ግን ለጡረታ እንኳን የሚተርፍ ታሪክ አላገኙም ። የወቅቱ ለውጥ የነበረውን እንዳልነበር አድርጎ በእሳቸው ህይወት ጭምር ጥቁር አሻራውን አኖረ ።

ዛሬ ወይዘሮዋን በመሀል መገናኛ ለልመና ያስቀመጣቸው አንዱ ምክንያት ይኸው ሆኗል። እድሜ ሲገፋ፣ አቅም ሲደክም ማንነት ይንገዳገዳል፣ ዙሪያው ገደል ይሆናል። እንዲህ እንደአሁኑ ኑሮ ሰማይ ሲነካ ደግሞ ለእንዲህ አይነቶቹ ነፍሶች መከራው ይለያል።

**የእናቶቹ ነገር ...**

ዛሬ ሁለቱን እናቶች ከቤት አውጥቶ ጎዳና ያዋላቸው በህይወታቸው ያለፉት ጠመዝማዛ መንገድ ነው። ልክ እንደነሱ ሁሉ ትናንትን የተደላደ ኑሮ የነበራቸው ወገኖች ፣ በተለያዩ ክፉ አጋጣሚዎች የሌላውን እጅ ለማየት ይገደዳሉ። ቀን ሲጎድል፣ ዕድሜ ሲያዘነብል ደግሞ « አለሁ »የሚል ወዳጅ ዘመድ ፣ደጋፊ የሚሆን አጋር ያስፈልጋል ።

በዕድሜ ማምሻ ፣ በማረፊያ ዘመን የሚያጋጥም የህይወት ስብራት በቀላሉ አይጠገንም ። ወድቆ ላለመቅረት ተረስቶ ላለመተው የሁሉንም ወገን ትብብር ያሻል። የቀድሞውን ማክበር ለነገ ማንነት መሰረት ነውና ።

# ከኢፌዴሪ ግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚታተም

ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

# የጥጥ ሰብል ነባራዊ ሁኔታዎችና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው

**በሰለሞን ደምሰው**

የጥጥ ሰብል በ17ኛው እና 18ኛው ክፍለ ዘመን አሜሪካና እንግሊዝ “Cotton is King” በሚል የኢንዱስትሪ አብዮትን ሲያቀጣጥሉ ከፍተኛ ድርሻን ያበረከተ ሰብል ነው። አሁን ለደረሱበት እድገት መሰረት እንደሆነም ይነገራል። መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የጥጥ ሰብል ጨርቃ ጨርቅን ጨምሮ ከ70 በላይ ለሚሆኑ ኢንዱስትሪ ምርቶች በግብዓትነት ይውላል። ሰብሉ በሚለማባቸው ከ70 በላይ በሚሆኑ ሀገራት ውስጥ ደግሞ ወደ 100 ሚሊዮን የሚጠጉ ጥጥ አልሚዎች ይገኛሉ።

ጥጥ ባለው ረዥም የእሴት ሰንሰለትና ቅብብሎሽ ምክንያት በቀጥታና በተዘዋዋሪ ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ይታወቃል። በአሁኑ ወቅትም በዓለም አቀፍ ደረጃ 250 ሚሊዮን ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል የፈጠረ ሰብል ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በዓመት 1 ነጥብ 5 ትሪሊየን የአሜሪካን ዶላር ዓመታዊ የጥጥ ንግድ ልውውጥ እንደሚደረግም መረጃዎች ያሳያሉ። እንደ ዓለም አቀፍ የጥጥ አምራች ሀገራት ህብረት መረጃ መሰረትም በየዓመቱ ከ30 እስከ 34 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በጥጥ ሰብል በመሸፈን ይለማል። በ2021/22 ምርት ዘመን በዓለምአቀፍ ደረጃ 33 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለምቷል። ከዚህ ውስጥ ህንድ 12 ነጥብ 6፣ አሜሪካ አራት፣ ቻይና 3 ነትብ 1፣ ፓኪስታን 2 ነጥብ 1 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በማልማት በቅደም ተከተል ተቀምጠዋል። በምርት ረገድም በየዓመቱ በአማካይ ከ26 እስከ 27 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የተዳመጠ ጥጥ ይመረታል።

በአህጉራችን አፍሪካ ቤኒን፣ ቡርኪናፋሶ፣ ካሜሮን፣ ኮትዲቫርና ማሊ ግንባር ቀደም ጥጥ አምራች ሀገራት ናቸው። ቢሆኑም እሴት በመጨመር ብዙም አልገፉበት።



**ሰፋፊ የእርሻ መሬት የሚጠይቀው የጥጥ ምርት**

የሚያመርቱትን ጥጥ ኤክስፖርት በማድረግ ብቻ በቀጥተኛ የውጪ ምንዛሪ ግኝት ይጠቀሙበታል። በአንፃሩ ግብፅ እሴት በመጨር በየዓመቱ በዓማካይ 550 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ከጥጥና ከጥጥ ምርቶች ኤክስፖርት ገቢ ታገኛለች። ኢትዮጵያና ታንዛኒያ ከግብፅ በመቀጠል የሚያመርቱትን ጥጥ በሀገር ውስጥ እሴት በመጨመር የተሻለ ደረጃ ላይ ይገኛሉ።

ኢትዮጵያ የጥጥ ሰብልን በማምረት በርካታ ክፍለ ዘመን ያስቆጠረ ታሪክ አላት። ቢሆንም ጥጥን በሰፋፊና የተሻሻለ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ማምረት የጀመረችው በ1960ዎቹ ሚቼልኮት በተባለ የእንግሊዝ ኩባንያ ነበር። በአዋሽ ተፋሰስ አካባቢ የጥጥ ልማቱም እየተስፋፋ ሄዶ ሽፋኑ እስከ 140 ሺህ ሄክታር ደርሶ ነበር።

በ1974 ዓ.ም ሀገራችን ወደ ሶሻሊዝም ሥርዓት ባደረገችው ለውጥ ምክንያት የግል እርሻዎች ወደ መንግሥት እንዲዞሩ የተደረገ ሲሆን ይህም በጥጥ ሽፋን ላይ ከፍተኛ መነቃቃትና መሻሻል እንዲፈጠር አስችሏል። ከ1991 በኋላ በመንግሥት ተይዘው የነበሩ የጥጥ እርሻ ልማት ድርጅቶች ወደ ግል ይዞታነት እንዲዘዋወሩ ስለተደረገ የመሬት ሽፋኑም ሆነ ምርቱ እየቀነሰ መጥቷል። በ2013/14 ምርት ዘመን ወደ 55 ሺህ ሄክታር ሲወርድ ዓመታዊ ምርቱም ወደ 35 ሺ ሜትሪክ ቶን አዘቅዝቋል። ይኸውም ለጥጥ ተስማሚ ከሆነው 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ በጥጥ የተሸፈነው መሬት ከ2 በመቶ በታች እንዲወርድ አድርጓል።


አሁን ላይ መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት ከሰጣቸው ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች መካከል የጨርቃ ጨርቅና ስፌት ዘርፉ ዋነኛ መሆኑ ይታወቃል። ይህንንም ተከትሎ በስፋት በተገነቡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥና ከፓርክ ውጭ የጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንቨስትመንት መስክ ያለውን አንፃራዊ ጠቀሜታ ታሳቢ በማድረግ በርካታ ባለሃብቶች ወደ ዘርፉ በመግባት ላይ ይገኛሉ።

አሁን ያሉት ነባርና አዳዲስ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው የሚያመርቱ ቢሆን ከ100 ሺህ ሜትሪክ ቶን በላይ የተዳመጠ ጥጥ ምርት እንደሚጠቀሙ ይጠበቃል። በተጨማሪም በኢንቨስትመንትና በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኙ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ወደ ሥራ የሚገቡ ከሆነ አጠቃላይ ሀገራዊ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ጥጥን የመጠቀም አቅማቸው ወደ 200 ሺህ ቶን ከፍ ሊል እንደሚችል ይገመታል።

ስለሆነም ይህንን ከፍተኛ የአቅርቦት ክፍተት መሙላት ይጠበቃል። ሀገራችን የጥጥ ሰብልን ለማልማት ያላትን ዕምቅ አቅም መጠቀም ያሻል። የኢንዱስትሪዎችን የጥጥ ፍላጎት ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ አቅርቦት መሸፈንም ይገባል። እንዲሁም ትርፍ ምርት በማምረት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እንዲያስችል በቀጣይ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ያስፈልጋል።

በምግብ ራስን መቻል፣ እሴት መጨመር፣ የገቢ ምርትን መተካት፣ ኤክስፖርት፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ ሰብሎችን ማምረት፣በግብርናው ዘርፍ የአስር ዓመት ዕቅድ መጨረሻ ላይ የተሻገረ ግብርና ዕውን እንዲሆን ትኩረት ተሰጥቶ ከሚሠራባቸው ይጠቀሳሉ። እንደዚሁም የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የምጣኔ ሃብት መዋቅራዊ ሽግግር፣ የአርሶ አደሩን ገቢ ማሳደግና ድህነት ቅነሳ ከትኩረት መስኮች መካከል ናቸው። ጥጥም በትኩረት ከሚሠራባቸው ዋንኛው ነው። ሁሉም እንዲሳኩ በማድረግ ረገድ ያለው ሚና የጎላ ነው። በመሆኑም የጥጥ ልማት በአጠቃላይ ለግብርናው ዘፍርና ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ያለው አስተዋፅኦ እጅግ ከፍተኛ ነው።

# ስፖርት



## የትግራይ ክልል አትሌቲክስን ወደ ነበረበት የመመለስ አበረታች ጅምር

ብርሃን ፈይሳ

ከማርሽ ቀያሪው ምሩጽ ይፍጠር አንስቶ የ5ሺ ሜትር የዓለም ክብረወሰንን እስከሰበረችው ጉዳፍ ጸጋዬ ድረስ በዓለም አቀፍ ውድድሮች ኢትዮጵያን የወከሉ 33 ብርቅዬ አትሌቶችን አበርክቷል፤ የትግራይ ክልል። የዘንድሮ የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ አሸናፊ እንደሆነው ወጣቱ አትሌት ቢንያም መሃሪ ያሉ ተተኪ አትሌቶችንም በማፍራት ላይ ይገኛል። በተለያዩ ስፖርቶች ብሄራዊ ቡድንን መወከል የቻሉ በርካታ ስፖርተኞችን በማፍራት እንዲሁም በሀገር ውስጥ ውድድሮችም ጠንካራ ፉክክር በማድረግ ከሚጠቀሱ ክልሎች መካከል አንዱ ትግራይ ነው።

ከ2012 ዓም አንስቶ እስካለፈው ዓመት ድረስ በክልሉ በነበረው ጦርነት ምክንያት ተጎጂ ከሆኑ ዘርፎች አንዱ ስፖርት ነው። ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ ክልሉን መልሶ ለማቋቋም እየተደረጉ ከሚገኙ ጥረቶች አንዱም የስፖርቱ ዘርፍ ነው።

የትግራይ ክልል በተለይም በአትሌቲክስ ስፖርት ውጤታማ ሲሆን፤ በተለይ እንደ ማይጨው ያሉ የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከላት በርካታ አትሌቶችን በማፍራት ይታወቃል። ነገር ግን በክልሉ በነበረው ጦርነት ምክንያት በሚሊዮኖች የሚገመት ውድመት በአትሌቲክስ ስፖርት ብቻ ደርሷል። የትግራይ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ኪዳነ ተክለሃይማኖት ጉዳቱን በተለያየ ዘርፍ ከፋፍለው ይመለከቱታል። የማዘውተሪያ ስፍራዎችን በሚመለከትም፤ ደረጃውን የጠበቀ መም ባለቤት የነበረው የመቀሌ ስታዲየም ከባድ ተሽከርካሪዎች ሲንቀሳቀሱበት በመቆየቱ ለብልሽት ተዳርጓል። ቀድሞ በኮረም ለመገንባት መሰረት ድንጋይ የተቀመጠለት የአትሌቲክስ መንደር እንዲሁም በሂደት ላይ የነበረው የአጭርና ሜዳ ተግባራት ማዕከልም እንቅስቃሴያቸው ሳይጀመር ሊቋረጡ ችለዋል።

በአትሌቲክስ ስልጠና ዘርፍም፤ ክልሉ ቀድሞ የነበሩት 8 ማዕከላት(ከ30-50 አትሌቶችን ያሰለጥኑ የነበሩ) ወደ 6 ሊወርዱ ችለዋል። ምክንያቱ ደግሞ ማዕከላቱ ያስተናገዱት ጉዳት ሲሆን፤ የስልጠና ቁሳቁሶችም ተዘርፈዋል። ለአብነት ያህል ውጤታማው የማይጨው አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል በአጠቃላይ ሲተመን 30ሚሊዮን ብር የሚገመት ጉዳት ደርሶበታል። ክለቦችን ሳይጨምር በጠቅላላው የክልሉ አትሌቲክስ ስፖርት ያስተናገደው ጉዳትም ከ43 ሚሊዮን ብር በላይ መሆኑም በቀረበው ሰነድ ተመላክቷል። በስፖርቱ ላይ የደረሰው ውድመት የጦርነት አስከፊነት በሁሉም ዘርፍ አውዳሚ መሆኑን ያሳየ ሲሆን፤ ከንብረት ባለፈ በርካታ የስፖርቱ ባለሙያዎች ህይወትም ተቀጥፏል። ከእነዚህም ውስጥ ጥቂት የማይባሉት አትሌቶች ናቸው። ይህ የደረሰው አስከፊ ጉዳት ሲጠቃለልም ስፖርቱን ወደኋላ የመለሰ እንደነበረም ፕሬዚዳንቱ አስታውሰዋል።

ከሰላም ስምምነቱ በኋላም ስፖርቱን ለማገዝ የሚያስችል የ2 ሚሊዮን ብር እና የትጥቅ ድጋፍ የተደረገለት ሲሆን፤ በዚህም አበረታች የሚባሉ ሥራዎች ተከናውነዋል። የስልጠና ማዕከላትን ወደ ሥራ ለመመለስ በተደረገ ጥረት 6 የሚሆኑት በተቻለ አቅም ስልጠናቸውን ጀምረዋል። የፕሮጀክቶች ውድድር በማዘጋጀትም ማዕከላቱ እንዲሁም ክለቦች የአትሌቶች ምልመላ ማድረግም ችለዋል። የመደበኛ ውድድሮች ተሳትፎን በሚመለከትም ባለፈው ዓመት በተካሄደው 52ኛው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ላይም አትሌቶችን አሳትፏል። በሌላ በኩል ክልሉ ስፖርቱን በማነቃቃት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የቆየውን ህዝብ ለማንቀሳቀስ የተለያዩ ስራዎች እያከናወነ ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል አንዱ ህዝባዊ የጎዳና ሩጫዎችን ለአራት ጊዜያት በተከታታይ(በመቀሌ እና አክሱም ከተሞች) ማዘጋጀት ነው።



የትግራይ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ኪዳነ ተክለሃይማኖት፣

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ባለፈው ሳምንት በክልሉ ያካሄደውን ጠቅላላ ጉባኤ ተከትሎ የተደረገው የማራቶን ሪሌ ውድድርም ስፖርቱን በማነቃቃት ረገድ ከተከናወኑ ሥራዎች መካከል ተጠቃሽ ነው። ሀብት ለማሰባሰብ በዕቅድ ቢሰራም በስፖንሰሮች ተሳትፎ ማነስ ምክንያት ውጤታማ ሊሆን አልቻለም። በዚህና ክልሉ ከነበረበት ሁኔታ አንጻርም ስፖርትም ሆነ አትሌቲክስ በፋይናንስ ረገድ ያለው ሁኔታ አሁንም ከችግር ያልተላቀቀ መሆኑን ተከትሎም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን 150ሺ ብር ድጋፍ ሰጥቷል። ከጠቅላላ ጉባኤው በኋላም በስፖርቱ ባለሙያዎች አማካኝነት የስነልቦና እና የተሳትፎ ስልጠናም ተሰጥቷል። በተጨማሪም በክልሉ ለሚገኙ ተፈናቃዮች የ2 ሚሊዮን ብር እገዛ በፌዴሬሽኑ ተደርጓል።

ይህንን ተከትሎም የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ስፖርት ኮሚሽነር ተክላይ ፈቃዱ፤ ፌዴሬሽኑን ጨምሮ የክልል ስፖርት ቤተሰቦች ላደረጉት ሁሉ ምስጋናቸውን አቅርበዋል። ምንም እንኳን ክልሉ አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ቢገኝም ነባራዊውን ሁኔታ መሰረት ባደረገ ሁኔታ የፌዴሬሽኑን ዕቅድ ወስዶ በተግባር ለማዋል የሚሰራ ይሆናል። ስፖርት የሰላምና የወዳጅነት መገለጫ እንደመሆኑ የሰላሙን ፍሬ ማሳያ ይሆናል፤ በሚቀጥለው ጊዜም ክልሉ አሁን ከነበረው ሁኔታ በተሻለ አቋም ላይ እንዲገኝ ጥረቱ እንደሚቀጥልም ጠቁመዋል።

ስፖርቱን በበላይነት የሚመራው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ በበኩሏ፤ የገንዘብ ድጋፉ ክልሉ ባለፉት ሶስት ዓመታ ተሳትፎ ስላልነበረው በልዩ ሁኔታ የተበረከተ መሆኑን ገልጻለች። ከዚህ ባለፈ በክልሉ ያሉ የአትሌቲክስ ማዕከላትና ፕሮጀክቶች መሰረተ ልማት የተጎዳ በመሆኑ በምን መልኩ መጠገንና የስልጠና ቁሳቁሶችን መልሶ ወደ ሥራ መመለስ ይቻላል በሚለው ላይ በሥራ አስፈጻሚ ደረጃ ውይይት ተደርጓል። በተጨማሪም የዳኝነት፣ የአሰልጣኝነትና ሌሎች ሙያዊ ስልጠናዎችም በፌዴሬሽኑ ባለሙያዎች ይሰጣል፤ ፌዴሬሽኑ ይህንን ሲወስንም በደስታ ነው። ከክልሉ የወጡ አትሌቶች ያለባቸውን ጫና ችለው በኦሊምፒክ፣ በሁለት የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናዎች፣ በወጣቶች ቻምፒዮና እንዲሁም በቤት ውስጥ ውድድሮች ኢትዮጵያ የተሻለ ውጤት እንድታገኝ አድርገዋል። በዚህም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ከልብ ያመሰግናል፤ የጥንካሬ ተምሳሌቶች ናቸውም ብላለች።


ሐበሻ habesha

### የፎርክሊፍት ጎማዎች
### ግዢ የጨረታ ማስታወቂያ
### የጨረታ ቁጥር፡ HBSC/01/0222/23

ሐበሻ ቢራ ፋብሪካ አክስዮን ማህበር የተለያዩ መጠን ያላቸው ለፎርክሊፍት የሚያገለግሉ ጎማዎችን ከቸርኬ (Rim) ጋር በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል። በመሆኑም ፍላጎትና አቅም ያላችሁ ተጫራቾች አዲስ አበባ ከካርጎ ፊት ለፊት ከአዲስ የልብ ህክምና ክሊኒክ ጎን በሚገኘው የሐበሻ ቢራ ፋብሪካ አ.ማ ዋና መ/ቤት ከህዳር 25 እስከ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ባሉት ተከታታይ የስራ ቀናቶች ውስጥ የማይመለስ 200 ብር በመክፈል የጨረታ ሠነድ በመግዛት መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ድርጅቱ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ሐበሻ ቢራ ፋብሪካ አ.ማ.**



### በድጋሚ ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ
### ጨረታ ቁጥር 06/2016

የአዳማ ጉምሩክ ኮሚሽን ቅ/ጽ/ቤት የጋራዥ አገልግሎት በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

ስለሆነም ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሠረት

1. ተጫራቾች ህጋዊ የታደሰ ንግድ ፍቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ የምስክር ወረቀት ያላቸው፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ የምስክር ወረቀት ያላቸው እንዲሁም የዘመኑን ግብር የከፈሉና ግዴታቸውን የተወጡ መሆን አለባቸው፡፡
2. ተጫራቾች ይህ ጨረታ በማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት 15ቀናት ውስጥ የማይመለስ ብር 100 /አንድ መቶ ብር/ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን ከልቻ ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር ቅጥር ግቢ በሚገኘው አዳማ ጉምሩክ ኮሚሽን ቅ/ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 31 በመቅረብ መግዛት ይቻላሉ፡፡
3. የጨረታ ሳጥኑ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ባሉት ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ታሽጐ በዛው ቀን ከጠዋቱ 4፡10 ሰዓት በግዥና ፋይናንስ ቡድን ቢሮ ይከፈታል፡፡ ዕለቱ የስራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት የጨረታ ሳጥኑ ታሽጐ ይከፈታል፡፡
4. ማንኛውም ተጫራች ለመጫረት ያቀረበውን አጠቃላይ 2% በባንክ የተመሰከረለት ቼክ /ሲ.ፒ.ኦ/ ወይም በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ጋራንቲ በአዳማ ጉምሩክ ኮሚሽን ቅ/ጽ/ቤት ስም አሰርቶ ማቅረብ አለበት፡፡ ቅ/ጽ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ**

**የግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ቢሮ ቁጥር 31**

**ስልክ ቁጥር 022-2-11-58-90/022-2-11-58-07**

**የአዳማ ጉምሩክ ኮሚሽን ቅ/ጽ/ቤት**